## ኤዲቶሪያል

# ተነጋገሩ፣ ተደማመጡ፣ አርአያ ሁኑ!

ከሳምንት በፊት በግብጽ በተካሄደው የናይል (የአባይ) ተፋሰስ አገሮች የሚኒስትሮች ም/ቤት ስብሰባ የጋራ ተጠቃሚነት የትብብር ማዕቀፍ ስምምነት ከዘጠኙ ባለቤቶች በሁለት አገራት /ግብጽና ሱዳን/ እምቢተኝነት ሳይሳካ ቀርቷል:: በየጊዜው በሚሰጧቸው መግለጫዎች «ታሪካዊ መብታችን ይጠበቅ» ከሚለው መደራደሪያ ጋር ባላቸው የገዘፈ ወታደራዊ መዋቅርና ዘመናዊ የመሳሪያ ትጥቅ በመመካት የፊት ለፊት «ጦርነት ሊቀሰቀስ ይችላል» ዛቻ ግን ምላሹ የተለመደው ውስጥ ወይራ አቋማችን ነበር::

ኢትዮጵያውያንን አስመልክቶ የተጻፉ ጽሁፎች በአዎንታዊነቱ ከሚያወሱት ጉዳይ አንዱ ከውጭ የሚቀሰቀሱብንን ጥቃቶች በአይበገሬነት ለመከላከል የምናሳየው ቁርጠኝነት ነው:: አንድ ምሳሌ መመልከት እንችላለን:: ሐምሌ ወር 2001 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የናይል (የአባይ) ተፋሰስ አገሮች የሚኒስትሮች ም/ቤት 17ኛውን መደበኛ ስብሰባውን ቢያደርግም ቀደም ሲል በኪንሻሳና በናይሮቢ በተደረጉ የውሳኔ ሃሳቦች ላይ ግብጽና ሱዳን ውጤቱን አንቀበልም ማለታቸው የራሱን አሉታዊ አሻራ አሳርፎ ነበር:: ይህም በቀጣናው ጦርነት ሊቀሰቀስ ይችላል በሚል ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ባለድርሻ አካላቱን በማነጋገር ያቀረቧቸው ዘገባዎች የፈጠረው ስጋት ሲሆን ከስጋቱ ተቋዳሾች አንዷ አገራችን ነበረች:: በወቅቱ በካይሮ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስ ፕሮፌሰር የነበሩት ኤግላል ራፋት ስምምነት ላይ ካልተደረሰ በውሃ የተነሳ ጦርነቶች ሊቀሰቀሱ ይችላሉ ሲሉ ለማስጠንቀቅ ሞክረው እንደነበር ይታወሳል::ይህን ስጋት አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ የውኃ ኃብት ልማት ሚ/ሩ ሐምሌ 28 ቀን 2001 ዓ.ም በፅ/ቤታቸው በሰጡት መግለጫ ላይ በ21ኛው መቶ ክ/ዘመን ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የጦርነት መከሰት ይኖራል የሚል ግምት እንደሌላቸው ከገለጹ በኋላ በአንድ ነጥብ ላይ አበክሮ ሰጥተው ተናገሩ:: «ከግብጽ ጋር በአንድ ወቅት ጉንደት ላይ ጦርነት ገጥመን አሸንፈናቸው እንደነበር ይታወሳል::» በማለት ለውጪ ጥቃት የሚታጠፍ ግንባር የለንም የሚል ውስጠ ወይራ መልዕክታቸውን አስተላለፉ::

ይህ ሁኔታ ኢትዮጵያውያን የቱንም ያህል በዝቅተኛ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ላይ እንሁን እንጂ በሉኣላዊነታችን ለሚቃጡ ጥቃቶች ያለን አቋም ዘመን የማይሽረው መሆኑን የሚያሳይ ነው ብለን እናምናለን::

እንደ አገርና ሕዝብ በጋራ እንድንቆም የሚያደርጉን ሁለንተናዊ ጉዳዮች ቢኖሩም በፖለቲካው ዘርፍ ግን አብረን ከምንቆምላቸውና ተደማምጠን ፍትሐዊ ውሳኔዎች ላይ ከምንደርስባቸው እንዲሁም በሕግ ስርአት ከምንገዛባቸው ነገሮች ይልቅ የምንለያይባቸው፣ ከስነ አመክንዮ ይልቅ ግብታዊነትን የምናስቀድምበቸው፣ ከሕግ አምባገነዊነትን የምናንፀባርቅባቸው፣ ተሞክሮዎች እየበዙ በመሄዳቸው ውስጣችንን በመፈተሽ እርምት ካልወሰድን አፍራሽ አካሄድ እየተከተልን ነው ለማለት እንፈልጋለን:: እነዚህ አፍራሽ አካሄዶች በየፖለቲካ ፓርቲዎቹ የሚታዩ፣ኃላፊነቱ በተጣለባቸው ልሂቃን በየአደባባዩ ያለህሊናዊ ተጠየቅ የሚተገበሩ መሆናቸው ደግሞ ሁኔታውን የበለጠ አሳሳቢ ያደርገዋል::

ልዩነት ተፈጥሯዊና አስፈላጊ ነገር ነው ብለን እናምናለን:: በጽንፈ ዓለሙ ውስጥ ያሉት ፍጥረታት በሙሉ አንዳቸው ከሌላቸው ጋር የተለያዩ የሚሆኑበት የየራሳቸው አሻራ አላቸው:: የፊዚካል ሳይንስ አጥኝዎች እንደሚሉት በአንድ መጋዘን ሙሉ ካለ የስንዴ ክምችት ፍፀማዊ አንድነት ያላቸው ሁለት ቅንጣቶች ማግኘት አይቻልም:: ወደፖለቲካዊ አስተሳሰብ ስንመጣም ግለሰቦች በተለያዩ አስተሳሰቦች ላይ የራሳቸውን ግንዛቤና አቋም መያዛቸው፣ በሚያስማሟቸው ጉዳዮች ላይ መደጋገፋቸውና በተቃራኒ ሁነቶች ላይ በአንፃሩ መሰለፋቸው የሚጠበቅ እውነታ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ፖለቲከኞችና የፖለቲካ ፓርቲዎች ከዚህ ሊያመልጡ እንደማይችሉ እንረዳለን::

ልዩነትና አንድነት ግን የሚገዙበት ሕግ፣ የሚመሩበት ስርአትና ጤናማ ባሕርይ ካልተከበረ ልንግባባቸው በሚገቡን ጉዳዮች ተለያይተን በሚያለያዩ አሉታዊ ተግባራት ደግሞ አብረን እንድንቆም እንገዳለን:: ይህም እስካሁን እየተፈጠሩ ተገቢውን ኃላፊነታቸውን ሳይወጡ ለተሰነጣጠቁትና የይስሙላ ድርጅት ሆነው መንቀሳቀስ የማያሳፍር ተግባር ለሆነላቸው ፖለቲካ ፓርቲ ተብዮዎች መሰረት ጥሏል ብለን እናምናለን::

የአገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለመደው አሉታዊ አካሄድ ሲከፋፈሉና መሪዎቹም የከፋ ነቀፌታ ሲደርስባቸው የእጃቸውን አገኙ ሊባል ይችላል:: የዘሩትን ነው ያጨዱት፤ ተጠያቂነቱም ከራሳቸው አይወርድም ማለት ይቻላል:: ድክመታቸው ውድቀታቸውና ለሕዝቡ የነሱት አክብሮት መንሳት ፈጥኖ ወይም ዘግይቶ እንደሚጎዳቸው ይታወቃል:: ጦሱ ግን በእነርሱ ላይ ብቻ አያቆምም!

እንደሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሉኣላዊነቱ መጽናት ሲቆም ኖሯል፣ ማሕበረሰባዊ መግባባት እንዲፈጠር በከበሩ ባሕላዊ ዘዴዎች ተግቷል፣ ለልማቱ ሌት ተቀን ለፍቷል፣ ለሕግ የበላይነት አክብሮት አሳይቷል:: ለሉኣላዊነቱ ያደረገው ተጋድሎ ግን በድል አጥቢያ ሲመክን፣ ለልማቱ እውን መሆን የሚያፈሰው ላብ የጥቂቶችን ኑሮ በማደላደል ሲመዘበር፣ ለሕግ የበላይነት ያለው አክብሮት በማን አለብኝነት የፍትሕን ልዕልና በሚያወርዱ ወገኖች ሲብጠለጠልበትና የመሳሰሉት አሉታዊ ችግሮች ሲደራረቡበት መፍትሔ ሊያመጡ ይችላሉ በሚል በተለያየ መንገድ ድጋፉን የሚሰጣቸው ወገኖች ተጨማሪ ችግር ሲሆኑበት የቀጥታ ተጎጂ የሚሆንባቸው መንገዶች ሊታዩ ይገባል እንላለን::

የፖለቲካ ልሂቃን በርዕዮተ ዓለም፣ በአደረጃጀትና በአስተሳሰብ የየራሳቸውን አካሄድ ቀርፀው ሲነሱ አባላትን የሚመለምሉት ከሕዝብ ውስጥ ነው:: የገንዘብ ምንጫቸው ዓላማቸውን በተለያ ምክንያትና መንገድ የሚደግፈው ሕዝብ ነው:: ቃል የሚገቡት፣ ተስፋ የሚሰጡት ለሕዝቡ ነው:: የፖለቲካ አስተምሕሯቸውን የሚያስፋፉት በሕዝቡ ውስጥ ነው:: በዚህም እኔነትን ይፈጥራሉ፣ ተስፋ ይጣልባቸዋል እንዲሁም በአርአያነት ይታያል:: የአገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ እስከዚህ እርከን ድረስ ለመወጣጣት የጎላ ችግር አይታይባቸው::

በሁለንተናዊ ቅስቃሴ ሕዝባዊ ተቀባይነትን አግኝተው ግቦቻቸውን ለማሳካት ወደጎዳናው ከገቡ በኋላ ግን ቀደም ሲል የተመለከተናቸው አሉታዊ መገለጫዎች መከሰት ስለሚጀምሩ ሁለንተናዊ ድጋፉን ሲሰጣቸው የኖረውን ሕዝብ በቀጥታ ተጎጂ ያደርጉታል:: ከጥሪቱ ቀንሶ የደገፈው አጋርነቱን ያሳየውና የቀጥታ ተሳታፊ የሆነበት ድርጅት በግለኝነት አዙሪት ወስጥ በገቡ ልሂቃን እንዳልተጠበቀ ሆኖ ሲቋጭ የሚኖርበት አካሄድ ሊገታ ይገባቸዋል:: ቀደም ሲል

የነበሩትን በርካታ መሰል ሕፀጾች ትተን ባለፈው ሳምንት የተፈፀመ አንድ ፖለቲካዊ ክንውን በምሳሌት ማንሳት እንችላለን።

የ3ኛው አገር አቀፍ ምርጫ መጠናቀቅ ተከትሎ በተከሰተው ያለመግባባት በእስር ላይ ቆይተው የነበሩተና ከእስር ከወጡ በኋላም «የተለያዩ» ፓርቲዎችን ከመሰረቱት ቡድኖች አንዱ 4ኛው አገር አቀፍ ምርጫ ሊካሄድ የአንድ ወር ያህል ጊዜ ሲቀረው አጠቃላይ ጉባኤ በመጥራት አመራር የመረጠው ከ«አንድነት» ፓርቲ አባልነት ተሰርዘዋል የተባሉ አባላት ጉዳይና እግዱን ባስተላለፉት ወገኖች ውስጥ ያለው አውድ ቀደም ሲል ለጠቀስነው መደማመጥ እየተቻለ ያለመደማመጥ፣ መግባባት እየተቻለ ያለመግባባት፣ ከስነአመክንዮ ይልቅ ግብታዊነት፣ ከሕዝብ ይልቅ ራስን የማዳመጥ ችግር ምሳሌ ይሆናል ብለን እናምናለን። በአሁኑ ሰአትም እስካሁን የሚታወቀው እና ከሳምንት በፊት የተመረጠው  አመራር በፓርቲው ሕጋዊ ባለቤትነት ላይ የይገባኛል «ክርክር» የሚጀምሩበት ምዕራፍ ተከፍቷል። በአንፃራዊ ሁኔታ የበለጠ ተግባብቶ ለመስራት በሚያስችል ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ቢያልፉም፣ እነሱን ተስፋ ያደረጉ ወገኖች መጠነ ሰፊ መስዋዕትነት ቢከፍሉም፤ ቀደም ሲል የነበረው ገንብቶ መናድ ተደግሞ ሌላ ዙር ራስን ማዳመጥ ቀጥሏል። በየትኛውም ወገን ላይ ጣታችንን ለመቀሰር ፍላጎቱም አላማውም የለንም። እነዚህ ወገኖች  ከአምስት ዓመት በፊት ከገቧቸው ቃላት ተነስተን ግን ይበጃል የምንለውን መልዕክት  እናስተላልፋለን።

የፖለቲካ ፍጥጫ እንዲቆም፣ ግልጽነት፣ ታማኝነት፣ ኃቀኝነትና ዘላቂነት እንዲኖር፣ በሕዝቡ መካከል በውይይት፣ በመደማመጥና በመቻቻል ላይ የተመሰረተ  እኩልነት እንዲኖር ወዘተ፣ ጥረት እንደሚያደርጉ ገልፀው ነበር። አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎችም እንዲሁ ያደርጋሉ። እየተመለከትን እንዳለው ግን የፖለቲካ ፍጥጫው  በእነሱ የባሰ መሆኑን ነው። አበው ሲተርቱ «...ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጣ?»እንዲሉ አማራጭ መፍትሄ ያመጣሉ የተባሉ ወገኖች ለውዝግቦቻቸው መፍትሄ ሲያጡ አሳዛኝ ይሆናል። የተለያዩ መግለጫዎች ይሰጡ እንጂ እውነተኛው ጉዳይ ሕዝቡን በሚያሳምን መንገድ አልቀረበም። መደማመጥ ፈጽሞ ርቋል። ቃልና ተግባር ለየቅል ወድቀዋል እያየን ነው። የእጃችሁን ታገኛላችሁ፣ ትጠየቃላችሁ፣ ማለት ይቻላል። ከዚያ በፊት ግን የአንዲት ኢትዮጵያ ልጆች ናችሁና ተነጋገሩ፣ ተደማመጡ፣ አርአያ ሁኑ የሚለውን መልዕክት በምሳሌነት ላነሳናቸውም ለሌሎቹም እናስተላልፋለን። ያሉብን ዘርፈ ብዙና ስር የሰደዱ ችግሮችም ይህንኑ ይሻሉ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

## verbatim

**«ነገሩ ሲጣራ ብዙ ችግሮች የሚመጡት ከእነሱ ነው። ገዥው ፓርቲ እስካሁን ጥቂት ችግሮች ነው የተገኙበት። ተቃዋሚዎች ግን ብዙ አጥፍተዋል።»**

**አቶ ሬድዋን አማን**

**የኢህአዴግ ስራ አስፈፃሚ አባልና በአዲስ አበባ የፓርቲው ተጠሪ**

የምርጫ ስነ ምግባር ደንቡ ከወጣ በኋላ አፈናና ወከባ አልቆመም የሚሉ ተቃዋሚዎች አሉ? ተብሎ ከሳምንታዊው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ የተወሰደ።

***«እኔና ክቡር ጠ/ሚኒስትሩ በኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ በሚነሱ ክርክሮች ላይ ብዙ ጊዜ አንግባባም:: የሳቸውን አመለካከት በደንብ ባላውቅም ወደ ኮሚኒስታዊ አመለካከት ያጋደለ ይመስለኛል»***

***አቶ ተመስገን ዘውዴ***

***የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባልና የአንድነት ፓርቲ ም/ሊቀመንበር***

*በተደጋጋሚ ፓርላማ ውስጥ ከጠ/ሚኒስትሩ ጋር ጠንከር ያሉ ቃላትን ትለዋወጣላችሁ... ምክንያቱ ምንድነው? ተብሎ ከአዲስ ፕሬስ ጋዜጣ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ::*

***«በ1997 ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ በአውሮፓ ሕብረት ታዛቢ ቡድን ላይ አንዳንድ ወቀሳዎች ቀርበው እንደነበር እናውቃን:: አሁን ያ እንደማይደገም ተስፋ እናደርጋለን»***

***ሚስተር ቲጂስ በርማን***

***የአውሮፓ ሕብረት ታዛቢ ቡድን መሪ***

*ባለፈው ዓርብ በሂልተን ሆቴል በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ከተናገሩት የተወሰደ::*

## ዜናዎች

# «የአውሮፓ ሕብረት ተልዕኮ ምን እንደሆነ አላወቅንም»

***መድረክ***

በኤልያስ ገብሩ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ሕገ መንግስቱን፣ የምርጫ ሕግንና የስነ ምግባር ደንቡን በመጣስ በመድረክ፣ በመድረክ ዕጩዎች፣ አባላትና በመራጩ ሕዝብ ላይ እየተሰነዘረ ያለውን ሕገ-ወጥ እርምጃ በአስቸኳይ ይቁም የሚል ጋዜጣዊ መግለጫ በአመራሮች ከትናንት በስቲያ በጽ/ቤቱ ተሰጥቷል::

በ24 ጉዳዮች ላይ ተፈፀሙ የተባሉ ችግሮች ተዘርዝረው የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ የጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ የማስፈራሪያ ንግግሮች፣ መድረክ የሚወዳደርባቸውን የተለያዩ ቦታዎች በመጥቀስ እጩዎችንና አባሎችን የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ መከልከላቸው፣ እጩዎች እየተደበደቡ መታሰራቸው፣ የምርጫ ቅስቀሳ ስብሰባ በኢህአዴግ ካድሬዎች እንዲበተን መደረጉ፣ እጩዎችና የእጩ ቤተሰቦችን ማዋከብ፣ ማስፈራራትና በጥቅም መደለል፣ የመድረክን የምርጫ ምልክት ፓስተር በህዝብ ፊት መቅደድ፣ ከተለጠፈበት መቅደድና እንዳይለጠፍ ማደረግ ተጠቅሰዋል::

እንዲሁም ተማሪ ቢያንሳ ዳባ የተባለ ግለሰብ በ29/7/2002 ዓ.ም በራሱ መኖሪያ ቤት፣ በሜዳ ቀና ወረዳ በሚሊሺያ ዘርፍ አባላት ተደብድቦ በአምቦ ሆስፒታልና በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሲረዳ ቆይቶ በ8/8/2002 ዓ.ም በሆስፒታል ሕይወቱ አልፎ በ11/8/2002 ዓ.ም እንደተቀበረ ተገልጿል::

በተጨማሪም ኢህአዴግ የምርጫ ዘመቻውን ስራ 1ለ5 በማቀናጀት መራጩ ሕዝብ ላይ ዝርዝር መረጃ መሰብሰብና እያንዳንዱ መራጭ ኢህአዴግን ለመምረጥ መስማማቱ እንዲያረጋግጥ

የሚያደርግ ወከባ በአስቸኳይ እንዲቆምና የምርጫው ምስጢራዊነት እንዲረጋገጥ ሲሉ አመራሮቹ አስታውቀዋል፡፡

ከመግለጫውም በኋላ ለመድረክ አመራሮች ከጋዜጠኞች የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ምላሽ የሰጡ ሲሆን ስለአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ስላላቸው አስተያየት ለተነሳው ጥያቄ ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ሲመልሱ «የአሁኑ የአውሮፓ ሕብረት ልዑክ በሂልተንና ትልልቅ ሆቴሎች እየተስተናገዱ እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ ተልዕኳቸው ምን እንደሆነ አላወቅም፡፡ እስከአሁን በጉዳዩ ላይ ያነጋገሩን ነገር የለም፡፡ ለ43 ሺህ የምርጫ ጣቢያ 150 ታዛቢ፤ በውቂያኖስ ላይ እንደምታርፍ የውኃ ጠብታ ነው፡፡ ስለዚህ በእነሱ አካባቢ ብዙ መፍትሔ እንደማናገኝ አውቀን ነው የምንቀሳቀሰው፡፡ ተስፋችን የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

*<u>ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ</u>* ፡-

# 174 ሰዎች በትራፊክ አደጋ ህይወታቸው አልፏል

በሰናይት ግርማ

ባሳለፍነው ግማሽ ዓመት በአዲስ አበባ ትራፊክ አደጋ 174 ሰዎች ህይወታቸውን ሲያጡ 14,449,033 ብር የሚገመት ንብረት ደግሞ መውደሙን የትራፊክ ፖሊስ ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት ዋና ሳጅን አሰፋ መዝገቡ ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡

በዚህ ግማሽ አመት ውስጥ 174 ሰዎች መሞታቸውን ገልፀዋል፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ በአሳለፍነው ስድስት ወር ውስጥ 350 ሰዎች ላይ ከባድ የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸው ዋና ሳጅን አሰፋ ገልፀዋል፡፡ ይህ አደጋ ከባለፈው አመት ጋር ሲነፃፀር በሰው ላይ የደረሰው ጉዳት መቀነስ እንዳሳየ ጠቁመዋል፡፡

በደንብ ቁጥር 27/2002 ከታህሳስ ወር ጀምሮ ተግባራዊ የሆነው የትራፊክ ሕግ ከወጣ በኋላ አሽከርካሪዎች የመከሰስ ቁጥራቸው መጨመሩን ተገልጿል፡፡ በዚህም የተነሳ የትራፊክ ፖሊሶች ያደረጉትን ቁጥጥር የሚያሳይ ተግባር ነው ብለዋል፡፡ በመጨረሻም በአደጋው እየተጐዳ ያለው እግረኛው ስለሆነ የወጣውን ሕግ ተግባራዊ በማድረግ የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ጠቁመዋል፡፡

# ለአድማ ብተና እየተደረገ ያለው የአስለቃሽ ጭስ ልምምድ ቅሬታ አስነሳ

**«ሕዝቡን የሚጐዳ መሆኑ ከተረጋገጠ ለማስተካከል ዝግጁ ነን»**

ኮማንደር ፍቅሬ ወ/ገብርኤል

በፌዴራል የፖለስ ኮሚሽን የልዩ ልዩ ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ሆኖ እያገለገለ የሚገኘው የኮልፌ ልኳንዳ ሰፈር በስሩ ያሉትን ፖሊሶች ለአድማ ብተና የሚያገለግለውን የአስለቃሽ ጭስ ልምምድ ሲያደርግ የሚለቀቀው ጭስ ጤናችንንና ማህበራዊ እንቅስቃሴያችንን እያወከ ነው ሲሉ የአካባቢው ነዋሪዎች ቅሬታቸውን ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በአካባቢው የነዋሪው ቁጥር ከፍተኛ መሆን እና በማሰልጠኛው አጠገብ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መኖሩ ችግሩን የከፋ ሊያደርገው መጫሉን በስፍራው በመገኘት ያነጋገርናቸው ታዛቢዎች ገልጸዋል፡፡

በጉዳዩ ላይ ያነጋገርናቸው የፌዴራል ፖሊስ ዋና ዳይሬክተር ስታፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑት ኮማንደር ፍቅሬ ወ/ገብርኤል እስካሁን ከሕብረተሰቡ የተነሳ ምንም ጥያቄ እንዳሌለ ገልፀው ምርጫውን በሰላም እንዲጠናቀቅ ለማድረግ የተደረገ ልምምድ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ኮማንደሩ አያይዘውም ጥያቄው ከቀረበና ሕዝቡን የሚጐዳ መሆኑ ከተረጋገጠ ግን የሚገባንውን ምርመራ አድርገን ለማስተካከል ዝግጁ ነን ብለዋል፡፡

# ከ205 ሚሊዮን ብር በላይ የመዘበሩ ተፈረደባቸው

በኤልያስ ገብሩ

የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 1ኛ ወንጀል ችሎት ከትላንት በስቲያበዋለው ችሎት ክስ በእነ አቶ በኃይሉ ለሚ የክስ መዝገብ ተመስርቶባቸው ጉዳያቸውን ይከታተሉ የነበሩት ሰባት ተከሳሾች ላይ እስከ 11 ዓመት ፅኑ እስራትና የ20 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጫ ድረስ ወሰነ፡፡

በፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ ከሳሽነት በወ/ጠ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 119/3/ መሠረት ተሻሽሎ በቀረበው በ1ኛ ክስ ሁለም ተከሳሾች በ1997 ዓ.ም የመጣውን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32 (1) (ሀ)፣ 33 እና 407 (1) (ሀ) (ሐ) 2 እና 3 ሥር የተደነገገውን መተላለፋቸው ተጠቅሷል፡፡

የወንጀል ዝርዝሩ እንደሚያስረዳው ከሆነ 2ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛና 5ኛ ተከሳሾች እንደቅደም ተከተላቸው በየካ ክፍለ ከተማ የማሕበራት ቡድን መሪ፣ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የሊዝ አፈፃፀም ክለርክ፣ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ የማሕበራት ማደራጃ መስተንግዶ ሰራተኛ ሆነው ይሰሩ ነበር፡፡

በዚህ ወቅት የተሰጣቸውን የስልጣን ችሎታ ከመጠን በላይ አሳልፈው በመገልገል እንዲሁም 1ኛ ተከሳሽ ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦታና ቤት አስተዳደር መምሪያ ቴክኒሽያን ሆኖ በሚጠራበት ጊዜ በሥራው አጋጣሚ ምስጢር በመጠቀም ሕገ ወጥ የሆነ ጥቅም ለግላቸው ለማግኘት፣ ለሌሎች ለማስገኘትና በመንግስት እና በሕዝብ ጥቅም ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ለማድረስ አስበው ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር ተመሳጥረው ከሙያ ጋር የተገናኙ የተለያዩ ሕገወጥ ተግባራትን መፈፀማቸው ተገልጿል፡፡

1ኛ ተከሳሽም ከ1998 ዓ.ም 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ራሱን እንደመንግስት ሰራተኛ ኃላፊ በማስመሰል ቀደም ሲል በ1981 ዓ.ም የተደራጀ ማህበር አለኝ በማለት «ቦጋለ» የመኖሪያ ቤት የሕብረት ሥራ ማሕበር (220 አባላት ያሉት) እና «ሾላ» የመኖሪያ ቤት የሕብረት ሥራ ማሕበር (248 አባላት ያለት) ከ1981 ዓ.ም ጀምሮ በሕጋዊ መንገድ ተደራጅተው ቦታ ያገኙ በማስመሰል ሃሰተኛ ሰነዶችን ከሌሎች ተከሳሾች ጋር አዘጋጅቷል፡፡

በዚህም በመገልገል ቀደም ሲል የነበሩ መስሪያ ቤቶችን ስም በመጥቀስ ማሕበሩ ቦታ እንዲያገኙ የፈቀዱ ለማስመሰል ሀሰተኛ ደብዳቤዎችን፣ የኃላፊዎች ፊርማን፣ የመ/ቤቶችን ማህተም እና ሣይት ፐላን በማዘጋጀት የተለያዩ ሕገ ወጥ ተግባራትን በመፈፀም በአጠቃላይ ሁሉም ተከሳሾች በወንጀሉ ሥራ እና በሚሰጠው ውጤትም ሙሉ ተካፋይ በመሆን የሊዝ ግምቱ

ብር 205,540,905.00 የሚያወጣ የመንግስት መሬት ለራሳቸው እና ለግለሰቦች በሕገወጥ መንገድ እንዲያገኙ በማድረግና በሕዝብና በመንግስት ላይ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረሳቸው በማስረጃ መረጋገጡ ተገልጿል፡፡

በዚህም መሠረት 1ኛ ተከሳሽ በ11 ዓመት ፅኑ እስራትና 20 ሺህ ብር፣ 2ኛ ተከሳሽ በሁለት ክስ 15 ዓመት ፅኑ እስራትና 20 ሺህ ብር፣ 3ኛ ተከሳሽ በአምስት ዓመት ፅኑ እስራትና አንድ ሺህ ብር፣ 6ኛ ተከሳሽ 5 ዓመት ፅኑ እስራትና 5 ሺህ ብር፣ ከ7ኛ - 9ኛ ያሉ ተከሳሾች በሌሉበት በሁለት ዓመት ጽኑ እስራትና 500 ብር የገንዘብ መቀጫ ተወስኖባቸዋል፡፡

## «የሙዚቃው ንጉስ» ኃውልት ዛሬ ይመረቃል

### 10 ልጆቹ ቅሬታቸውን አቀረቡ

በሰናይት ግርማ

ከዓመት በፊት የክርስትና ኃይማኖት ተከታዮች የትንሳኤን በዓል የሚያከብሩበት ቀን ነበር - የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያስደነግጥ መርዶ የተሰማው፤ የክቡር ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ዜና እረፍት፡፡

በመድረክ ሥራዎቹ አልቅሶ የሚያስለቅሰው፤ ፈንድቆ የሚያስፈነድቀው፤ የአበሻ የሙዚቃ ንጉስ ሞት ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ ከባድ ሀዘኑን በቀብር ስነ-ስርዓቱ ላይ አሳይቷል፡፡

ሚያዚያ 11 ቀን 2001 ዓ.ም የዕረፍት ዜና ከተሰማ ከአምስት ቀን በኋላ (የዛሬ ዓመት) ነበር የቀብር ስነ ስርዓቱ የተፈፀመው፡፡ የክቡር ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ባለቤት ወ/ሮ ሮማን በዙ እና የዝግጅቱ አስተባባሪ ኮሚቴ ለአንደኛ ሙት ዓመት መታሰቢያው ዝግጅት መሳካት ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረጉ ነው፡፡ በክቡር ዘበኛ የሙዚቃ ክፍል ውስጥ ለረዥም ጊዜያት አብረውት ይሰሩ ከነበሩት የቅርብ ጓደኞቹ መሀከል አንዱ የሆነው አርቲስት ተስፋዬ በቀለ /ሽልንጌ/ በዚህ በዓል ላይ የክቡር ዘበኛ የተወሰኑ አባላት በኦርኬስትራ ክፍል፣ በቲያትር ክፍል፣ በሰልጣኝ የሙዚቃ ማርሽ ቡድን በዝግጅቶች ላይ እንዲገኙ ጥሪ እንደተደረገላቸው ገልጿል፡፡

በዝግጅቱ መርሀ ግብር መሰረት በአዲስ አበባ ስታዲም ሊካሄድ ታስቦ የነበረው የሙዚቃ ኮንሰርት በአየር ትንበያ መሰረት ዝናብ ሊሆን ይችላል በመባሉ ወደ ሚሊኒየም አዳራሽ በመዛወር ትናንት በዚያ ተካሂዷል፡፡ አድናቂዎቹ እና የሚወደው ሕዝብ ካለ ክፍያ በመታደም ለአርቲስቱ ያላቸውን ፍቅር እና ክብር ገልጸዋል፡፡

በዚህ ኮንሰርት ላይ የተለያዩ ታዋቂ አርቲስቶች ስራቸውን ያቀረቡ ሲሆን ለኮንሰርቱ መሳካት የኢትዮጵያ ሙዚቀኞች ማሕበር የተለያዩ ድጋፎችን እንዳደረገላቸው ተጠቁሟል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዛሬ የአርቲስቱን የአንደኛ ሙት ዓመት መታሰቢያ ቀንን ምክንያት በማድረግ በቅድስት ስላሤ ካቴድራል ቤተክርስቲያን የኃውልት ምርቃት እና የፀሎት ሥነ-ስርዓት እንደሚከናወንና ከቤተክርስቲያን መልስ በመኖሪያ ቤቱ የተዘጋጀ ፀበል ፀዲቅ እንደሚኖር ተገልጿል፡፡ በመቀጠልም ዛሬ ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በክቡር ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ስም የልብስና የፎቶ አውደ ርዕይ እንደሚከፈት ተገልጿል፡፡ በአውደ ርዕዩ ላይ በመድረክ

ሲዘፍን የተነሳቸው ፎቶዎች፤ በህይወት እያለ ለህዝብ ያበረከታቸው ስራዎች በሸክላ፣ በሲዲ እንዲሁም በካሴት ይቀርባሉ:: በህይወቱ ዙሪያ የሚያጠነጥነው መጽሐፍ በኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር አዘጋጅነት ለምረቃ እንደሚበቃም ይጠበቃል:: በመጽሐፉ ላይ ህዝቡ የማያውቃቸው የተደበቁ ታሪኮች ይወጣሉ ተብሎም ይገመታል::

በነገው እለት በመሿለኪያ (አራተኛ ክፍለ ጦር አጠገብ) የኮከብ ቅርፅ ያለው መንገድ በክብር ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ስም እንደሚሰየም እና ከአዲስ አበባ አስተዳደር ጋር የርክክብ ስነ-ስርዓት እንደሚደረግ ተገልጿል::

ከዚህ ጋር በተያያዘ የክብር ዶ/ር አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ አስር ልጆች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት ደብዳቤ ላይ እንደገለፁት የአርቲስቱን ታሪክ በያዘው መጽሐፍ ላይ እኛ ልጆቹ፣ የቅርብ ወዳጆቹና ጓደኞቹም ሊመለከቱት እና ሃሳባቸውን ሊሰጡበት ሲገባ ወ/ሮ ሮማን በዙ (ባለቤቱ) በፈለጉት መንገድ እና በሚስማማቸው ሁኔታ እንዲቀርብ አድርገውታል ሲሉ ቅሬታቸውን ገልፀዋል:: በተጨማሪም በሃውልቱ ስራ ላይ እኛ ልጆቹ እንዳንሳተፍ አድርገዋል በማለት ያላቸውን ቅሬታ አሰምተዋል::

## ፊቸር

# የኢትዮጵያ ፖለቲካና የዳያስፖራው ሚና

**በዳዊት ከበደ**

በሰሜን አሜሪካ በ«አናንዳሊ-ቨርጂኒያ» ነዋሪ የሆነው ኤልያስ ክፍሌ በቀን ውስጥ ከ16 ሰዓታት በላይ የሚሆነውን ጊዜ በ«ላፕቶፑ» ላይ ተጠምዶ ይሳልፋል:: ዋነኛ ትኩረቱ የምስራቅ አፍሪካ ጂኦ-ፖለቲካዊ ክዋኔዎችን የተመለከቱ አዳዲስ መረጃዎችና ዜናዎችን እያሳደደ ከድረ-ገፁ አቋም ጋር በማጣጣም ኦዲዮቪዥዋል መረጃዎች፣ ዘገባዎች፣ ቃለ-ምልልሶችና ዜናዎችን በመላው ዓለም ለሚገኙ የድረ-ገጹ አንባቢያን ያቀርባል:: የድረ-ገጽ ጎብኚዎችን በዲጂታል መለኪያ እየተቆጣጠረ የሚያወዳድረው www.alexa.com ይፋ ባደረገው ዓመታዊ የድረ-ገጾች የደረጃ ሰንጠረዥ መሰረት የኤልያስ ድረ-ገጽ የሆነው ethiopianreview.com በጎብኚዎች ብዛት ከኢትዮጵያ ድረ-ገጾች በአንደኛ ደረጃ ላይ ሲገኝ ከአፍሪካ ደግሞ 55ኛ እንደሆነ ተጠቅሷል::

በብዙዎች ዘንድ አወዛጋቢ የፖለቲካ አቋም እንዳለው የሚነገርለትና በኢህአዴግ ደጋፊዎች ዘንድ «ጋዜጠኝነትንና ፖለቲካን አጣምሮ የሚያራመድ» የሚል ትችት የሚሰነዘርበት ኤልያስ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የሰላ ትችት ከመሰንዘር አልፎ «አገዛዙ በማናቸውም መንገድ ከስልጣን መወገድ አለበት» የሚል አቋም ያራምዳል:: «እንደ ነጻ ጋዜጠኛ ማሰብ ያለብን አገራችንን ነጻ አውጥተን ዴሞክራሲያዊ መንግስት ሲቋቋም ብቻ ነው ሲል ይከራከራል:: ይህ ግቡን እንዲመታ ደግሞ ከፀሐይ በታች ከማንም ወገን ጋር መደራደር የግድ አስፈላጊ ነው ይላል:: በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ ሁለት ጊዜ አስመራ ተመላልሷል:: አቶ ኢሣያስ አፈወርቂን «ኢትዮጵያዊያን ለነፃነት በምናደርገው ትግል ከጎናችን የመቆም የሞራል ግዴታ አለብህ» ብሏቸዋል:: አቶ ኢሳያስም በሀሳቡ እንደተስማሙ ለድረ-ገጹ በሰጡት ቃለ-ምልልስ ላይ

አረጋግጠዋል፡፡ ባለፈው ዓመት በ ethiopianreview.com ድረ-ገጽ የዓመቱ ሰው (person of the year) ተብለው የተመረጡት አቶ ኢሳያስ ነበሩ፡፡ ዘንድሮም ድረ-ገጹ የመረጠው የአቶ ኢሳያስ ቃል-አቀባይ (ማስታወቂያ ሚኒስትር) የሆኑት አቶ ዓሊ አብዶን ነው፡፡

የኤልያስ አይነት አቋም ያላቸው የኢትዮ-ዲያስፖራ አባላት በርካታ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለዘብተኛ አቋም ያላቸውና ሰላማዊ ትግል ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ ለሁሉም ችግሮቻችን መፍትሔ ነው ብለው የሚያምኑም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም፡፡ የኢትዮ-ሚዲያ ኤዲተር የሆነው የሲያትሉ አብርሀ በላይ ሰላማዊ ትግልን ለሚከተሉ ተቃዋሚዎች ሽፋን ይሰጣል፡፡ ኢትዮ ሚዲያ ፎረም ሰላማዊ ትግል ለሚያራምዱም ሆነ ሰላማዊ ትግል አብቅቶለታል ለሚሉ ወገኖች እኩል ሽፋን ይሰጣል፡፡ የዳያስፖራውን ባቡር በመዘወር በኩል ከድረ-ገጾችና ብሎጎች ሌላ ፓልቶክ ሩሞች እና ሬዲዮ ጣቢያዎችም ያላቸው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ከሬዲዮ ጣቢያዎቹ መካከል የአበበ በለው አዲስ ድምጽ፣ ከፓልቶክ ሩሞች የኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች መወያያ መድረክ (ECADF) ለዚህ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በውጭ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ አባል እነዚህ ሚዲያዎች ለማናቸውም የአገር ቤት ጉዳይ የመጀመርያ የዜና ምንጮች ናቸው፡፡ ኢትዮ-ሚዲያ ባለፈው ሰኞ መድረክ በዲያስፖራ ከፍተኛ ድጋፍ እያገኘ ነው በማለት በሲያትልና ዋሽንግተን ለተደረጉ የመድረክ ስብሰባዎች ሰፊ ሽፋን ሰጥቷል፡፡ ኢትዮ-ሚዲያ እንደዘገበው «ከወ/ሪት ብርቱካን መታሰር ወዲህ ይህን ያህል ቁጥር ያለው ማሕበረሰብ ሲገኝ የመድረክ ስብሰባ የመጀመሪያው ነው» ብሏል፡፡

## አነስተኛ ቁጥር ግን ደግሞ ተጽዕኖ ፈጣሪ

ዶ/ር አክሊሉ ኃ/ስላሴ «በኢትዮጵያ ፖለቲካ ተሳታፊ የሚሆኑ ፓርቲዎች ውጤታማ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የዳያስፖራ ድጋፍ ሊኖራቸው ግድ ነው» ይላሉ፡፡ በ1997 ዓ.ም ምርጫ ዳያስፖራው በመጀመሪያ ድጋፉን የሰጠው ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኀይሎች ሕብረት ነበር፡፡ እንደሚታወቀው ሕብረቱ መሠረታቸውን በውጭ አገር ያደረጉ ተቃዋሚዎችን በማሰባሰብ የምስረታ ጉባኤውን በዋሽንግተን ዲሲ ነበር ያካሄደው፡፡ ለዚህም ነው በ1997 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ቅንጅት ሲመሠረት ዳያስፖራው በጥርጣሬ የተመለከተው፡፡ ሆኖም በወቅቱ በቴሌቪዥን ክርክሩ ላይ ተቃዋሚዎች የነበራቸውን አንፃራዊ ነፃነት በመጠቀም በቴሌቪዥን ክርክሩ ቅንጅት የበላይነት ሲያሳይ በውጭ ያለው ማሕበረሰብ ለቅንጅት አዎንታዊ ምላሽ መስጠት ጀመረ፡፡ «በተለይ በ1997 ዓ.ም መጋቢት ወር ወደ ሰሜን አሜሪካ ያቀኑት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የቅንጅቱ እንቅስቃሴና ዓላማ ለውጭ ማሕበረሰብ በማሳመናቸው ቅንጅት ከፍተኛ ድጋፍ ሊጎርፍለት ችሏል» ይላሉ ዶ/ር አክሊሉ በጥናታቸው፡፡

በ1998 ዓ.ም መጀመሪያ የሰሜን አሜሪካ የሕብረት አመራር በእነ ዶ/ር መረራና ዶ/ር በየነ የሚመራው የአገር ውስጥ አመራር «ፓርላማ መግባት የለበትም» የሚል ውሳኔ ሲያሳልፍ አዲስ አበባ የነበሩ አመራሮች ግን ውሳኔውን ውድቅ በማድረግ ፓርላማ መግባታቸው በዲያስፖራው ዘንድ ከባድ ቁጣ ቀሰቀሰ፡፡ ይህንኑ ተከትሎ ከዳያስፖራ ማህበረሰብ ይደረግለት

የነበረው ድጋፍ በመቋረጡ የአገር ውስጡ የሕብረት አመራር የቢሮ ኪራይና ተያያዥ ወጪዎችን መክፈል የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር የዶ/ር አክሊሉ ጥናት አመልክቷል::

«የዳያስፖራ ተጽዕኖ የመፍጠር አቅም የሚገነዘቡት ተቃዋሚዎች ብቻ አይደሉም» የሚሉት ዶ/ር አክሊሉ ገዢው ፓርቲ ካደረጋቸው እንቅስቃሴዎችም የሚከተለውን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ:: «በ1993 ዓ.ም በሕወኃት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት መካከል የተፈጠረውን መከፋፈል ተከትሎ ቡድኖቹ ያደረጉት ግንባር ቀደሙ ተግባር ሁለቱም የየራሳቸውን ተወካዮች ወደ ሰሜን አሜሪካና አውሮፓ በመላክ እዛ የሚገኙ የትግራይ ተወላጆችን ለማሳመን ያደረጉት ጥረት ተጠቃሽ ነው» ይላሉ::

በ1999 ዓ.ም እስር ቤት ውስጥ የነበሩ የቅንጅት አመራሮች ለሁለት እንዲከፈሉ መንስኤ የነበረው ሰሜን አሜሪካ በነበረው የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር (Kinjit International Leadership) ውስጥ የተፈጠረው አለመግባባት ነው:: አስራ አንድ አባላት የነበሩትና የመኢአድ አባል በሆኑት ሻለቃ ዮሴፍ ያዘው ይመራ የነበረው ይኸው አመራር የቀስተደመና አባላት የሆኑትን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ አቶ ብርሃነ መዋና አቶ ዳዊት ከበደን ከአመራር አባልነት እንዲሰናበቱ በማድረጉ ክፍፍሉ እንደተፈጠረ በሬዲዮ ይፋ ተደረገ:: ይህ በሆነ በጥቂት ቀናት ውስጥ ግን የሰሜን አሜሪካው ክፍፍል ወደ ቃሊቲ ተዛመተ፤ እስር ቤት የነበሩ አንዳንድ የመኢአድና የቀስተደመና አመራር አባላት ልዩነታቸውን በይፋ መግለጽ ጀመሩ:: አንድ የቅንጅት ስራ አስፈጻሚ አባል በወቅቱ ለዚህ ፊቸር ጸሐፊ (እስር ቤት ውስጥ) የሰጠው አስተያየትም ይኸው ነበር ::«በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ በጎም ሆነ መጥፎ ክስተት መነሻው ዳያስፖራ ነው:: ይህ ክፍፍል መነሻው ዳያስፖራ እስከሆነ ድረስ እዚህ ባለው አመራር መፍትሔ አያገኝም»

እንደሚታወቀው የቅንጅት አመራሮች ከእስር እንደተፈቱ የመጀመርያ ጥቂት ሳምንታት ውስጥ በተለያየ ቡድን ውስጥ ተከፋፍለው ወደ ሰሜን አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ ደቡብ አፍሪካና ካናዳ በማቅናት ከኢትዮ-ዳያስፖራዎች ጋር መወያየት ነው:: በአመራሮቹ መካከል የተፈጠረው መከፋፈል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ የተደረገውም በሰሜን አሜሪካ ዋሽንግተን ዲ.ሲ. ነበር::

ዮሲ ሻይን እና ታማራ ኮፍማን ዊትስ የተባሉ ፀሐፊዎች እንደሚያስቀምጡት የዳያስፖራ አባላት በአገር ውስጥ ፖለቲካ ያላቸው ሚና እጅግ የሰፋ ነው:: የውጭ ምንዛሬ በማስገባት፣ ጠንካራና ተቀናቃኝ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በማጠናከር እንዲሁም በተለያዩ የሲቪክና የእርዳታ ተቋማት አማካኝነት የአገራቸውን ፖለቲካ የማሽከርከር አቅማቸው ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል:: ዮሲ ሻይን ለዚህ መከራከሪያው የሚከተለውን ምሳሌ ጠቅሷል::

እ.ኤ.አ በ1991 በታላቁ ጆርጅ ቡሽ የሚመራው የአሜሪካ አስተዳደር ለእስራኤል ሊሰጥ የታሰበውን ብድር ለመስጠት አንድ ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል:: ያ ቅድመ ሁኔታ በእስራኤል ይዞታ ስር የነበሩ የፍልስጤም ከተሞች ዌስት ባንክ እና ጋዛ ላይ የሰፈራ ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት እንዳይውል የሚል ነበር:: በአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት እና በሌሎች ታላላቅ ተቋማት በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ የሚያገለግሉ አባላትን ያቀፈው «አይሁድ-አሜሪካዊያን አድቮኬሲ ቡድን» ግን ተቃውሞውን አሰማ:: ይህ አይነቱ ድጋፍ በቅድመ ሁኔታ መቀመጥ እንደሌለበትና እርዳታው ከተሰጠ በኋላ ከአገራችን መንግስት ጋር ተወያይተን የፍልስጤማዊያን ወንድሞቻችንን ጥቅም የሚያስጠብቅ ሕግ እንዲፀድቅ እንስማማለን በማለት እርዳታውን አስለቀቁ::

በአሜሪካ የሚገኘው «Jewish-American lobbying organization » ለዘመናት ከሚከራከርባቸው አጀንዳዎች አንዱ የእስራኤል ርዕሰ ከተማ ከቴላቪቭ ወደ እየሩሳሌም እንዲቀየር በማድረግ ላይ ነው:: በአሜሪካ የሚገኙ አርመን አሜሪካዊያን የአዘርባጃን መንግስት የዜጎቹን መብትና ነፃነት እያፈነ ነው:: በማለት አገዛዙ ከአሜሪካ ምንም አይነት እርዳታ እንዳያገኝ የሚያደርግ ሕግ በኮንግረስ እንዲፀድቅ አድርገዋል::

በዮሲ ሻይን ጥናት ውስጥ ከተካተቱ አገሮች መካከል ኢትዮ-ዳያስፖራዎች ይገኙበታል:: ሻይን እንዳለው በኢትዮጵያና ኤርትራ የድንበር ጦርነት ወቅት የኤርትራ ዳያስፖራዎች ለጦር መሣሪያ መግዣ የሚውል መጠነ ሰፊ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ለአገራቸው መንግስት አስረክበዋል:: ኢትዮጵያውያንም በተመሣሣይ መልኩ ሰፊ እንቅስቃሴ ቢያደርጉም በውጭ የነበሩ የኤርትራ ዳያስፖራ አባላት ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጋር ሲነፃፀር ግን የኢትዮጵያዊያን ተሳትፎ አነስተኛ ነበር ሲል ሻይን በጥናቱ ላይ ገልጿል::

የኤርትራ መንግስት በአገር ውስጥ የፕሬስ ነፃነት፣ የመደራጀት መብት፣ የሲቪክ ማህበራት እንቅስቃሴን አይፈቅድም:: ከሪፈረንደም ወዲህ በዛች አገር ምርጫ ተደርጎ አያውቅም:: በዚህ የተነሳ ዜጎች በአስፈሪና አስቸጋሪ ሁኔታ በድንበር በኩል እያቋረጡ ወደ ጎረቤት አገር ይሸሻሉ:: ይህ የአቶ ኢሣያስ ተግባር በውጭ አገር በሚገኙ ዜጎቹ ከፍተኛ ተቃውሞ እንዲቀሰቀስ አድርጓል:: ሆኖም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከሦስት ወራት በፊት ኤርትራ ላይ ማዕቀብ ሲጥል ኤርትራዊያኑ የፖለቲካ አቋማቸውን ወደ ጎን በማድረግ ከአቶ ኢሣያስ ጎን ተሰልፈው በመላው ዓለም የተቀናጀ የተቃውሞ ሰልፍ አካሄዱ::

አንዳንድ ተንታኞች የኤርትራና የኢትዮጵያ ዳያስፖራዎችን በማነጻጸር እንደሚሉት የፖለቲካ ልዩነትን ወደ ጎን አድርጎ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ከኢህአዴግ ጋር መተባበር ለኢትዮጵያኑ የማይታሰብ ነው:: በተለይ ውጭ ያለውን ኢትዮጵያዊ በማስተባበር በኩል የጎላ ድርሻ ከነበራቸው የማሕበረሰቡ አባላት መካከል ከ20 በላይ የሚሆኑት በ1997 ምርጫ ማግስት ከቅንጅት አመራሮች ጋር በሌሉበት ክስ እንዲመሰረትባቸው መደረጉ በኢህአዴግና በእነሱ መካከል ያለው ጥላቻ እንዲከር ምክንያት ሆኗል::

በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቁጥራቸው ከሦስት ሚሊዮን ይበልጣል የሚለው ኤሊያስ ክፍሌ «በእኔ ግምት ከዚህ ውስጥ የአገራቸውን ፖለቲካ በንቃት የሚከታተሉት ቁጠራቸው ከ10 በመቶ አይበልጥም:: ሆኖም እነዚህ ኢትዮጵያውያን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በአገር ውስጥ ፖለቲካ ተፅዕኖ የማሳደር አቅማቸው በጣም ከፍተኛ ነው» ሲል አስተያየቱን ለአውራምባ ታይምስ ሰጥቷል::

የ1997 ዓ.ም ምርጫ በዓለም አቀፍ ማሕበረሰብ ዘንድ ትኩረት እንዲሰጠው በማድረግ በኩል የኢትዮ-ዳያስፖራ ተሳትፎ የላቀ ነበር:: በተለይ ምርጫውን ተከትሎ በተፈጠረው ውዝግብ ምክንያት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች፣ ጋዜኞችና የሲቪክ ማሕበራት መሪዎች ሲታሠሩ በኢትዮ-ዳያስፖራ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ታላቅ ትዕይንተ ሕዝብ በህዳር 1998 ዓ.ም አጋማሽ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ተካሄደ:: ኢትዮጵያውያኑ የተለያዩ መፈክሮችን በማንገብ ከኋይት ኃውስ እስከ ኮንግረስ (ካፒቶል ሂል) ድረስ በእግራቸው በመጓዝ ተቃውሞአቸውን አሰሙ:: በዕለቱ

የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ባልደረባ የሆነው ጋዜጠኛ አዲሱ አበበ «ይህን ያህል ቁጥር ያለው ኢትዮጵያዊ የተሳተፈበት ትዕይንተ ሕዝብ በአሜሪካ ቆይታዬ አጋጥሞኝ አያውቅም» ካለ በኋላ ከፖሊስ አባላት አገኘሁት ባለው መረጃ መሰረት ሰላማዊ ሰልፍ የወጣው ሕዝብ ቁጥር ወደ 10,000 የሚጠጋ እንደሆነ ገለፀ፡፡

ኢትዮጵያውያኑ በዚህ ትዕይንተ ሕዝብ ብቻ አልተገቱም፡፡ ተከታታይ የርሃብ አድማ፣ የሻማ ማብራት ስነ-ስርዓት፣ የተለያዩ የተቀውሞ ሰልፎች አደረጉ፡፡ የወቅቱ ፕሬዝዳንት ጆርጅ ደብሊው ቡሽ ለእረፍት ቴክሳስ በሚገኘው የግል መኖሪያ ቤታቸው በተገኙበት በአንድ እሁድ ቀን ሳይቀር ኢትዮጵያውያኑ ወደ ስፍራው በማቅናት ጥያቄያቸውን ለፕሬዝዳንቱ እስከማቅረብ ደርሰው ነበር፡፡

ኢህአዴግ ውጭ ያለውን ማሕበረሰብ አውሬ አድርጎ ነው የሚስለው የሚለው አርቲስት ታማኝ በየነ «ውጭ ያለነው ህልማችን ኢትዮጵያ ሰላማዊና የሁላችንም አገር እንድትሆን መፈለግ ነው፡፡ ዋናው ነጥብ እኛ የምንኖረው ውጪ ነው የባሕላችን ቋንቋችን የልምዳችን ቦታ አይደለም ሆኖም ግን ሰው ሊያገኘው የሚገባውን መብት አግኝተን ነው የምንኖረው፡፡ ይህን መብት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ወገን በአገሩ ለምን አያገኝም?» ሲል በታህስስ ወር አጋማሽ ከአውራምባ ታይምስ ጋር ባካሄደው ቃለ-ምልልስ አስተያየቱን ሰጥቶ ነበር፡፡

## ዳያስፖራውና መድረክ

አቶ ያሬድ ጥበቡ ለ23 ዓመታት በአሜሪካ ኖረዋል፡፡ በውጭ ያለው ማሕበረሰብ የፖለቲካ ተሳትፎን አስመልክቶ ሲናገሩ «ከአገር ቤቱ ሁኔታ ጋር አብሮ ከፍና ዝቅ የሚል ነው» ይላሉ፡፡ በ1997 ዓ.ም ቅንጅት በዳያስፖራው ማሕበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍ እንደነበረው የሚያስታውሱት አቶ ያሬድ «በአመራሮች መካከል የተፈጠረው መከፋፈል ግን የበርካታዎቹን ተስፋ አጨናግፏል» ይላሉ፡፡ ከቅንጅት መከፋፈል በኋላ ዳያስፖራ ውስጥ በተቃውሞ ጎራ ሁለት አይነት ፅንፍ ተፈጥሯል፡፡ አንዱ «ኢህአዴግ በማናቸውም መንገድ ሊወርድ ይገባል» የሚል አቋም ያላቸውን ተቃዋሚዎች የሚደግፍ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከወ/ሪት ብርቱካን መታሰር በኋላ «የእሷ ራዕይ እውን ሊሆን ይገባል» በሚል ለአንድነት ብሎም የስምንት ፓርቲዎች ስብስብ እንደሆነ የተነገረለትን «መድረክ» የሚደግፈው ቁጥሩ ቀላል የማይባል ነው፡፡ አቶ ያሬድ ጥበቡም በዚህ ይስማማሉ፡፡ መድረክ በያዘው አካሄድ ከቀጠለና የቅንጅት አይነት ዕጣ ካልገጠመው የዳያስፖራውን ድጋፍ ለማግኘት እንደሚችል ግምታቸውን ቢሰጡም «ከአንድነት በፀረ-ዴሞክራሲ እርምጃ የተገለሉት እንዲሳተፉ ቢደረግ በዳያስፖራው ዘንድ የመድረክ ተሰሚነትን ያጠናክረዋል፡፡ እነ ፕሮፌሰር መስፍንን የዳር ተመልካች አድርጎ ለመሄድ የሚደረገው ሙከራ ግን ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል» ይላሉ፡፡

አንዳንድ ወገኖች ደጋግመው የሚያነሱት ጥያቄ አለ፡፡ «የመድረክ አመራሮች የሚወዳደሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፡፡ ይመርጠናል የሚሉት ህዝብም ያለው በአገር ውስጥ ነው፡፡» በማለት «ወደ ውጭ የሄዱበት ዋነኛ ምክንያት ገንዘብ ለመሰብሰብ ነው» ሲሉ ይተቻሉ፡፡ ሆኖም የዳያስፖራ ድጋፍ ካልታከለበት ውጤታማ እንደማይሆኑና ዳያስፖራው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ያለውን ሚና በግልፅ ለመረዳት የመድረክ አመራሮች ጉብኝት በራሱ ቀላል ምሳሌ

እንደሆነ ተንታኞች ይስማማሉ፡፡ የመድረክ አመራሮች ግን እንደ ቀድሞ ቅንጅት የዳያስፖራውን ቀልብ በመሳብ በኩል ውጤታማ እንዳልሆኑ አንዳንዶች ጥርጣሬአቸውን ይገልጻሉ፡፡ መድረክ ከቀድሞ የአገሪቱ ፕሬዝዳንትና የህወኃት አመራሮች ጋር በመሆን ትልቅ ውጤት እንደሚያስመዘግብ በየመድረኩ በልበ ሙሉነት ቢገልጽም በውጭ ያለው ማሕበረሰብ ግን መድረክ ከእነዚህ የቀድሞ ቱባ ባለስልጣናት ጋር መጣመሩ በአዎንታዊ ጎኑ የተመለከተው አይመስልም፡፡

የመድረክ አመራሮች በሲያትል ስብሰባቸውን ባደረጉበት ወቅት በቦታው ላይ ተገኝተው የታዘቡትን የፃፉት አቶ መክብብ ማሞ «የመድረክ አመራሮች በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ እንዲደግፋቸው ከፈለጉ ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አጥጋቢ ምላሽ መስጠት ያሻቸዋል» ይላሉ «የመድረክ አመራሮች በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ላነሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች በሲያትሉ ስብሰባ አጥጋቢ ምላሽ ሰጥተዋል ለማለት አልችልም፡፡» ያሉት አቶ መክብብ በተለይ የአንድነት አመራር ውጭ ከሚገኘው ኢትዮጵያዊ ጋር ያያያዘው ብቸኛው ቀጭን ገመድ የብርቱካን እስር ቤት መግባት ነው ይላሉ፡፡

## ዳያስፖራውና የኢትዮጵያ መንግስት

የኢትዮጵያ መንግስት የኢትዮ-ዳያስፖራ ተፅዕኖ የመፍጠር አቅም በመገንዘብ ከ1997 ምርጫ ማግስት ከማሕበረሰቡ ጋር የሚያገናኘው ድልድይ ለመገንባት አዲስ ስትራቴጂ መከተሉ ይታወቃል፡፡ በተለይ በ2000 የተከበረው የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ዋነኛ ዓላማው በውጭ የሚገኙ የኢትዮጵያ ማሕበረሰብ አባላትን ቀልብ ለመሣብ ነው ይላሉ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ውስጥ የሚሰሩ አንድ ኤክስፐርት፡፡ «የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን እና ሌሎች የመንግስት ሚዲያዎች ሚሊኒየምን አስመልክቶ ያቀርቧቸው የነበሩ የቅስቀሳ ዘጴዎችን ልብ ብሎ የተመለከተ ማንም ዜጋ የመንግስትን ትኩረት ለመገንዘብ አይቸገርም» ይላሉ እኒህ ኤክስፐርት፡፡

በ1999 ዓ.ም አጋማሽ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስር የተቋቋመው «በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጉዳይ ዳይሬክቶሬት» በርካታ እንቅስቃሴዎችን እንዳደረገ የሚገልፁት አስተያየት ሰጪዎች ኢትዮጵያዊያኑ ወደ አገር ቤት እንዲመጡ በርካታ ጥቅማጥቅሞች መመቻቸታቸውን በማስታወስ መሬት በነፃ እንዲወስዱ፣ ንብረቶቻቸውን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ ከመመቻቸቱም ባሻገር በሚሊኒየም አዳራሽ በጠ/ሚ/ር ሰብሳቢነት በመንግስት በኩል ብዙ ነገር እንደሚመቻችላቸው ቃል ተገባላቸው፡፡ ዶ/ር አክሊሉ እንደሚሉት ጥቂቶች የጥቅማጥቅሙ ተቋዳሽ ሆነው ቢመለሱም መንግስት ከጎኑ እንዲሰለፉ የሚፈልጋቸው እነዛ ዋነኛ ተቀናቃኞቹ ግን ለጥቅማጥቅም ቦታ ካለመስጠታቸውም ባሻገር «መንግስት ላቋቋመው የሚሊኒየም ሴክሬቴሪያት እውቅና አንሰጥም» በማለት በዋሽንግተን ዲሲ በአርቲስት አለምፀሐይ ወዳጆ ሰብሳቢነት በዓሉን በደማቅ ሁኔታ አክብረዋል፡፡ በዶ/ር አክሊሉ ዕምነት በ2000 ዓ.ም ወደ አገራቸው መጥተው በነፃ ያገኙትን መሬት ቸብቸበው የተመለሱት እነዚህ የዳያስፖራ አባላት ቀድሞውኑ በተቃውሞ ፖለቲካ ውስጥ ተሳትፎ ያልነበራቸው እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡

ለዚህ ፊቸር ማጠናከሪያ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ጉዳይ ዳይሬክትሬት እያደረገ ስላለው እንቅስቃሴ አንዳንድ መረጃዎችን ለማግኘት ጽህፈት ቤቱን በአካል

ተገኝተን ጥያቄ ብናቀርብም «የጽሕፈት ቤቱ ዳይሬክተር ጄነራል የሆኑት ወ/ሮ መብራት፤ በስራ ምክንያት ወደ ውጭ አገር ስለሄዱ ከእርሳቸው ፍቃድ ውጪ ሌሎች የጽሕፈት ሰራተኞች መረጃ መስጠት አይችሉም» ተብሎ ስለተገለጸልን የጽህፈት ቤቱን መረጃ በአግባቡ ማካተት አልቻልንም::

ጽህፈት ቤቱ መረጃ ሊሰጠን ፍቃደኛ ባይሆንም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ላይ የሰፈረው የጽህፈት ቤቱ ዓላማና ተግባር እንደሚያትተው የተቋሙ ዋነኛ ዓላማ በውጭ የሚገኘውን ማሕበረሰብ በአገሪቱ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የጎላ ተሳትፎ እንዲያደርግ ማበረታታት እንዲሁም ባለበት አገር መብቱና ጥቅሙ እንዲከበር በተጨማሪም ማሕበረሰቡ የአገሪቱን መልካም ገጽታ በማስተዋወቅ ድርሻውን እንዲወጣ ለማስቻል ስለ አገሩ በቂ መረጃ መስጠት ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የተለያዩ የሚኒስትር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት ጋር አገናኝ ድልድይ ሆኖ ይሰራል ይላል:: ስለ መስሪያ ቤቱ እንቅስቃሴ ለሚዲያ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ያልሆነ መስሪያ ቤት ውጭ አገር ለሚገኝ አንድ ኢትዮጵያዊ ስለአገሩ የተሟላ መረጃ ይሰጣል ማለት ተራ ስላቅ ይሆናል::

## መጣጥፎች

# «ሁለት ደቂቃ ለስንት ሰቆቃ ይበቃል?!»

አቤ ቶኪቻው

abeto2007@yahoo.com

ወዳጄ እንደምን ሰንብተዋል? ቀጥሎ የሚቀርብ አንድ ጨዋታይኖረናል:: ጨዋታው ከዚህ በፊት አውግቼዎት ሊሆን ይችላል:: ወይ ደግሞ ሌላ አውጊ ሲያወጋ ሰምተው ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን አንድም ከላይ ካነሳነው ርዕስ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው በመሆኑ፤ ሁለትም ውጊያ እንጂ ወግ ቢደገም ጤና ላይም ሆነ ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጥረው ቀውስ ባለመኖሩ የተነሳ እንደሰሙት የምጠረጥረውን ጨዋታ እንደሚከተለው እደግመዋለሁኝ::

መምህሩ ለተማሪዎቻቸው ግጥም እንዲፅፉ ያዟቸዋል:: «የግጥሙ ርዕስ ጉዳይ ሀገራችን ኢትዮጵያ ትሁን...» አሉ መምህሩ:: ተማሪዎቹም በአንድ ድምፅ «እሺ» አሉ:: የመምህሩ መመሪያ ቀጠለ:- «ግጥሙ ስድስት መስመር ይኑረው...» አሁንም ተማሪዎቹ መመሪያውን ተቀበሉ፣በመጨረሻም «በስድስት ደቂቃ ውስጥ ጨርሱ» በማለት ትዕዛዛቸውን አጠናቀቁ:: ተማሪዎቹ እንደታዘዙት በስድስት ደቂቃ ውስጥ ስድስት መስመር ያለው ግጥም ለዛውም ስለታላቋ ኢትዮጵያ፤ ሰማንያ ብሔረሰብ፣ ሰማኒያ ሚሊዮን ህዝብ፣ ሰማኒያ ሚሊዮን ችግር፣ ሰማኒያ ሚሊዮን ደስታ፣ ሰማኒያ ሚሊዮን ወዘተ ላላት ሃገር ስድስት መስመር ግጥም ለመፃፍ መውተርተር ጀመሩ:: መምህሩ እጃቸውን ኪሳቸው ከተው ከወዲያ ወዲህ እየተንጎራደዱ የተማሪዎቹን ስድስት ደቂቃ ይቆጣጠራሉ:: ከአፍታ ቆይታ በኋላ አንድ ተማሪ እጁን መዥረጥ አድርተጎ መዘዘና «መምህር ጨርሻለሁኝ::» አለ:: «እስቲ አንብበው» አሉ መምህሩ እጃቸው ከኪሳቸው ሳይወጣ አፋቸው ለሂሳቸው እየተሰናዳ:: ተማሪው ግጥሙን አነበበ::

«እንኳን ስድስት መስመር፣
መቶም አይበቃሽ::

እንደው በደፈናው፣
የጉድ ሀገር ነሽ፡፡»

አለ፡፡ መምህሩ ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ «ደህና ግጥም ነበር፡፡ አንዱም ጉድ አንተ ነህ...ነገር ግን ስድስት መስመር አልሞላም» ብለው ትልቅ ኤክስ አደረጉበት፡፡ (ኤክስ ለመስጠት ምክንያት ከሚያፈላልግ መምህር ይሰውርዎ! «አብሮ ይሰውረን» ይበሉኝ ወዳጄ፤እንዲህ እርስ በርሳችን እየተመራረቅን ካልሆነ የዘንድሮ ኑሮ የሚገፋ አይደለም፡፡)

እኔ የምለው ወዳጄ የዘንድሮ ምርጫ ክርክር እንዴት ነው? ደህና እየኮመኮሙልኝ ነው? ወይስ ኢቲቪ «ፍሪ» ነዎት? እኛ በስልካችን ውስጥ «ያልዎት ቀሪ ሂሳብ አነስተኛ ነው» እንደምትለን አይነት ሴትዮ ሰዎቻችንን «ያልዎት ቀሪ ሰዓት ሁለት ደቂቃ ነው...» እየተባሉም ቢሆን ችግሮቻችንን ለማስረዳት የሚያርጉት ጥረት የሚበረታታ አይደለም ይላሉ? ምንም እንኳ አንዳዳንድ ወገኖች «ሁለት ደቂቃ ለስንት ሰቆቃ ይበቃል?» እያሉ ቢጠይቁም ሰዎቻችን ደቂቃዋን ለማብቃቃት የሚያደርጉት ጥረት እኛም ለኑሮአችን ደቂቃን ሳይሆን ምግብ እና መጠጣችንን ለማብቃቃት ጥሩ ትምህርት እየሰጠን ይገኛል፡፡

አንድ ወዳጄ በቅርቡ ከአፋር ሎጊያ አካባቢ ስልክ ደውሎልኝ ነበር፡፡ እናም ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ በሀገሩ በዓል መሰረት «ዳጉ» ማድረግ ጀመርን፡፡ (በቅንፍ የአቅሜን ያኽል ስለ ዳጉ ማብራሪያ እሰጣለሁኝ፡፡ «ዳጉ» በአፋር ነዋሪዎች ርስ በርሳቸው መረጃ የሚለዋወጡበት ስልት ሲሆን ከወደ ሰሜን የሚመጣው አፋር ከወደ ደቡብ አቅጣጫ ለሚመጣው ጓደኛው ያየውን የሰማውን ያጋጠመውን (ሲጋነንም) ሊያጋጥመው ያሰበውን ሁሉ ሳይቀር መረጃ የሚያቀብልበት ስልት ነው፡፡ በ«ዳጉ» ጊዜ «ሁለት ደቂቃ ቀርቶሀል ሀሳብህን አጠናቅ» የሚል የለም፡፡ የያዙት መረጃ ካልተጠናቀቀ መላቀቅ የለም፡፡) እናም ወዳጄ ባደረሰኝ «ዳጉ» መሰረት በመብራት እጦት የተነሳ ክርክሩን ለመከታተል አልቻልንም «መላዎ መላዎ ምንድነው መላዎ!?» ሲል በዜማ ጠይቆኛል፡፡ እኔ ዜና እንጂ ዜማ አልከታተልምና ሰሞኑን በሰማሁት ዜና የግልገል ጊቤ ችግር በቅርቡ ስለሚቀረፍታ ከመብራት ችግር እንደምንገላገል ጥቆማ አድርሼዋለሁኝ፡፡

እውነት ግን ይሔ የመብራት ነገር እንዴት ነው ነገሩ? መብራት ሀይሎች ምናለ በተለይ አንዳንድ ወሳኝ እና ልማታዊ የሆኑ (ልማዳዊ አላልኩም) ልማታዊ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ላይ መብራቱን ባታጠፉብን? ለምሳሌ ባለፈው ሳምንት የአልማን ቴሌቶን እንዳንከታተል ሆን ተብሎ ይሁን በአጋጣሚ ባይለይም ልክ ፕሮግራሙ ሲጀምር የጠፋው መብራት ፕሮግራሙ መጠናቀቁን ካረጋገጠ በኋላ ነበር የመጣው፡፡ «የት ሄዶ?» ብለው ቢጠየቁ «መብራቱ እራሱ ፕሮግራሙን ሊከታተል ሄዶ ነበር፡፡» ብለው በፌዝ የመለሱ ሰዎች አይጠፉም፡፡ ኧረ ተዉ ኤልፓዎች እኛንም ማሾፊያ አታድርጉን!

አልማ ግን ደህና አድርጎ «አልሸቀለም» ትላላችሁ? በርግጥም ገንዘቡ ከመድረክ ለሰማናቸው የተቀደሱ አላማዎች የሚውል ከሆነ መልካም ነው፡፡ በስሚ ስሚ እንደሰማነውማ አንዳንዶች «ግማሽ ሀብቴን እሰጣለሁኝ» ብለው ሁሉ ቃል ገብተዋል አሉ፡፡ «እንዴት ነው ነገሩ ፍቺ አስመሰላችሁት እኮ!» ብለን ብንላቸው «ነገሩ እንኳ ከፍቺ ይልቅ ለጋብቻ ይቀርባል፡፡» ሲሉ ከነገሩን በኋላ እርዳታውን በመስጠታቸው የሚገኙ አንድ አንድ ጥቅማ ጥቅሞችን ጠቃቅሰውልናል፡፡ እንዲህ ነው እንጂ «በማንኪያ ሰጥቶ በአካፋ መቀበል!» የሆነ ሆኖ አልማዎች

«አንድ ሆነን እንደ ሺህ... ሺህ ሆነን እንደ አንድ!» ብለው ከየ አቅጣጫው የሰበሰቡት ብር ቁምነገር ላይ እንዲያውሉት እና በአጉጉል ነገር እንዳይጠፉ በረከቱን ያፍስላቸው እንላለን!

ከላይ «አንድ ሆነን እንደ ሺህ ሺህ ሆነን እንደ አንድ!» የሚለውን የአልማዎችን ሀይለቃል ሳነሳ ትዝ ያለኝ «አንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲ» ነው:: ብዬ ብልም በክፉ ይተረጎምብኝ ይሆን?

እውነት ግን የአንድነት ፓርቲ አባላት ነገር እንዴት ነው? ባለፈው ሳምንት ከወጡ የጋዜጣ ዜናዎች ሁሉ የተመለከትኩት ማራኪ ርዕስ ቢኖር «አንድ ብርቱካን ለሁለት!» የሚለው ርዕስ ነው:: መጀመሪያ ላይ ርዕሱን ብቻ እንደተመለከትከትኩኝ ስለ ኢትፍሩቶች ብርቱካን መወደድ የሚያወራ መስሎኝ ነበር:: (ለነገሩ የእርሱም ዋጋ የትየለሌ ነው::) ኋላ ላይ ግን ለካስ የሚያወራው ስለ ዳኛዋ፣ ስለፖለቲከኛዋ፣ ስለ እስረኛዋ... ብርቱካን ሚዴቅሳ መወደድ ነው:: ባሳለፍነው ሳምንት ውስጥ በአንድነት ፓርቲ ውስጥ «መርህ ይከበር!» እያሉ ደጅ ሲጠኑ የከረሙ አባላት «ከዛሬ ጀመሮ በህግ አግባብ የአንድነት ፓርቲ አመራሮች እኛ ነን:: ዋና ሊቀመንበራችንም ብርቱካን ሚዴቅሳ ናት» በማለት አንድ መግለጫ አውጥተው ነበር:: ይህንን የሰማ አንድ ወዳጄ «ይቺ ሴትዮ ከአንድም ሁለት ቦታ እርሷ በሌለችበት ሊቀመንበራችን ናት እየተባለች ነው:: ለምን በስሟ ጥዋ አይጠቱላትም» ሲል በብስጭት ተናገረ:: የሰውየውን ብስጭት ልብ ብዬ ከተመለከትኩኝ በኋላ «የእኛ ሰው ነው ብዬ እያሰብኩኝ» ሰዎቹ በሁለት ጎራ ሆነው በየወሩ ጧፍ እያበሩ የሚያነግሷትን አስታውሼው ከፊቷ ቅድስት የሚል ቅፅል አልሰጧትም እንጂ አከባበራቸውስ ያው ከጥዋ አይተናነስም አልኩት:: በዚህ ጊዜ ይበልጥ ብስጭት እያለ «እስር ቤት ስትገባ የሚያስታውሳት ያለ አልመሰለኝም ነበር:: አሁን ብለው ብለው ሰዎቹ ከአንድም ሁለት ቦታ ሊቀመንበር አድርገው ሾሟት እና አረፉት?» ሲል ትንሽ ተከዝ ካለ በኋላ «ሁለት ቦታ ሊቀመንበር ሆኖ መሾም በአዲሱ የፓርቲዎች ስነምግባር ህግ አያስጠይቅም እንዴ?» ሲል ጠየቀኝ:: እኔም በሀሳቤ ከእኛም በላይ ለግንባሩ ተቆርቋሪ ለካስ በየቦታው ብዙ አለና ብዬ ሳስብ አራት ሚሊዮኑ አባላት በሀሳቤ ትዝ አሉኝ::

አንድነት ፓርቲ ግን አንድነቱ ስሙ ብቻ ሆኖ ሊቀር ነው ማለት ነው? አንተም ተው አንተም ተው የሚል አንድ ትልቅ ሰው እንዴት ይጠፋል? በእውነት ግራ የሚገባ ነገር ነውኮ! ህዝቡ እህል ያጠግቡኛል ብሎ ተስፋ የጣለባቸው ሰዎች እልኽ እንጂ እህል የሚያቀርቡለት አልመሰለኝም:: በዚህ እልኽ የተነሳ የ«አንድነት» ፓርቲ አባላትን አንድ የሚያደርጋቸው በእስር ላይ የምትገኘዋ የህግ ባለሞያ የጋራ ሊቀመንበረቸው መሆኗ ብቻ ነው:: ሰላሙን ያውርላቸዋ!

እኔ የምለው የዚች የሁለት ደቂቃ ነገር ግን እንዴት ናት? በፓርላማ ውይይት ሁለት ደቂቃ... በፓርቲዎች ክርክር ሁለት ደቂቃ... «ችግራችን ብዙ ደቂቃችን ትንሽ...» ሆነ እያለ ሰዉ በየ ጓዳው እያወጋ ነው:: የሚባለው ነገር እውነት ነው እንዴ? የስድስት መስመሯን ግጥም ያስታወሰኝም ይኸው ነው:: ከታማኝ ምንጮች እንደሰማሁት ከሆነማ አንድ አንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በየ ክርክሩ የሚቆረጥባቸውን የክርክር ሀሳብ እና በሁለት ደቂቃዋ ማለቅ ያቃታትን ሀሳብ በቪሲዲ ለደጋፊዎቻቸው ለማቅረብ አስበዋል አሉ:: (ታድያ አሉ ነው) ይቺ ጥሩ ዘዴ ሳትሆን አትቀርም::

በመጨረሻም

መኢአድ

በአሁኑ ወቅት ካሉ አንጋፋ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል የሚመደበው መኢአድ የዛሬ አምስት አመት ለተፈጠረው ታሪካዊው «ቅንጅት ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ» ፓርቲ ምስረታ ዋነኛ አስተዋፅዖ ካደረጉት መካከልም ነበር፡፡ (የህይወት ታሪክ የሚያነቡ እአስመሰልኩብዎ እንዴ? ይቅርታ ጠይቄ እቀጥላለሁኝ፡፡)

መኢአድ ባለፈው ሳምንት ውስጥ አንድ ህዝባዊ ስብሰባ ጠርቶ ነበር፡፡ ህዝባዊ ስብሰባውን ሲቀሰቅስ የነበረው ትጉህ ቀስቃሽ «አልረሳም አለኝ...» በሚል አንድ ባህላዊ ዘፈን ታጅቦ «እንዴት ይረሳል ሚያዝያ ሰላሳ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሰባት...» ካለ በኋላ «ዛሬም ያንን ታሪክ ለመድገም መኢአድ ባዘጋጀው ስብሰባ ይምጡ... የስብሰባ ጥምዎንም ይቁረጡ...» (እዚች ላይ ለወሬ ማድመቂያ ብዬ እኔም ትንሽ ጨማምሬያለሁኝ፡፡) ለማንኛውም በዚህ መልኩ የተቀሰቀሰው ስብሰባ ባለፈው ሳምንት ውስጥ ተካሂዶ ነበር፡፡ በውሃ ልማት አዳራሽ፡፡ (በቅንፍ ውሃ ልማቱም ውሃ ማደሉን ትቶ አዳራሽ ማከራየት ዋናው ስራ አድርጎታል!) ታድያ የመኢአድ አመራሮች በስብሰባቸው ላይ ፕሮግራም እና እጩዎቻቸውን ከማስተዋወቅ በዘለለ በተለይ የስምንት ፓርቲዎች ጥምረት ሆነውን «መድረክ» አባላት እያንዳንዳቸውን ስም እየጠቀሱ ሙልጭ አድርገው ልክ ልካቸውን ነግረዋቸዋል፡፡ ኧረ ምን መድረኮችን ብቻ ማናቸው ውጪ ሃገር ያሉት... እኒያ ዶክተሩ... (እዚህ ሀገር ስማቸውም ሆነ የሚመሩት ድርጅት ስለማይጠራ ነው ይቅርታ ያድርጉልኝና ሰባት የሚባል ቁጥር ራሱ መጥራት ከባድ ሆኗል) በመኢአዶች ስብሰባ ግን እርሳቸውም አልቀረላቸውም፡፡ የቀረ ተቃዋሚ የለም እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ተደርጎ ተነገረው እልዎታለሁኝ፡፡

ታድያ ይህንን የተከታተሉ ገለልተኛ ሰዎች «መኢኢድ የተቃዋሚዎች ተቃዋሚ ነው ወይስ የገዢው ፓርቲ ተቃዋሚ?» ሲሉ ደረቅ ጥያቄ ጠይቀውኛል፡፡ እኔም አማራጭ ለሌላቸው ጥያቄዎች መልስ መስጠት ብቃቱ ስለሌለኝ ጥያቄውን ለሚመለከተው ክፍል መርቼዋለሁኝ፡፡

አሁን ቻው እንባባል...

አማን ያሰንብተን!

# ፖሊስ፤ ሕግ አስከባሪ ወይንስ መብት ሸርሻሪ?

**በግዛው ለገሠ**

መቼም የዴሞክራሲ ግንባታ ቃሉን የመሸምደድ ጥረት አይደለም፤ ለህዝብ የወገነ የመንግስት ሥርዓትን ለማቆም ምሰሶዎችን የመትከል ግንባታ እንጂ፡፡ ምሰሶዎቹ ጥንካሬያቸው አስፈላጊ ቢሆንም ከፅድ ወይም ከአርማታ የተሰሩ እንዳልሆኑም ግልፅ ነው፡፡ ፍርድ ቤት፣ ፓርላማ፣ ምርጫ ቦርድ፣ ሚዲያ... የመሳሰሉት ተቋማት ሁሉ የአንድ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሰሶዎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል «ሕግ» በራሱ አንድ ራሱን የቻለ ተቋም ነው፤ ያለ «ሕግ» ሥርዓት አይኖርምና፡፡ ይሁንና ግን ሕግን ጨምሮ ሁሉም ተቋማት ተሳስረው በአንድነት ካልተወጠኑ በቀር አሁንም ሥርዓት አይኖርም፤ ቢኖርም የተሰናከለ ይሆናል፡፡ እንግዲህ ሰላምን

ለማስፈን፣ ሕግን (መብትን) ለማስከበር፣ እንዲሁም ሥርዓቱን በሥርዓትነት ለማስቀጠል ወሣኝ ናቸው ከሚባሉት ተቋማት መካከል ደግሞ «ፖሊስ» አንዱ ነው፡፡

በቅድሚያ በጥቅሉ ስለተቋማት እናውራ፡፡ ተቋም ወፍ ዘራሽ አይደለም፤ የሚቋቋምበትን ዓላማ ቅልብጭ አድርጐ የሚያስቀምጥ ፈጣሪ ሕግ አለው፡፡ ዓላማዎቹ ተፈፃሚ የሚሆኑበት መንገድ «ደመ-ነፍስ» አይደለም፤ በሕግ የተዘረዘረ እንጂ፡፡ ጐን ለጐንም ተቋሙን የሚያንቀሳቅሱ ሰዎች ብቁነታቸው ተረጋግጦ ሲመደቡለት ቢያንስ በመርህ ደረጃ ተቋመን ሙሉ ያደርጉታል፤ ምክንያቱም ከአንቀሳቃሾቹ ሰዎች ወይም ከተፈፃሚው ሕግ (ዓላማ) እንከን ቢገኝ ተግባረ-ምሉእነቱን ያደናቅፈዋልና፡፡ ከዚህ አኳያ «ፖሊስ» የተሰኘው ተቋም ምንም ያህል ሰናይ ዓላማን የሰነቀ የመቋቋሚያ ሕግ ቢኖረው፣ ምንም እንኳን አባላቱ (አንቀሳቃሾቹ) ይታነፁበት ዘንድ የተሟላ የማስፈፀሚያ (የሥነ-ምግባር) ሕግጋት ቢኖረው የአንድ ፖሊስ ምግባረ-ብልሹነት ብቻውን የተቋሙን ተግባረ-ስንኩልነት ያሳብቅበታል፡፡

በብሔራዊ ጀርባ ወደ ቴሌ ባር የሚወስደውን መንገድ ይዣለሁ፡፡ ደንገዝገዝ ብሏል፡፡ ሁለት ወጣቶች የቀልድ የማይመስል ልፊያ ውስጥ ናቸው፡፡ ቀረብ ስል ግን ልፍያ አልነበረም፡፡ ቡቅሻ ነው፤ ለዚያውም ያንድ ወገን፡፡ ተማቺው ፖሊስ ነበር፡፡ በአካባቢው የነበሩ ሰዎች «ኧረ… እንዴ…» እያሉ ለማገላገል ጠጋ ቢሉም አንዱ ወጣት ፖሊስ መሆኑን ሲገነዘቡ ርቀታቸውን ጠብቀው ቆሙ፡፡ ሆኖም አንድ በእድሜ ጠና ያሉ ሰው ተገቢ ድርጊት አለመሆኑን ለመናገር ሞክረው ነበር፤ ከፖሊሱ የተሰጣቸው «ሌባ ነው» የሚል ምላሽ ግን እንዳይገፉበት አደረጋቸው፡፡ ጥያቄ አንድ፡- ፖሊስ መሆን የመማታት ሥልጣንን ያጐናጽፋልን? ጥያቄ ሁለት፡- «ሌባ» ብሎ የመወሠን ሥልጣን የፖሊስ ነውን? ጥያቄ ሦስት፡- በዚህ ዘመን «ሌባ» ተብሎ በፍርድ ቤት የተወሰነበትን እንኳን በግርፋት መቅጣት ይቻላልን? ሕጉንና ትግበራውን ለተመለከተ ለሦስቱም ጥያቄዎች ምላሽ ያጣል፡፡

በርግጥም ይህ ጽሁፍ ሁሉንም የፖሊስ አባላት ወይም የአጠቃላይ ተቋሙን ምንነት ላይወክል ይችላል፤ ፖሊስ የመሆናቸው ዓላማ ህብረተሰቡን ለማገልገል፣ በህዝብ ዘንድ የሰላምን መንፈስ ለማስረጽ መሆኑ ገብቷቸው በፊታቸው ገፅታ እንኳን ሳይቀር በፈገግታና በአለኝታነት ስሜት የሚቀኙን አያሌዎች አሉ፡፡ በዚያው ልክ ግለሰባዊ ስሜታቸው ከተሰጣቸው ጠንካራ ኃላፊነት ልቆባቸው ቃል ኪዳናቸውን የሚዘነጉ፣ የቆሙለትን ዓላማ ወደጐን የሚገፉ፣ ፖሊስ መሆን ከሕግ በታች ሆኖ ማገልገል መሆኑን ለአፍታ እንኳን ያለተገነዘቡ አባላት ስለመኖራቸው የሚክድ አይኖርም፡፡

ከላይ ያስቀመጥኩት ከብዙዎቹ ገጠመኞቼ አንዱ ነው፡፡ እንዲህ ያለው ሁኔታ እኔን ብቻ የሚገጥመኝ ሁሉ ይመስለኝ ነበር፡፡ ሆኖም ይህን ጉዳይ ያነሳሁለት ወዳጅ፣ ዘመድ፣ የሥራ ባልደረባ ሁሉ ያየውን፣ የሰማውን፣ እንዲሁም የደረሰበትን ሲያጫውተኝ ይህ ሌት ተቀን የሚዘመርለት የተቋማት ግንባታ ያሳስበኛል፡፡

በቅርቡ ነው፡፡ የዚህ ጋዜጣ ግራፊክ ኤዲተር ከሆነው ባልደረባዬ ጋር ቅዳሜን፣ ብቸኛ የዕረፍት ቀናችንን በወጉ አጣጥመን እየተሸኘኘን ነው፡፡ ከኦሎምፒያ ወደመስቀል ፍላወር በሚወስደው መንገድ ላይ ዳሽን ባንክ አካባቢ ነን፡፡ ሁለት (ወንድና ሴት) ወጣቶች ጠበቅ ያለ ጭቅጭቅ ላይ ናቸው፡፡ እንደመያያዝ ብለውም አብረዋቸው የነበሩ ሰዎች አገላግለዋቸዋል፡፡ ደግሞ እንደገና ይጨቃጨቃሉ፡፡ ወንዱ ወንድነቱን ለማሳየት ሲጥርም አይተነዋል፤ ምናልባት

ሳይሰነዝርም አልቀረም - ወደ ሴቷ:: ከመቅጽበት አንዲት ነጭ ቶዮታ ፒክአፕ መኪና ትክክል ባልሆነ (በድንገተኛ) አቋቋም ከተጣዮቹ ወጣቶች ፊት ትቆማለች:: («ፖሊስ» የሚለው ቢጫ ታርጋ ተለጥፎባታል::) ወዲያውም ሾፌሩ ተንደርድሮ በመውረድ ወንዱን ወጣት ያለማስጠንቀቂያ ይመታዋል:: ልጁ «ለምን ትመታኛለህ፤ የመማታት መብት የለህም» እያለ ይጮኻል:: ከመኪናዋ ውስጥ ከላይ የለበሰው ልብስ ወልቆ በካኒቴራ የሚታየውን ሾፌር ጨምሮ ሙሉ ዩኒፎርም የለበሱ፣ አንድ ሴት እና ሁለት ወንድ ፖሊሶችም ወርደዋል:: አንደኛው ዩኒፎርም ለባሽ ፖሊስ ወደማገላገሉ አመዝኗል፤ ሌላኛው ግን የተሰበሰበውን ሰው ለመበተን ይሁን፣ «ለምን ትመታኛለህ» የሚለውን ወጣት ዝም ለማሰኘት ባይታወቅም የያዘውን ክላሽንኮቭ አስሬ እያቀባበለ ይንቀሳቀሳል፤ ሴቷ ፖሊስ ተረጋግታ ቆማለች::

እዚህ ላይ «እሱስ ቢሆን ሴት ልጅን እንዴት ይመታል?» የሚል አንባቢ እንደሚኖር ጥርጥር የለኝም:: ሙሉ ለሙሉ እስማማለሁ፤ ሕግ ባለበት ሀገር ሴት ልጅ ቅንጣት ታክል ልትነካ አይገባም:: ነገር ግን «ወንድ ልጅ ይመታ» የሚለውስ ሕግ የትኛው ይሆን? ፖሊስ ጠብ አብራጅ ሊሆን ሲገባ የጠቡ አካል የሚሆንበት አግባብስ የቱ ነው? በኋላ ጠቡ መብረዱ ባይቀርም እኔ ግን ቆሜ ማየት አላስቻለኝም ነበር:: ተረጋግታ ቆማ የነበረችውን ፖሊስ ለማናገር ሳመራ ባልደረባዬም ተከትሎኛል:: «የሆነውን ሁሉ ስከታተል ነበር... መማታት ተገቢ ነወይ... ለተቋሙ ገጽታ ሲባልስ ሁለቱን ወጣቶች ሌላ ቦታ ወስዶ ማነጋገር አይቀልም ወይ?...» እያልን ሴቷን ፖሊስ እያነጋገርን ሳለ ነበር አንድ ሲቪል የለበሱ ቁመተ-ረጅም ሰው መጥተው «እናንተም ጋር ችግር አለ?» ሲሉ የጠየቁን:: «አይ፣ እኛ ጋር ችግር የለም... እንዲሁ ሀሳብ ለመጠቆም ነው... እኛ ጋዜጠኞች ነን» ከማለቴ «ምንም መረጃ አንሰጥም..» በማለት ኮማንደር እከሌ መሆናቸውን አስታወቁን:: መረጃ ፈልገን እንዳልሆነ፣ እንዲያውም መረጃ ለመስጠት መሆኑን ብንገልጽላቸውም ሳንግባባ ተለያየን::

ምናልባትም ይህንን ክስተት ከምንም የማይቆጥር አንባቢም ይኖራል፤ ከዚህ የባሰ ሁኔታ ያጋጠመው ይኖራል:: በሌላ በኩል በፖሊስ አሌኝታነት ህይወቱ የዳነ፣ ንብረቱ የተረፈ አንባቢም መኖት ይሆናል፤ ፖሊስ በተመለከተ ቁጥር ሰላማዊ መንፈስ ሊሰማው ሲገባ አንዳች ነገር የሚረብሸው ዜጋ መኖሩ ሳይዘነጋ:: ለምሳሌ፣ የፋሲካ ሰሞን በየመጠምዘዣ መንገዱ ላይ ፍተሻ ሲያካሄዱ የነበሩ ፖሊሶች (እኔን ያጋጠሙኝ) እጅግ ትህትና የተሞላባቸው ነበሩ:: በርግጥም ፖሊስ፣ እንደተቋም ለህዝብ ደህንነት የቆመ መሆኑን በተግባር ሲያመላክቱ ታዝቤያለሁ:: (በየመታጠፊያው ሦስት፣ አራቴ መፈተሼ በመጠኑ ሊያሰለቸኝ የተቃረበ ቢሆንም::) ይህ ጽሁፍ ተቋሙን በጥቅል የመንቀፍ ዓላማ እንደሌለው እንዲህ ከገለጽኩኝ ዘንዳ አንድ የኔ ያልሆነ ገጠመኝ ልጨምር::

ዑራኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ነው:: «ሰፈር ውስጥ እየገቡ ልብስ ይሰርቃሉ» በሚል ሁለት ልጆች እራሳቸው ይዘውት በነበረ፣ ፍራሽ አዳሾች ለፍራሽ እደሳ የሚጠቀሙበት ሽቦ በመሰለ ነገር ይገረፋሉ:: ከገራፊው ጋር የነበረው ሌላኛው ፖሊስ መሣሪያ ይዞ በጥያቄ ያፋጥጣቸዋል:: የልጆቹ መልስ «እኛ ምንም አላደረግንም» ይሁን አንጂ መገረፋቸው አልቀረም:: ግርፊያው ቦታ ያልመረጠ ሳይሆን አልቀረም መሰል፣ አንደኛው ልጅ ዓይኑ አካባቢ ደምቷል:: ህዝቡም እንደተለመደው ዙሪያ ከቦ ትዕይንቱን ይከታተላል:: «ህዝቡ ምን ያድርግ?» የሚል ሊኖር ይችላል፤ «አትምቷቸው፣ ጣቢያ ወስዳችሁ በአግባቡ ጠይቋቸው፣ ሁነኛ መረጃ ካገኛችሁባቸው

(የዋስ መብታቸውን አክብራችሁ) መረጃውን አጠናቅራችሁ ለአቃቤ ሕግ አስተላልፉ፣ በኋላም ፍርድ ቤት አስቀርቧቸው...» ብሎ ማለት አይቻልም ይሆን? ይህንን የሚል ሕግ እንዳለን አሳምሬ አውቃለሁኝ! ልጆቹ ግን ተገርፈው «በሉ ጥፉ» ተብለው ተለቀቁ:: በሌላ አገላለፅ ከሳሽ፣ ፈራጅ፣ ቀጪ የተሰኙ መዋቅሮች በአንድ አካል ሊጨበጡ ይቻላልን?

ይህ ጽሁፍ ከፖሊስ ገለልተኛነት ጋር፣ አልያም ከሌሎች የፖሊስ ሥነ-ምግባሮች ጋር የተገናኘ አይደለም፤ ይህንን ሁሉ በአንዲት ጽሁፍ መዳሰስ አስቸጋሪ ነውና:: ይልቁንም ከፖሊስ የኃይል አጠቃቀም ወይም «use of force» ጋር ይያያዛል:: በቅድሚያ ሰላምን ለማስከበር በሚል አንድ ፖሊስ ኃይል መጠቀም ይችላል ወይ? አዎ፣ ይችላል:: የሚጠቀመውስ መቼ እንዴት፣ በምን ሁኔታና ምን ያህል ነው? ለምሳሌ፣ አንድ አቅመ ደካማ እስረኛ ለማምለጥ ቢሞክሩ ሮጦ መያዝ እየቻለ በጥይት እግራቸውን መትቶ የሚያስቆም ፖሊስ ገደቡን አልፈኻል ሊያስብለው ይችላል:: ከእንዲህ ያሉ ምሳሌዎች ባሻገር ፖሊስ በጭራሽ ኃይል የማይጠቀምባቸውም ሁኔታዎች አሉ:: ከአንድ ተጠርጣሪ መረጃ ለማግኘት ምንም ዓይነት ኃይል ቢጠቀም፣ አንደኛ- መረጃው በፍርድ ቤት ተቀባይነት አይኖረውም፣ ሁለተኛ ደግሞ«ቶርቸር» እንደመፈፀምም ሊፈረጅ ይችላል::

ለአንድ መንግስታዊ ሥርዓት መስፈን፣ ወይም ለአንድ ህብረተሰባዊ መስተጋብር ሰላም ፖሊስ ወይም ሕግ አስከባሪ የመኖሩ ጉዳይ የግድ ስለመሆኑ የማይስማማ አይኖርም:: በሀገራችንም ፖሊስ፣ እንደአንድ የዴሞክራሲ ሥርዓት ምሰሶ (ተቋም) ለቀጣይ የህዝቦች እጣፈንታ ሚናው ከፍተኛ ነው:: ይሁንና ግን ህብረተሰቡ ለፖሊስ የሚሰጠውን ትርጓሜ የማዛባት አቅም ያላቸው አንዳንድ ፖሊሶች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ ወይም እንዴት እንደሚወጡ ሊነገራቸው ይገባ ይመስለኛል:: አንድ ሰው እንደዜጋ ምግባረ-ብልሹ ስለሆነ ፖሊስ ለበላይ አለቆቹ የማመልከት ልማድ አለው ወይ? ይህ ልምድ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ሲንቀሳቀሱ መለያቸውን (ባጃቸውን) በግልጽ የሚያሳዩ ፖሊሶችስ ስንቶቹ ናቸው? በምግባራቸው የተቋሙን ገጽታ የሚያበላሹትን አባላት ለመጠቆም የበላይ አካል ዘንድ ቢኬድስ ክትትሉ የት ድረስ ይዘልቃል? ይህንን ጽሁፍ በምፅፍበት ወቅት ባልደረቦቼ «አምባሳደር ጋር እንዲህ ሆኖ ነበር፣ አራት ኪሎ ጋር...» እያሉ ገጠመኞቻቸውን መዋዋሳቸው ቀደም ሲል ያነሳኋቸው ጥያቄዎች ገና መመለስ እንዳለባቸው እንዲሰማኝ አድርጎኛል::

በግሩፕ ሆነው ሊዝናኑ የወጡ ወጣቶች ናቸው:: ጥግብ ብለው ሰክረዋል፤ በተለይ አንዱ «ለይቶለታል» ሊባል ይችላል:: ድንገት ከተረኛ ፀጥታ አስከባሪ ፖሊሶች ጋር ይገናኛሉ:: ያ የለየለቱ ፖሊሶቹን ሲመለከት «ፖሊስ የሰላም ዘብ፣ ፖሊስ...» እያለ ዝማሬውን ሲጀምር አጣጭ ወዳጆቹ አላስቻላቸውም - መሬት እየነኩ ሳቃቸውን ለቀቁት:: ፖሊሶቹም አላስቻላቸውም፤ ጠጋ ብለው የማላገጥ ዝማሬ የሚያከናውነውን፣ የለየለቱን «አንድ-ሁለት» ብለው ከመሬት አስተኙት:: ታዲያ ይኼኔ አጣጭ ወዳጆቹ ከሳቃቸው ተላቀው «ኧረ ሰክሮ ነው... እብድ ነው... አብሾ አለበት» እያሉ ተማፅኖ ይገባል:: ፖሊሶቹም ዘማሪውን እመሬት ትተውት መንገዳቸውን ይቀጥላሉ:: የለየለቱ ግን እንደምንም ተደጋግፎ ተነሳ፤ ደገመው፤ «ፖሊስ የሰላም ዘብ፣ ፖሊስ...»:: የመጀመሪያው «አንድ-ሁለት» ዝም ሊያሰኘው አልቻለም፤ ፖሊሶቹ ተመለሱለትና ደገሙለት:: «ኧረ ባካችሁ... ሰክሮ ነው... አብሾ አለበት»፣ የጓደኞቹም ተማፅኖ ተመሳሳይ ነው:: እንደምንም ተላቀውት መንገዳቸውን ሲጀምሩ እንደምንም ተፍጨርጭሮ ይነሳና «ፖሊስ የሰላም ዘብ፣...»

ማለቱን ይቀጥላል፡፡ ምንኛ እንደሚያቃጥል አስቡት፤ ፖሊሶቹም በመጨረሻ ሰልችቷቸው ነው የሄዱት፡፡ ይህንን ገጠመኝ ያጫወተኝ፣ በወቅቱ ከአጣጮቹ መካከል የነበረው ወዳጄ ያ የለየለቱ እቤቱ እስከሚገባ ድረስ መዘመሩን እንዳላቆመ ሲነግረኝ ሁኔታውን በማያቋርጥ ሳቅ እያስታወሰ ነበር፡፡ በርግጥ ገጠመኙ እኔንም አስቆኛል፤ ነገር ግን በሰካራሙ ላይ የተወሰደው እርምጃ የግል ስሜትን እንጂ ሕግን የተከተለ እንዳልነበር አምናለሁ፡፡

አንባቢያን ሆይ፣ በዚህ ቅጽበት የየግላችሁን ገጠመኞች እየሰላሰላችሁ እንደምትገኙ ይሰማኛል፡፡ ሁሉም ሰው መጥፎ ገጠመኞች አሉት ብዬ አላስብም፤ ከፍ ብዬ እንደገለጽኩት የምንመካባቸው የፖሊስ አባላት አያሌ ናቸው፡፡ ሆኖም ገጠመኞቻችሁን መጥፎና ጥሩ ብላችሁ አመዛዝኗቸው፤ ለፖሊስ የሚኖራችሁ ትርጓሜ ሚዛኑ ላይ ይመረኮዛልና፡፡ በተቋም ደረጃ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው፣ ፖሊስ የህብረተሰቡ አካል እንደመሆኑ መጠን መከታም እንደሚሆን እምነቴ ነው፡፡ በሌላ በኩል ሌላው ዓለም «አህያ ለምን ተመታች፣ ለምን ጀርባዋ ቆሰለ?» ሲል በሚከራከርበት ዘመን ሰብዓዊ ፍጡርን መምታት ክብደቱ የላቀና ሰብዓዊ መብትን መጣስ ስለመሆኑም ልብ ሊባል ይገባዋል፡፡ «እንዲህ ያሉ ፖሊሶችን ለመቆጣጠር ሌላ የፖሊስ አካል መዋቀር አለበት እንዴ?» ብለን ለመጠየቅ እንድንገደድ አንሻም፡፡ ስለዚህም «ፖሊስ የህዝብ አሌኝታ ነው» ብለን በዴሞክራሲ ግንባታው ዘርፍ ለተቋማት ቅድሚያ እንስጥ፡፡

# የኢኮኖሚ ዕድገት መገለጫ ጂ.ዲ.ፒ. ለምን የኢኮኖሚ ዕድገትን አይገልጽም?

በበድር ባንጫረ

በኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በቁጥር ጉዳይ መጣላት እየተለመደ የመጣ ነገር ሆኗል፡፡ በተራበው ሕዝብ ቁጥር ብዛት፣ አሁን ደግሞ በኢኮኖሚያዊ ዕድገታችን መጠን፡፡ መንግሥት በአንድ በኩል ኢኮኖሚው በሁለት አሀዝ እያደገ ነው ሲል፣ አስተዳደጉ ያልገባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ደግሞ እንዴት ብሎ? እያሉ መሟገታቸውን ይዘዋል፡፡ በዚህ የኢኮኖሚ ዕድገት ትንተና ውስጥ ቁልፉ መገለጫ ሆኖ ስላለው አጠቃላይ ዓመታዊ አገራዊ የምርት ዕድገት መለኪያ «GDP» (ጂ.ዲ.ፒ.) የተወሰነ ትንተና ለማድረግ እሞክራለሁ፡፡ ይህ መለኪያ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማሳየት ፈጣን መግለጫ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡ ይህ ማለት ግን የኢኮኖሚ ዕድገትን በተመለከተ ሙሉ የሆነ ገለፃ ይሰጣል ማለት አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ጂ.ዲ.ፒ.ን እንደ ብቸኛ የኢኮኖሚ ዕድገት መግለጫ መጠቀም፣ እየተከሰተ ስላለው ዕድገት በቂ ዕይታ ሊያሳጣ ይችላል፡፡

እ.ኤ.አ. እስከ 1990፣ በአንዳንድ አገራት ለኢኮኖሚ ዕድገት መገለጫ ከጂ.ዲ.ፒ ይልቅ በአገራዊ ዜጎች የተገኘ ዓመታዊ የምርት ዕድገት መለኪያ GNP - ጂ.ኤን.ፒን እንደ የኢኮኖሚ ዕድገት መለኪያ ይገለገሉበት ነበረ፡፡ ጂ.ዲ.ፒ ዓመታዊ የአገር ኃብት ልኬት የሚያሳይ ሲሆን ይህም በአገር ውስጥ ኢትዮጵያዊ በሆኑና ባልሆኑ ዜጎች የሚመረት አጠቃላይ የምርት ዕድገትን የሚያሳይ ነው፡፡ ነገር ግን ጂ.ኤን.ፒ አጠቃላይ የዜጎች የኃብት መለኪያ ሲሆን፣ ይህም

ከአጠቃላይ የአገሪቷ ዓመታዊ የምርት ዕድገት ውጤት መጠን፣ ምን ያህል በአገሪቷ ውስጥ የቀረ መሆኑንና በአገሪቷ ዜጎች እጅ የተገኘ መሆኑን የሚገልጽ ነው።

በአገሪቷ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትልቅ ሚና እየተጫወተ ያለው፣ የውጭ አገር ሞቀኃብቶች በአገር ውስጥ የሚያደርጉት ኢንቨስትመንት «FDI» - ኤፍ.ዲ.አይ ሲሆን፣ ይህም ሴክተር በአሁኑ ወቅት ከ10 በመቶ ያላነሰ አጠቃላይ የአገሪቷን የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል። ይህም የአገሪቷ ጂ.ዲ.ፒ እያደገ ነው በተባለበት ወቅት የታየ እምርታ ነው። በመሆኑም ይህ ሴክተር ለጂ.ዲ.ፒው ካደረገው አስተዋፅዖ ምን ያህሉ ወደ አገር አቅም ግንባታ መሄዱን ማየት ያስፈልጋል። ይህም የሚወሰነው የውጭ ባለኃብቱ ካገኘው የትርፍ መጠን፣ በአገሪቷ እንዲያስቀር የሚገደደው መጠን ነው። የአገራችን የኤፍ.ዲ.አይ ፖሊሲ ከተገኘ ው ትርፉ በአገር ውስጥ መቆየት ያለበት መጠን በጣም ዝቅተኛ ከሚያደርጉት ውስጥ በመሆኑ፣ በጂ.ዲ.ፒ ውስጥ በሴክተሩ ከተመዘገበው ውስጥ የእኛው ነው የምንለው ላይ ሊኖረው የሚችለው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው።

በተጨማሪ በጂ.ዲ.ፒና በጂ.ኤን.ፒ የምዘና ሂደት ውስጥ መታየት የሚገባው ነጥብ፣ በአገራችን በጂ.ዲ.ፒ ምዝገባ ውስጥ የግንባታው ሴክተር ያለው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው። በዚህ የግንባታ ተግባራት ውስጥ የውጭ አገር ኮንትራክተሮች ሚና በጣም ከፍተኛ ነው። ሚናቸው በጣም ከፍተኛ በመሆኑም ዝቅተኛ የማይባል የአገራችን የጂ.ዲ.ፒ መጠን  እንደ ሌላ አገራት የምርት ዕድገት የመውሰድ ሁኔታ እንደሚኖር ያሳየናል። እነዚህ ዕውነታዎች የሚታይበት ሁኔታ፣ የጂ.ኤን.ፒ መለኪያን ማለትም ኢትዮጵያውያን ከውጭ አገራት የሚያገኙትን ኃብት በማካተት፣ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት በማሳየት፣ በአገር ውስጥ የቀረውን አጠቃላይ የኃብት መጠን በመለካት ለኢኮኖሚው ዕድገት የተሻለ ገለፃ ይሰጣል። እንደ ስቲግሊዝ ያሉ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ከጂ.ኤን.ፒ  ወደ ጂ.ዲ.ፒ መዞርን ከፖለቲካዊ ፍላጎቶች ጋር የተያያዘ ነው የሚል መላምት አላቸው።

የኢኮኖሚን ዕድገት በጂ.ዲ.ፒ ብቻ መግለፅ የሚከተሉት ችግሮች ይኖሩታል፤ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ኃብት በአግባቡ መጠቀምን /ውጤታማነትን/ ያለማሳየት ችግር አንዱ ነው። ለምሳሌ በአንድ አገር ኢኮኖሚ ዕድገት የጂ.ዲ.ፒ መለኪያ ውስጥ፣ የጤና አገልግሎት ዘርፉ የጂ.ዲ.ፒውን 10 በመቶ የሚይዝ ነው ብንል፣ ለዚህ ለጤና መስክ ከሚወጣው አጠቃላይ ወጪ 20 በመቶ በአግባቡ የመጠቀምን ደረጃ ለማሻሻል የሚቀር ቢሆን ኖሮ፣ የተመዘገበው ዓመታዊው ጂ.ዲ.ፒ በሁለት በመቶ ይቀንስ ነበር ማለት ነው። በአገራችን ያለውን ሁኔታ ስናይ፣ ካለው አጠቃላይ የውጭ ጉድለት እና አጠቃላይ የኢኮኖሚው ዘርፍ በግንባታ ሂደት ላይ ባለበት ሁኔታ፣ ከውጤታማነት ጋር በተያያዘ ሊደርስ የሚችል የኃብት ብክለት ነገር ግን በጂ.ዲ.ፒ ውስጥ እንደእድገት ታሳቢ ሆኖ የሚመዘገብበት የቁጥር ሁኔታ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ጂ.ዲ.ፒ አጠቃላይ ለግንባታ የተረጨውን ገንዘብ ከተገኘው የምርት ዕድገት ጋር ለይቶ አያሳይም።

ጂ.ዲ.ፒ በተጨማሪ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን የዕድገት ቀጣይነት ለማሳየት አቅም ያጥረዋል:: ለምሳሌ በዓለም ገበያ በአንድ የምርት ዓመት የደን ኃብት ምርት ከፍተኛ የዋጋ እምርታ አሳየ እንበል፤ ኢትዮጵያም ይህን ዕድል ለመጠቀም በማሰብ የደን ኃብቷን በከፍተኛ ሁኔታ ብትሸጥ፣ በዚያ የምርት ዓመት ጂ.ዲ.ፒ በከፍተኛ ሁኔታ ማደጉን ሊያሳይ ቢችልም፣ የዚህ ዕድገት በተከታታይ መከሰትን ወይም ቀጣይነትን ግን ከጂ.ዲ.ፒው በግርድፉ ማየት ያዳግታል::

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕደገት ሂደት ውስጥ ትልቁ ጥያቄ፣ ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት (Economic Growth) ሂደት ድህነትን በማስወገድ ረገድ ያለን አቅም ማስተዋል ነው:: ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ድህነትን ከማስወገድ ጋር ያለውን ትስስር ከዕድገት አቅጣጫ ባህሪ ጋር የተያያዘ ቢሆንም፣ አጠቃላይ ተፅዕኖው ግን በረጅም ጊዜ የመመጋገብ ዝምድና ላይ የተመሰረተ ነው የሚል የተሻለ መግባባት አለ:: በመሆኑም በጂ.ዲ.ፒ መልክ ተመዘገበ የተባለው ዕደገት በአገሪቷ ድህነትን እያስወገደ ነው ለማለት በተመዘገበው ዕድገትና በኃብት ስርጭቱ መካከል ያለውን ዝምድና ማየት ያስፈልጋል:: ነገር ግን ጂ.ዲ.ፒ.ን ብቻ መሰረት ያደረገ የዕድገት ገለፃ ይህን ማድረግ ይሳነዋል:: ለምሳሌ በሶስት ተከታታይ ዓመታት ተመሳሳይ ገቢ ያላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች የመግዛት አቅማቸው በ30 በመቶ ቢቀነስና በነዚህ ዓመታት ውስጥ ጂ.ዲ.ፒ.ው በ12 በመቶ ቢያድግ፣ የነዚህ የሕብረተሰቡ ክፍሎች ኑሮ እያሽቆለቆለ በጂ.ዲ.ፒ. መለኪያ ብቻ የተጠቀምን እንደሆነ፣ ኢኮኖሚው አድጓል ለማለት ያስችለናል ማለት ነው::

የጂ.ዲ.ፒ አለካክ በራሱ አሁን ባለው የዋጋ ተመን የሚለካ /normal GDP/ እና በቋሚ ዋጋ የሚለካ /real GDP/ በመባል ይታወቃል:: የመጀመሪያው አይነት መለኪያ የዋጋ ለውጥን ወይም የዋጋ ግሽበትን ታሳቢ የሚያደርግ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ይህን የዋጋ ተመን የምንወስድበት ዓመት (base year እ.አ.አ. 1992)፣ በ2001 በ11 በመቶ አደገ የተባለው በ1992 የዋጋ ተመን የተሳከውን የኢኮኖሚ ዕድገት እንጂ፣ በጊዜው በ2001 ዋጋ የተወሰደው ኢኮኖሚ ያደገው እንግዲህ በ45 በመቶ ነው::

አንድ ሰው እንውስድና በሁለት ተከታተይ የኢኮኖሚ ዓመታት 100 ብር የሚያገኝ ቢሆን፣ ይህ ግለሰብ በቀደመው ዓመት በ100 ብር አስር ዳቦ ቢገዛ፣ በቀጣይ ዓመት ግን የዳቦ ዋጋ ወደ 20 ብር ቢያድግ፣ በጂ.ዲ.ፒ. ውስጥ ከግለሰብ አንጻር የተመዘገበው ሙሉ መቶ ብር በአጠቃላይ በምርቶች ዋጋ የተገመተው እንጂ፣ ግለሰቡ ያጣቸውን ዳቦዎችና የኑሮ ደረጃውን አይደለም:: ይህም የጂ.ዲ.ፒ. መለኪያ በአገልግሎት ውድነት ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ የታጣን የኑሮ ደረጃን አያሳይም:: ሌላ ምሳሌ ብንጨምር፣ አንድ በሽተኛ በአንድ የኢኮኖሚ ዕድገት ልኬት ዓመት ወደ ሕክምና ቢሄድና የኢኮኖሚ ዕድገት ልኬቱ በጂ.ዲ.ፒ በተወሰደው ዓመት ላይ የሕክምና ወጪ ወድ ቢሆን፣ በጂ.ዲ.ፒ. መለኪያ /በጊዜው ያለውን የጥራት ደረጃና ውድነት ሳናይ/ ኢኮኖሚው አድጓል የሚል ስዕል ሊሰጠን ይችላል ወይም ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱን ያለ አቅሙ ያሳብጠዋል ማለት ነው::

ከወንጀልና ከሌሎች ማሕበራዊ ሁኔታዋች አንጻር «በተረጋጋና» «ባልተረጋጋ» ማሕበረሰብ ውስጥ የኢኮኖሚ ምርታማነት ልዩነት መኖሩ የማይታበይ ነው። ይህም ለተረጋጋ ማሕበረሰብ ማድላቱ እሙን ነው። ኢኮኖሚያዊ ምርታማነት ዕድገት በጂ.ዲ.ፒ ብቻ በሚመዘገብበት ወቅት፣ ላልተረጋጋ ማሕበረሰብ የተሻለ የኢኮኖሚ ዕድገት ሊሰጥ ይችላል። ይህም ሊሆን የሚችለው በጂ.ዲ.ፒ ምዝገባ ውስጥ ለእስረኞችና ለእስር ቤት ግንባታዎች የሚወጡ ወጪዎች ስለሚካተትና ይህም ወጪ ባልተረጋጋ ማሕበረሰብ ውስጥ ከፍ ያለ ስለሚሆን ነው።

በሌላ በኩል በአንድ የምርት ዓመት፣ በአንድ የአገራችን ክልል በጎርፍ ምክንያት ከፍተኛ ጥፋት ቢደርስና በቀጣይ ዓመታት የግንባታ ሰራዎች ቢካሄድ፣ ግንባታው በተደረገባቸው ዓመታት በሙሉ የጂ.ዲ.ፒ ዕድገት የሚመዘገብ ሲሆን፣ ነገር ግን አካባቢው ውስጥ የነበረው የኢኮኖሚ ዕድገት ነባራዊ ሁኔታ ከጥፋት በፊት እንደነበረው ላይሆን በሚችልበት ሁኔታ በጂ.ዲ.ፒ መለኪያ ኢኮኖሚው አድጓል ተብሎ ሊዘምር ይችላል። ይህም ማለት በመልሶ ማቋቋም ወቅት አካባቢዎ የነበረው ኢኮኖሚያዊ ነባራዊ ሁኔታ ትክክለኛውን ቅርፅ ሳይዝ ኢካኖሚው ገና መልሶ ግንባታ እያደረገ አድገዋል ሊያስብል ያስችላል።

ጂ.ዲ.ፒን እንደ ኢኮኖሚ ዕድገት መገለጫ እየተጠቀምን ባለንበት ወቅት እንኳን በተለያዩ የኢኮኖሚ መገለጫዎች መታጀብ ይኖርበታል። ይህም የጂ.ዲ.ፒውን ቅርጽ ሂደትና ቀጣይነት፣ ዕድገቱ በድህነት መገለጫዎች ላይ ያለውን ተፅዕኖ፣ በዕደገት ሂደት ስርጭት የተፈጠሩ የስራ ዕድሎች፣ የኢኮኖሚው ሞተር በሆነው በግብርናው ላይ የተለዩ ተጨባጭ እምርታዎች፣ እንዲሁም ዕድገት በተመዘገበበት ዓመት የመንግስት የበጀት ጉድለት (budget deficit)፣ የአገሪቱ የዕዳ መጠን፣ የመክፈል ግዴታ (dept service)፣ የውጪ ንግድ ሚዛን፣ በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ገንዘብ ነክ ያልሆኑ የኢኮኖሚ ዕድሎችና ተግዳሮት፣ የኃብት ፍሰት ሂደት እና አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ጤነኛነት መታየት ይኖርበታል። አለበለዚያ ጂ.ዲ.ፒ ብቻ ማለት ከሾላ በድፎ ተረት አያስመልጠንም። በዚሁ ሁሉ ሂደት ጂ.ዲ.ፒ በሚዘጋጅበት ወቅት ተግዳራትና አሉታዊ የሆኑ ጉዳዮች እንዳሉ ታሳቢ መሆን ይኖርበታል።

ኢትዮጵያውያን የተሸከምነው መገንባት ያለበት ኢኮኖሚ ነው። ይህም ግንባታ የኢኮኖሚ ዕድገት ለውጥ የሚጠይቅ ነው። ይህ የኢኮኖሚ ለውጥ በተወሰኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች በሚደረግ ግንባታ የሚቆም አይደለም። ከተማ ውስጥ ከሚበላው፣ ሊበላ ከሚያየውም፣ ከሚበላው አራትና አምስት እጥፊ የሆነ ሕዝብ ከፍተኛ ተጋላጭ በሆነ የግብርና መስክ የሚኖር ነው። ድህነታችን ከምንደብቀው በላይ ያሳብቅብናል፤ ስለዚህም ይህን መልክ ማስያዝ ይጠበቅብናል። በመሆኑም ዓመታዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ከድህነትና ድሀዎችን ከድህነታቸው እንዲላቀቁ ከሚያደርጓቸው ስትራቴጂዎች ጋር መፍትሄ ቢሆንም፣ ጂ.ዲ.ፒን እንደ ብቸኛ የእድገት መለኪያ መውሰድ ትንሽ ቅር ያሰኛል።

የኢኮኖሚ ዕድገት በአንድ ማታ ሚያልቅ ተግባርም አይደል። እንዲሁም የጥቂት ማሕበረሰብ ጥረት ውጤትም አይደለም፤ ሁሉም ማሕበረሰብ የኢኮኖሚ ጥረቶች ውጤት ነው። የኢኮኖሚ

ዕድገት ከማምረት ጋር እና የማምረት ጥርቅም ሂደት ጋር በሚገባ መያያዝ አለበት:: የኢኮኖሚን ዕድገት በከፍተኛ የብድር ዕዳ እንዲሁም የተፈጥሮ ኃብት ባሚጠጠ መልኩ ለመጪው ትውልድ በሚተው ዕዳ አማካኝነት ለማምጣት መሞከር የለበትም:: በእርግጥ ኢኮኖሚው መገንባት አለበት:: አልተጀመረም፣ አላዋጣኝም አካሄዱ፣ «ጤነኛ ነውም» «አይደለምም ልል አልችልም»:: ነገር ግን አጀንዳችን፣ «ቀጣይነት ያለው፣ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ /ያደረገ ዕድገት» አይደል?

ከላይ በጽሑፍ መግቢያ፣ ከጂ.ዲ.ፒ ጋር እንደአማራጭ መለኪያ ጂ.ኤን.ፒ ተጠቅሷል:: በተጨማሪ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች የጂ.ዲ.ፒ መለኪያ ካለው ክፍተት አንጻር፣ ሌሎች መለኪያዎችን ለማየት ሞክረዋል:: የሰው ዕድገት መለኪያ ኢንዲክስ (Human Development Index - HDI) በዚህ የዕድገት መለከያ ትንተና በአገሪቱ በአማካይ ይኖራል ተብሎ የሚገመተውን የዕደሜ ጣሪያ ልክንና የአገሪቷን የትምሕርት ደረጃ የሚያሳይ ነው:: ትክክለኛ የዕድገት ሂደት ጠቋሚዎችን (Genuine Progress Indicators) ይህ መለኪያ ብዙዎችን የጂ.ዲ.ፒ ክፍተቶች የመያዝ አቅም አለው፤ ይህም በጂ.ዲ.ፒ የተገኘን የስሌት ውጤትን፣ ለገቢ ስርጭት ውጤት እንዲስተከከልና በኢኮኖሚ ሂደት ውሰጥ በአገር ደረጃ የተገኙ አጠቃላይ ማሕበራዊ እስቴቶችን በመጨመርና በዚህም ዓመታዊ የዕድገት ግኘት ላይ በወንጀልና በአየር ብክለት የተከሰቱ ክፍተቶችን በማካተት የሚዘጋጅ ነው::

በዓለም ባንክ በኩል ደግሞ የኃብት ግምት (Wealth Estimates) የሚል መለኪያ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ይህም መለኪያ በገንዘብ በሚለኩ ኢኮኖሚያዊ እድገቶችን በገንዘብ ከማይለኩ ማለትም አገራዊ ኢንስቲቱሽኖች ዕድገትና ከሕብረተሰባዊ ኃብት ዕድገት ጋር የአካባቢ አየር ብክለትን በማቀናጀት ሊዘጋጅ የሚችል ነው:: ሌላው ደግሞ አረንጓዴ ጂ.ዲ.ፒ የሚባል ሲሆን ይህ በስተግሊዝ የተሞከረው ነው:: ይህ የኢኮኖሚ ዕድገት የጂ.ዲ.ፒ መለኪያ ለተፈጥሮ፣ ኃብት ዕልቀቶችና በአካባቢ አየር ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን ታሳቢ በማድረግ የሚዘጋጅ ነው::

በመሆኑም የዕድገታችን ውጤት ከማንም በላይ ሕዝብን የማዳንና በሕብረተሰብ ውስጥ እርካታን የመፍጠር ጥያቄ ነው:: በዚህ ሂደት የአገራችን የልማት አቅጣጫ ሂደት እያመጣ ያለውን ተጽዕኖ ታሳቢ ያደረገ፣ ከጂ.ዲ.ፒ ጋር የተጣመረ የኢኮኖሚ ዕድገት መለኪያ ማዘጋጀት፣ በአንድ ወገን «ቅንነት» ካለ በሌላ ወገን ደግሞ የተገኘውን ውጤት «ለክፋት» ሳይሆን ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ሂደቶች ከተጠቀምንበት ይቻላል::

# ራስ-ገዝ የፖለቲካ ማሕበረሰብና የልማት ችግሮች

**በፍቃዱ በቀለ(ዶ/ር)**

ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ዓለም አንድ በሆነችበት ወቅት፣ የራስ-ገዝ የፖለቲካ ማሕበረሰብ ውስጠ-መገለጫ ለብዙ በማደግ ላይ ለሚገኙ አገራ ራሱን የቻለ ጉዳይ አይመስልም:: በርካታ ታዳጊ አገራት - በተለይ ከሰሃራ በታች የሚገኙ የአፍሪካ አገራት - በውጭ እርዳታ ጥገኞች ናቸውና የሉዓላዊነት ጥያቄ እና በአንድ የድንበር ወሰኖች ውስጥ ያሉትን የማሕበራዊ መሰናሰሎች የመጠበቅ ጠቀሜታ መጠናት ያለበትና አወያይ ጉዳዮች አይደሉም:: በርካታ

ምሁራንና የሰሃራ በታች የአፍሪካ አገራት የፖለቲካ ሊቃን ስለእንዲያ አይነቱ ወሳኝ ጥያቄ ግንዛቤ ያላቸው አይመስልም:: በርካታ የአፍሪካ አገራት የተገበሯቸው ያለፉት ስድስት አስርት ዓመታት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ግሎባላይዜሽን፣ የሉዓላዊነትን ጥያቄ ጉዳይ ከብዙ መሪዎች አእምሮ በተግባር ሸርሽረዋል::

በምንገኝበት ውስብስብና አንድ መንደር በሆነች ዓለም፣ የብሔራዊ ማንነት እና የሉዓላዊነት ጉዳዮች ከመቸውም በበለጠ አንገብጋቢ ሆነዋል:: የኢትዮጵያን መንግስት ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ መሪዎች ከእንግዲህ የራሳቸውን ጉዳዮች በራሳቸው የሚያስተዳድሩ ባለመሆናቸው፣ ሌላው ቀርቶ ፊደል ያልቆጠሩ ሰዎች እንኳ እየኖርን ያለነው በሉዓላዊት አገር ውስጥ ነው ወይንስ አይደለም በማለት ራሳቸውን እስከመጠየቅ ደረጃ ደርሰዋል:: በኢትዮጵያ ያሉ ብዙ ሰዎች፣ የታቀደ ፓለቲካዊ ጥፋት የሥርዓቱ መግለጫ ከሆነ ለመጪው ትውልድ ምን ሊተርፍ ይችላል በማለት ራሳቸውን ይጠይቃሉ:: የሌሎች የአፍሪካ አገራትን ችግሮች ወደ ጐን ትተን በኢትዮጵያ፣ በኤርትራና በሶማሊያ ነፍሱ ከስጋው ያልተነጠለ መንግስት፣ ጠንካራ የኢኮኖሚ ሥርዓትና በሶስቱም አገራት ያሉ ሰዎችን በጠቅላላ ማስተናገድ የሚችል ማሕበራዊ ሥርዓት ወደ ፊት በተጠቀሱት አገራት እንዲኖራቸው በአገራቱ እየታዩ ያሉ ሁነቶች ጥልቅ ጥናቶችና አመክንዮዓዊ ምላሾች ያሻቸዋል:: የሶማሊያ ችግር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ አለውና፣ በሶማሊያ ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ ከሆነ እኛ ኢትዮጵያውያን በዝምታ ልናልፈው የምንችለው አይደለም:: ያ ማለት ግን የትኛውም የኢትዮጵያ መንግስት በሶማሊያ የውስጥ ጉዳዮች ጣልቃ መግባት አለበት ማለት አይደለም:: ላስገነዝብ የፈለኩት፣ የየትኛ-ውም ጐረቤት አገር ብጥብጥ ለአጠቃላዩ ክልል ጐጂ ውጤቶች ይኖረዋል የሚለውን መልዕክት ነው:: ዘላቂ ሰላም እስከሌለ ድረስ፣ የክልሉ ሕዝብ በድህነትና ርሃብ እንዲኖር መገደዱ የማይቀር ነው::

የሽብርተኝነትና ኢኮኖሚያዊ ግሎባላይዜሽን ጉዳዮች እና አሁን ደግሞ በስፋት መሬት በራስ ቁጥጥር ስር ማድረግ በርካታ አገራት የተከላካይነት አቋም እንዲይዙ እያደረጋቸው ይገኛ ል:: በተለይ ሽብርተኝነትን መዋጋት በሚል ስም በሶማሊያ እየተካሄደ ያለው ጦርነት፣ የንጹን መፈናቀል እና በኢትዮጵያና በኤርትራ ያለው ጭጋጋማ ሁኔታ አስጊ የሆነና በርካታ አገራት ክልሉን ወደ ቋሚ የጦርነት አውድማ ለመለወጥ እንዳሳቡ ሊያደርጋቸው የሚችል ነው:: እናም፣ ትክክለኛና ዘላቂ መፍትሄ መስጠት እንዲቻለን የጦርነት፣ ርሃብና የኋላቀር-እድገት መንስኤዎችን ማጥናት የእኛው ግዴታ ነው:: በኢትዮጵያና ኤርትራ እንደምንመለከተው፣ ፖለቲካዊ ጥፋት በማህበረሰባች ውስጥ ስር የሰደደ ሲሆኑ መንስዔውም ያልተፈቱና የተከማቹ ችግሮች ናቸው:: የተቀናጁና በአግባቡ ሊተገበሩ የሚችሉ ኢኮኖሚያዊ መዋቅሮችና ማሕበራዊ ሥርዓት በሌሉባቸው ማሕበረሰቦች ውስጥ፣ እንደዛ ያለ ሁኔታ ለፖለቲካዊ ጥፋት የተመቸ ነው:: ፖለቲካዊ አለመረጋጋት በተንሰራፋባቸው፣ ፖለቲካዊና ማሕበራዊ ንቃት ባልዳበረባቸው ክልሎች ወይም አገራት ውስጥ፣ የውጭ ኃይሎች የመሰል አገራትን ደካማ ሁኔታ ተጠቅመው መሪዎቻቸው ወደ ጦርነት እንዲዘፈቁ የማወናበድ ሙከራ ያደርጋሉ:: ውጤቱ የንጹሀን ዜጐች መፈናቀልና የሰውና የተፈጥሮ ኃብቶች ብክነት ነው:: ይህን በተመለከተ በሶማሊያ እየተሰተዋለ ያለው እና በሶማሊያ የውስጥ ጉዳዮች ኢትዮጵያ ጣልቃ መግባቷ እና የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት በክልሉ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በጠቅላላ መረጋጋት እንዳይኖራቸው የሚያደርጋቸው ነው:: ሁኔታውን በቅርበት ካጠናነው፣ በክልሉ እየተሄደ ያለው ጦርነት የእጅ አዙር ጦርነት ነው:: የእነዚህ አገራት ሕዝብ

ማሕበሪዊ ታሪክ የማይገባቸው፣ ሁሉም ሰዎች በነፃነት የፈጠራ ኃይላቸውን እንዲጠቀሙ የሚያስችላቸውን ሥርዓት መፍጠር የማይቻላቸው ንቃት የጐደላቸው መሪዎቻቸው ተጠያቂዎች ናቸው::

ክልል የተጋፈጠውን ውስብስብ ሁኔታ በመገንዘብ የንቃት ችግርን ከኢኮኖሚ ልማት ጉዳይ ጋር ማያያዝ አለብን፤ ይህንንም ከአንድ የፖለቲካ ማሕበረሰብ መፈጠር ጥያቄ ጋር ማቆራኘት ይጠበቅብናል:: ለተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ልማትና አገር ግንባታ እውነተኛው መሰረት ማሕበራዊ፣ ባሕላዊና ፖለቲካዊ ንቃት ብቻ ነው የሚል አቋም አለኝ:: ብሔራዊ ንቃትና ስለታሪካዊና ማሕበራዊ ሂደቶች ጥልቅ ግንዛቤ በሌለበት ሁኔታ፣ አንድም አገር ዘላቂ የፖለቲካ ማሕበረሰብ መገንባት አይቻለውም::

እስኪ የተወሰኑ ጥያቄዎችን ልጠይቅ:- ከአእምሮ ተሳትፎ ውጪ ሊደረግ የሚችል ነገር አለ? በፈለግነውና ባቀድነው መንገድ ነገሮችን እንድናደርግ የሚመራና የሚቆጣጠር አእምሮ ነው ወይንስ ሌላ ነገር? አመዛዛኝ ወይም በተቃራኒው እንድንሆን ምን አይነት ነገሮች ናቸው አእምሮአችንን የሚቀርፁ? አእምሮአችንን በመቅረጽ ረገድ ባሕል ያለውን ድርሻ እንዴት እንመለከተዋለን? እንደሚመስለኝ፣ በአንድ የተለየ የፖለቲካ ማሕበረሰብ ውስጥ ባለን ግንኙነት የንቃት ድርሻን መገንዘብ የምንፈልግ ከሆነ ማንሳት የሚጠበቁብን የተወሰኑት ጥያቄዎች እነዚህ ይመስሉኛል::

በምሁራን አካባቢ፣ በተለይ በኢትዮጵያውያን መካከል፣ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እጦት ለሕዝባችን ጉስቁልና መንስዔ ነው የሚል የጋራ እምነት አለ:: የተወሰንነው መሪዎቻችን በተፈጥሮአቸው ጨካኞችና በአገራችን በተንሰራፉ ባሕላዊ ሁኔታዎች ያልተቀረጹ ናቸው ብለን እናስብ ይሆናል:: ወታደራዊ መሪዎቹ ያደጉባቸውን ማሕበራዊና ባሕላዊ ሁኔታዎች ከግንዛቤ ሳንከት ወታደራዊ ሥርዓቱ ጨካኝ ነው ብለን እንወነጅለዋለን:: ወታደራዊ መሪዎቹ በኢትዮጵያ ውስጥ *ሶሻሊስቶች* ከመሆናቸው አስቀድሞ፣ *ከሶሻሊስት ብሎክ* አገራት ውጭ በፈለቀ ወታደራዊ ርዕዮተ-ዓለም እንደሰለጠኑ እንዘነጋዋለን:: ቀደምት ማሕበራዊ መስተጋብሮቻቸውን ለመረዳት ሙከራ ሳይደረግ፣ የወቅቱ የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ አምባገነናዊና በከፋፍለህ ግዛ አካሄዱ ይወነጀላል:: እንደዚያ ያለ ቀላል አካሄድ፣ አገራችን ያለባትን ችግር የሚፈታ አይደለም:: ልክ ከምንም ነገር ጋር ንኪኪ የሌለው ፖለቲካዊ ችግር፣ ለመሰል ውስብስብ ችግሮችና ኢ-አመክንዮዓዊ ባህሪ ምላሹ የሚገኘው ከፖለቲካ ሳይንስ ምልከታ አይደለም:: በሌላ አገላለጽ እንደምንመኘው የሆነ አይነት *«ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ»* ቢኖረን እንኳን የኋላ-ቀር እድገትና የድህነት ችግር በቀላሉ የሚቀረፉ አይሆኑም:: ከጦርነትና ርሃብ ጋርም እውነታው ተመሳሳይ ነው:: ግልጽ ምላሽ የምንሻ ከሆነ ከተለመደው ፖለቲካና ከተገመተው ዴሞክራሲያዊ አገዛዞች በላቀ መንዝ አለብን::

ካለምክንያት አይደለም ከዛሬ 3ሺህ ዓመታት ጀምሮ ፈላስፋዎችና *ሳይኮሎጂስቶች* የሰብዓዊ ፍጡራንን ስሜት፣ አስተሳሰብና የባህሪ አካሄድ በተመለከተ አእምሮ ያለውን ድርሻ ለመገንዘብ በመመራመር ላይ የሚገኙት:: የአእምሮን አስተዋጽኦ እና የአንዲት አገር ማሕበራዊ ሁኔታ ሳይጤን፣ የፖለቲካ መሪዎችን ተፈጥሮ (ባህሪ) አንድም ሰው ማወቅ እንደማይቻለው በትክክል የተገነዘቡት እውነታ ነው:: ከቅድመ ሶቅራጠስያዊ ፈላስፋዎች እስከ ሶቅራጠስ፣ ፕሌቶና እስከ 17ኛው ክ/ዘመን ድረስ፣ ፈላስፋዎች በዋናነት የተጠመዱት የአእምሮን የተለያዩ ክፍሎች መመርመር ነበር:: ሰብዓዊ ፍጡራን ከእንስሳት የተለዩ በመሆናቸው ምክንያት፣ አመዛዝነው

ማሰብና አካባቢያቸውን መለወጥ ይቻላቸዋል። የተወሰኑ፣ ጥያቄ ለማንሳትና አመክንዬ ለተለበሰ ባህሪ ይህን ከፈጣሪ የተሰጠ ኃይልን የመጠቀም ብቃት የላቸውም። በስሜትና በራሳቸው ፍቃድ ተመርተው የራሳቸውን አገር ያወድማሉ። ፍሩድ እንዳስተማረን፣ ለባህሪዎቻችን መንስዔ የሆኑ ሶስት የአእምሮ ክፍሎች አሉ። የመጀመሪያው በጣም ዝቅተኛ የማመዛዘን ደረጃ ያለው የአእምሮ ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ሰብዓዊ ፍጡራን ሁሉም አይነቶች ምኞቶችና ያልዳበሩ አስተሳሰቦች አሏቸው። ምንም አይነት አመክንዩዓዊ ሥርዓት የሌለውና በቀላል የራስ ፍላጐቶች የሚመራ ክፍል ነው። ሁለተኛው፣ የግለሰብን ማንነት የሚቀርጸውና የሚገልጸው ክፍል ነው። አንዳንድ ሰዎች ባደጉባቸው አኳኋኖችና የማሕበራዊ መስተጋብር ሁኔታዎች ሊቀረጽ የሚችል ነው። ይህን የአእምሮ ክፍል በመቅረጽ ረገድ የመምህራንና የወላጆች ድርሻ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በጊዜና በየትኛውም አይነት አዎንታዊ ለውጦች አማካኝነት ይህ ክፍል በየጊዜው የበለጠ በማሕበረሰቡ እየተገራ የሚሄድና ንቁ የሚሆን ነው። አስተሳሰቡና ባህሪው በአንዲት አገር በይበልጥ በሚስተዋል ማሕበራዊ ሁኔትዎች ቁጥጥር ይደረግበታል። አመዛዛኝ ባልሆነው ክፍልና በማሕበራዊ ሁነቶች በተገራው ክፍል መካከል ቋሚ ፍልምያ አለ። ይህን ጊዜ ሶስተኛው ክፍል የአስታራቂነትን ሚና በመውሰድ ፍልምያውን ሚዛናዊ አድርጎ ለመጠበቅ ይሞክራል። እንደ ፍሩድ፣ ሶስተኛው ክፍል ለአመዛዛኝ የሰው ልጅ አስተሳሰብ፣ እቅድ እና ውሳኔ ምክንያት የሆነ ነው። ችግሩ ምንድነው በተወሰኑ ሁኔታዎች አመዛዛኝ ያልሆነው የአእምሮ ክፍል በይበልጥ የበላይ ይሆንና ያ አመክንዮ ያልተላበሰው ክፍል የተወሰኑ ቡድኖችን የሚገዛ ባህሪ መሆኑ ነው። አንዳንድ መሪዎች በሥልጡን ሁኔታዎች ቢያድጉም፣ አስተሳሰባቸውና ተግባራቸው አመዛዛኝነት እንደሌለው በታሪክ ተመልክተናል። መጀመሪያውኑ የሰረፀን የጥላቻና የወረራነት አመለካከትን ለመለወጥ ትምህርት መፍሄ እንደማይሆን ሂትለር ቅልብጭ ያለ ምሳሌ ነው። በሺህዎች የሚቆጠሩ ሳይንቲስቶች፣ ፈላስፋዎች፣ ሙዚቀኞችና ጥበበኞች እንደእውር ሂትለርት ተከትለውታል፤ የሂትለርን አይሁድያውያንንና የሌሎች አናሳ ቡድኖችን የማጥፋት የናዚ ፐትፓጋዳን አምነው ተቀብለዋል።

ሰብዓዊ ፍጡራን ንቁና ሙሉዕ ናቸው። በራሳቸው የተሟሉ፣ ጥገኛ ያልሆኑና በራሳቸው የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ውስጣዊ ኃይል አላቸው። እጅግ አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ሊጐዱ ይችላሉ። ለመጠየቅና ለማመዛዘን ካልተቻላቸው የኃሰተኛ ርዕዮተ-ዓለም ተጠቂዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በአብዛኛው፣ ሰብዓዊ ፍጡራን ራሱን የቻለ አካል ሆነው ለመለወጥና በንቃት እርምጃ ለመውሰድ የውስጥ ኃይላቸውን አይጠቀሙም። በሀሰተኛ ትምህርትና ርዕዮተ-ዓለም እያንዳንድ ያለው የውስጥ ኃይል ይሸረሸራል። በዚህም የሀሰተኛ አስተሳሰብ /ርዕዮተ-ዓለም ሰለባ በመሆን አእምሮአቸው በጥላቻና ቁጣ ይሞላል። ከዚያ በኋላ ስለሚያደርጉት አንዳች የሚያውቁት አይኖርም። ቢማሩ እንኳ በጥልቀት የሚያመዛዝኑ አይሆኑም። ተጠራጣሪ በመሆን ትችት ለመቀበል ዝግጁ አይሆኑም።

በማሕበረሰባችን ኃይል ያልተቀላቀለበት ለውጥ ማምጫ መንገዶች ቢኖሩም፣ በነፃነት ስም መሳሪያ የሚያነሱ ስለምን ሆኑ? አብዩተኞች የተባሉት አመክንዮ በሌለው መልኩ እንዲንቀሳቀሱ በመቅረፅ ረገድ ርዕዮተ-ዓለም የራሱን ደርሻ ተጫውቷል ብለን እንደለመድነው ልናሳብብ ይቻለናል? በአገራችንና ሌላው ቀርቶ በቀደምት በርካታ ሶሻሊስት አገራት ውስጥ እንደርዕዮተ-ዓለም ሶሻሊዝም በእነዚያ አገራት በጠቅላላ ለተፈጠረው ተጠያቂ ተደርጓል። ባለፉት 5 አስርት

ዓመታት አሜሪካንን ጨምሮ በበርካታ የምዕራብ አገራት የታየው አንፃራዊ ብልጽግና አእምሮአችንን አሳውሮታል:: በአፍሪካና በሌሎች *የሶስተኛው ዓለም አገራት* ውስጥ በእነዚህ ሰልጥነዋል በተባሉት አገራት የተፈፀሙ ጭፍጨፋዎችን ሁላችንም ዘንግተነዋል:: የመጀመሪያውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች፣ ቃሉ ባለው እውነተኛ ትርጉም እንደሚባለው በትክክል የዓለም ጦርነቶች ባይሆኑም፣ የተካሄዱት በበለፀገችው አውሮፓ ውስጥ ነው:: የራስን አጀንዳ ለመሸፋፈን ርዕዮተ-ዓለምን ምክንያት ማድረግ የተደለመ ሆኗል::

ርዕዮተ-ዓለም የሰብዓዊ ፍጡርን አእምሮ በመቅረፅ የራሱ ድርሻ ቢኖረውም፣ ከሶሻሊስታዊ ርዕዮተ-ዓለም ጋር በ20ና አካባቢ የእድሜ ክልላቸው ወቅት ትውውቅ የነበራቸው ሰዎች በአእምሮአቸው የሰረፀ የተለየ ታሪካዊ ዳራ ነበራቸው:: በዚህ ጉዳይ ላይ የተማሪው ንቅናቄ ላደረሰው ጉዳት እና የአሁኑን መንግስት ጨምሮ ወታደራዊው አገዛዝ በኢትዮጵያ ላይ ላደረሱት ጉዳት ማርክሲዝምን ተጠያቂ አላደረገም:: ያደግንበት ባህላዊ አግባብ፣ ማለትም የፊውዳል አመለካከት፣ ለግትሩና ኢ-ሰብዓዊ ባህሪያችን መንስኤ ሆኗል የሚል አቋም ነው ያለኝ:: ያደግንበት የትምህርት ሥርዓት ፀረ-ብሄርተኛና ቀልባሾች የሚያደርገን ነው:: የተማሪዎች ንቅናቄ መሪዎች በመፈክሮቻቸው ምንም ጽፈው የነበረ ቢሆን እንኳ፣ በተግባር ለፀረ-ኢትዮጵያ አመለካከት የተመቸ ሁኔታን ፈጥረዋል:: አሳሳቢው በዚህ የጉዳዩ ውስጥ ምክንያት አይደለም:: በአብዮት ስም የተፈፀመው ደም አፋሳሽ ጦርነት ብዙ ሰዎችን የሚያስጨንቅ ነው:: የልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ሞት ከአእምሮአቸው ሁሉንም ደስታዎች ሙልጭ አድርጐ አስወግዷል - በማይሽር ሀዘን እንዲኖሩም ሆነዋል:: በሌላ ጐን ሁሉም የነፃነት ተፋላሚዎች የተባሉ ብሄር ላይ የተመሰረቱ፣ በአእምሮአቸው አንድ ነገር ነበራቸው:: በነፃነት ስም ብረት ያነሱ  ሁሉንም ድርጅቶች ከወሰድን፣ አላማቸው የነበረውና አሁንም ያልተለወጠው ኢትዮጵያን መበታተን ነበር:: ካለጥርጥር የውጭ ኃይሎች ሰለባዎች ሆነው ነበር:: እንዲሁም የራሳቸውን ሕዝብ እንዲያጠፉ የተሳሳተ አካሄድ እንዲከተሉ ተደርገውም ነበር:: በተመሳሳይ ንቃት ያልነበራቸው እርምጃዎች ሰለባዎች ናቸው:: ጥያቄ ማሳት አልተቻላቸውም ወይም አስተሳሰባቸውንና እርምጃቸውን ለማረጋገጥ እንደ ጤነኛ ሰው ለመሆንም አልሞከሩም:: ፍሩድ እንዳለው፣ ሥልጣን ለመያዝና ፍላጐታቸውን ለመፈፀም በነበራቸው ኢ-አመክንዮዓዊ እቅዶቻቸው ነበር የተመሩት:: ለአዳዲስ ሃሳቦች አእምሮአቸው ዝግ ይሆናል:: የሰረፀ ሀሳብ አስቀድመው የያዙ በመሆናቸው ከህዝብ ራሳቸውን ያርቃሉ:: የራስ መተማመን አለመኖር ከሃዲዎች ያደርጋቸዋል፤ እናት አገራቸውን ለመሸጥም የማያንገራግሩ ይሆናሉ:: መሰል ሰዎች አንድ ግለሰብ ማህበረሰቡን ለመቅረጽ ያለውን ድርሻ፣ በግለሰቡና በአጠቃላይ በማህበረሰቡ መካከል ያለው መስተጋብር አይገባቸውም::  እንደ ማህበረሰብ፣ የግለሰብ ነፃነት፣ ተጨባጭ የኢኮኖሚ እድገት እና ሉዓላዊነት ያሉ ግንዛቤዎች የአእምሮአቸው አካል አይደሉም:: ማህበረሰብ ጠንካራ ባልሆነ መልኩ የተደራጀና ሁሉም በመምጣት እንደፍላጐቱ/ቷ የሚኖርበት ነው ብለው ያስባሉ:: የትኛውም አገር እንደዚያ ባለ የማያገናዝቡ አካለት በምትተደዳደርበት ወቅትና የተማሩ የተባሉ በሺህዎች ያሏት ከሆነ፣ አገሪቱ ዜጐች እውነተኛ ነፃነታቸውን በነፃነት የሚተገብሩባት ስፍራ አትሆንም::

አሁን ደግሞ ባህል አእምሮን በመቅረጽ ረገድ ወዳለው ድርሻ እንመለስ:: በመጀመሪያ የህፃንነት የእድገት ደረጃ ላይ፣ አግባብነት ያለው ትምህርት በህፃን የአስተሳሰብ ብቃትና አተገባበር ላይ አዎንታዊ ውጤት እንዳለው በአግባቡ የተመረመረና የተጠና ነው:: በተመሳሳይ ጠቅላላው

ሁኔታ፣ አካባቢ፣ የትምህረት ሥርዓት፣ የወላጆችና መምህራን ድርሻ ጐረቤቶችና ሌሎች ተፅዕኖ አሳዳሪ አካላት፣ እያደገ ያለ ህፃን አእምሮን በመቅረጽ ረገድ የራሳቸው ድረሻ አላቸው:: የአንድ ሰው ሰብዓዊነት ለሌሎችና ለአገርና ለመላ አካባቢው ያለው ፍቅር ከህፃንነት ጀምሮ ተኮትኩቶ ባደገበት የትምህርት ሥርዓት የሚወሰን ነው:: በተለይ የቤተሰብ ፍቅር የአንድን ህፃን ባህሪ በመቅረጽ ወሳኝ ነው:: አንድ ሰው እድሜው ገፍቶ ከበሰለ በኋላ ያመለጠን እድል መልሶ ማግኘት የሚቻል አይደለም:: በአጋጣሚ ወይም በተለይ ቴራፒ የአንደን ግለሰብ ባህሪ መቅረጽ ሊቻል ይችል ይሆናል::

ለማስረገጥ ወደ አገራችን ሲመጣ፣ ስለምን ኢትዮጵያ እንዲያ ያሉ የተጨመላለቁ ዓመታት እንዲያጋጥማት ሆነ? ስለምን ህዝቧ በኢትዮጵያ ውስጥ በተወለዱ፣ ባደጉና ትምህርት ቤት በሄዱ ኃይሎች ባለፉት አራት አስርት ዓመታት በጠቅላላ ተሰቃዩ? ትምህርት ቤት መሄድ አግባብነት ያለው ትምህርት በመቅሰም መልካም ባህሪ ለማግኘትና ሰብዓዊነት ለመላበስ ሆኖ ሳለ፣ ስለምን እነዚህ ልጆች ገዳይ ሆኑ? ኢትዮጵያን ለመበታተን እየታገሉ ላሉ የውጭ ኃይሎች የተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ለእነርሱ እጅ እንዲሆኑ ምን አነሳሳቸው? ሁሉም አገራትና ባህሎች አነሰም በዛ ተመሳይ መንገድ ተከትለዋል:: የአገራትን አመሰራረት ስናጠናና ስንገነዘብ፣ የአንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ ግንባታ አስፈላጊነት ይገባናል::

አገራችን የተለየች የሚያደርጋት ያልተደመደመው የአገር ግንባታና የመሪዎቻችን ኢ-አመክንዮ ድርሻና ባለፉት ሺህ ዓመታት ውስጥ አገራችን ያስተናገደቻቸው የተለዩ ሁኔታዎች ናቸው:: ሁሉም እነዚህ መንስኤዎችና ዘመናዊ የትምህርት ሥርዓት ተብዬው ለተሳሳተ አስተሳሰብና አተገባበር ተጠያቂዎች ናቸው:: ይህን በተመለከተ ለአገራችን ያለን ፍቅርና ንቃት ካደግንበት አጠቃላይ ህብረተሰብ ሂደት ሊነጠል የሚችል አይደለም:: ጥያቄው ያለንበትን መጥፎ ሁኔታዎች እንዴት መለወጥ ይቻለናል? ዴሞክራሲያዊና ጠንካራ ኢትዮጵያን ለመገንባት አዎንታዊ ድርሻ ለማበርከትና አመዛዛኝ እርምጃ ለመውሰድ እንዴት ይቻለናል? ላለፉት አንድ ሺህ ወይም አካባቢ ዓመታት በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ትመራ የነበረው በአማራዎችና በትግሬዎች ነበር ብለው የተወሰኑ ቡድኖች አሁንም እያሰቡ በሚገኙበት ወቅት፣ እንዴት አድርገን ነው ጉዳዩ እንደዛ እንዳልነበርና ሁኔታው ከተለየ ጎን በጥልቀት መጠናት ያለበት ነው ብለን ልናሳምናቸው የሚቻለን? የዘውግ- ብሄርተኝነት ጉዳይ የህዝብ ችግር አይዳለም:: የራሱን ድርሻ መገንዘብ ያልተቻለውና በበታችነት ስሜት እየማቀቀ የሚገኘው ምሁራን ችግር ነው:: በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ራሱን ከባህሉና ከአገሩ ጋር የመግለጽ አንዳች ችግር የለበትም:: ህዝቡ አዳዲስ ነገሮችን ለማወቅና ራሱን ለመለወጥ ዝግጁ ነው::

***(የዶ/ር ፍቃዱ በቀለ ጽሁፍ ክፍል ሁለት ሳምንት ይቀጥላል)***

# ተጠየቅ

**<u>ከአዘጋጁ</u>:- አቶ አበራ ዳስሎ በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ላይ የጻፉትን አስመልክቶ የውሀ ሀብት ሚኒስቴር ቅሬታ አቅርቧል:: የሚኒስትር መስሪያቤቱ ቅሬታ ከአቶ አበራ ጽሁፍ ቀጥሎ ተስተናግዷል**

# ለሐይድሮሎጂ መምሪያው ችግሮች መንስኤዎች እና የመፍትሔ ሀሳቦች

## የውሃ ሀብት ሚኒስቴር ማኔጅመንት ሲፈተሽ

የውሃ ሀብት ሚኒስቴርን ማኔጅመንት ለሶስት ተከታታይ ሳምንታት ሲፈትሹ የቆዩት የሐይድሮሎጂ ባሙያው አቶ አበራ ዳስሎ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሐይድሮሎጂ መምሪያው ችግሮች መንስኤ ናቸው ያልዋቸውን ጉዳዮችና የራሳቸውን መፍትሔ ሀሳቦች ያስነብቡናል

**በአበራ ዳለሎ**

ባለፉት ሣምንታት ለመዘርዘር የሞከርኩት በውሃ ሀብት ሚኒስቴር የሐይድሮሎጂ መምሪያ ትኩረት ያጣ ስለመሆኑና በውስጡ ያሉ የአሰራር እና የአፈፃፀም ብልሽቶች፣ እንዲሁም ያጋጠሙት ችግሮች ለዓይነት ያህል የቀረቡ እንጂ፤ ውስጡ ሲገባ ከዚህም በለይ ናቸው:: መምሪያውን ለነዚህ ሁሉ ችግሮች የዳረጉት መንስኤዎች ምንድን ናቸው? ሌሎች የመምሪያው ወይም የመ/ቤቱ ባልደረቦች የራሳቸውን ምክንያቶች ሊደረድሩ ይችላል:: በእኔ እይታ ግን የሚከተሉትን በዋነኛነት አስቀምጣለሁ::

**1.** የውሃው ዘርፍ የተበታተኑ ባለስልጣን መ/ቤቶች (ማለትም በሸለቆዎች ልማት ጥናት ባለስልጣን፣ የተፈጥሮና የአካባቢ ጥበቃ ልማት ባለሥልጣን፣ የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ባለስልጣን፣ ብሔራዊ ሜትሮሎጂ አገልግሎት ባለስልጣን፣ የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ባለስልጣን፣ የውሃ ሥራዎች ዲዛይን ቁጥጥር ድርጅት) የአደረጃጀት መዋቅር ሲሰራ አንዳንዶቹ ተደባልቀውና በአንድ ላይ ተጠቃለው የሚኒስቴር መ/ቤት ሲሆኑ በተፈፀመው የመዋቅር ለውጥና የሰው ኃይል ድልደላ በድጋፍ ሰጪነት መ/ቤቱን የሚያሽከረክሩትን የኃላፊነት ቦታዎች የሐይደሮሎጂ መምሪያ የነበረበት /የመጣበት/ የሸለቆዎች ልማት ጥናት ባለስልጣን ድጋፍ ሰጪ ኃለፊዎች መጋራት ዕድል አላገኙም::

ከሌሎች የመጡት የበላይነትን ይዘው ስለነበር እነዚህ ደግሞ የሐይድሮሎጂን ሚና አያውቁትም፣ በመሆኑም በቀጣዩቹ የሥራ ዓመታትና እስከዛሬም ድረስ ትኩረት አልሰጡትም:: በአስረጂዎች ለማስረዳት:-

**ሀ)** መምሪያው ከነበረው የሰው ኃይል አንዳንድ ቴክኒሺያኖችን ሊገለጽ በማይችል ምክንያት በመዋቅር ሰበብ በተኗቸው፣ ጥቂት ዓመታት ቆይተው ደግሞ ሥራው ቀጥ ሲልባቸው እነዚያኑ የተበተኑትን አድራሻቸውን እያፈላለጉ መለሷቸው:: የየራሳቸው ደካማ ጎን ቢኖራቸውም እስከዛሬ የሥራው የጀርባ አጥንት ሆነው በየቀጠናው ጽ/ቤት በማንቀሳቀስ ላይ የሚገኙት እነሱ ናቸው:: ብተናው የተፈፀመው ከግንዛቤ ጉደሉት ይመስለኛል::

**ለ)** የቀጠና ጽ/ቤት የሚባል ነገር አናውቅም፣ የቀጠና ጽ/ቤቶች እድሳት አስተዋሽ ማጣት - የሠራተኞች ደሞዝ ለኪ. ማጣት ወዘተ. ከግንዛቤ ጉድለት የመጡ ይመስሉኛል::

**ሐ)** የመስክ ጥናት ጣቢያዎች የማቋቋምና ጥገና የሚያስፈልጋቸውን የጥናት ጣቢያዎች ፈጥኖ በመድረስ የጥገና ተግባር የሚያከናውን የሰለጠነ ግብረ-ኃይል «skilled Laborers» የሚገኙበት የሐይድሮሎጂ ዎርክሾፕ ሙሉ በሙሉ በመዋቅሩ ሰበብ ተዘግቶ ግብረ-ኃይሉም ተበተነ:: የዚህን ግብረ-ኃይል አባላት በ«ሀ» ስር እንደተገለፀው ዓይነት መልሶ የመጥራት ሙከራ አልተሳካም:: የኋላ ኋላ መምሪያው ቢቸግረው ተመሳሳይ የሐይድሮሎጂ ዎርክሾፕ ለማደራጀት ጥረት እያደረገ ይገኛል::

የደለል ውሃ ናሙናዎች ያስመረምርበት የነበረው የተደራጀ ጠንካራ የውሃ ምርምር ላቦራቶሪም ለውሃ ሥራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት በመተላለፍ የሐይድሮሎጂ መምሪያ የራሱን ላቦራቶሪ ለማደራጀት ጥረት እያደረገ ይገኛል:: ይህ ሁሉ የተፈፀመው ከግንዛቤ ጉድለት ይመስለኛል::

**መ)** እስከዛሬ የተዘረዘሩት ለክፍሉ ሥራ ድጋፎች መንፈግ እና ትኩረት ማጣት የመጣው ስለመምሪያው ታሪካዊ አመጣጥ፣ አፈፃፀም፣ ነባር አደረጃጀቱንና የሥራ ባህሉን የማያውቁ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች በኃላፊነት ቦታዎች በመመደባቸው የግንዛቤ ጉደሉት ያመጣው ጣጣ እንጂ በማወቅ ሆን ተብሎ የተፈፀመ ተንኮል ነው ብዬ አላምንም::

<u>**ለምሳሌ:-**</u> የውሃ ከፍታ መዝጋቢዎችን (ኦብዘርቨሮችን) እንደጠቃሚ መረጃ ሰብሳቢ ሠራተኞች አለመመልከትና ለችግራቸው አለመድረስ፤ ይባስ ብሎም ክፍያቸውን ሲነጠቁ አግባብ ያለው ፍትህ አለመስጠትና የሚገርመው ደግሞ ከ40 እና 50 ዓመት በላይ ለሀገሪቱ ጠቃሚ መረጃ ሲመዘግቡ ቆይተው ጣቢያው ሲዘጋ «እግዜር ይስጥልኝ» ብሎ ከማሰናበት ፍ/ቤት መገተር (ለአስረጂነት- ከ1958 እስከ ዛሬ ድረስ ሲመዘግብ የኖራውን አቶ ዱጋሳ ኤጀታ፣ የነሺ ወንዝ ፊንጫ አካባቢ የሚገኝ ይመለከቷል::)፤

- መምሪያው የሚያዝባቸውን 17 ያህል መኪኖች ነጥቆ ለሌሎች ፕሮጀክቶች ማስማራት፣ መምሪያው በበጀቱ የገዛቸውን መለዋወጫዎቻቸውን ለሌሎች አገልግሎት ማዋል፤
- የክፍሉን ሙያተኞች በተብብር ሽፋን ለሌሎች ክፍሎች አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣ በዚያው ማስቀረት... ተዘርዝሮ አያልቅም::

**2.** ከተለያዩ ክፍሎች የሚመጣውን ጥቃትና የበላይ አካላትን ተጋፍጠው ሊያሳምኑ የሚችሉ ብቃት ያላቸው ኃለፊዎች አለመመደብ የመምሪያው ህልውና ፈተና ላይ እንዲወድቅ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ነው::

**3.** ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 2 የተገለፀው ቢኖርም በዜግነታችን የመምሪያው ዕድገትና ውድቀት ይመለከተናል ብለው የሚጋፈጡ ሠራተኞች አለመኖር፣ ብልጣ ብልጦች ሲጠቀሙበት የዋሓኑ ሲጎዱበት አይተው እንዳላዩ በዝምታ ማለፍን የመረጡ እና ድርሻቸውን በተለያየ መንገድ ተጠቅመው ዞር ለማለት ያደፈጡ መብዛታቸው ሌላው ምክንያት ነው::

**4.** በመምሪያው ኃላፊነት ቦታዎች ላይ የሚቀመጡት ከመምሪያው ውጭ በሆኑ ተደራቢ ሥራዎች እንዲጠመዱ መደረጋቸው ስለመምሪያው እቅድ፣ በጀት፣ የመርሀ ግብር አፈፃፀም፣ የኢኒስፔክሺን ሥራዎች ወዘተ. ለማከናወን አለመቻል ሌላው የችግሩ መንስኤ ነው::

**5.** ለመምሪያው መዳከም ሥውር የውጭ እጅ አለበት የሚል ጥርጣሬ አለኝ፣ ይኸውም ከአባይና ከገባር ወንዞች ተጋሪ አገሮች ጋር በተያያዘ የቴክኒክ ድጋፍ ተረድኦ፣ የአህጉራዊ ቀጠና ስብሰባዎች፣ ዎርክሾፖች ወዘተ. እየተባለ የመምሪያው ሥራ ትኩረት ማጣት ከመንስኤዎቹ መካከል ነው::

**6.** የመዋቅሩ፣ ሥራ ላይ አለመዋል፣ የሰው ኃይል አለመሟላት፣ ያለውም የሰው ኃይል እንክብካቤ ማጣትና የአያያዝ ጉደለት ሌላው የመምሪያው መዳከም ምክንያት ነው::

7. የበላይ አካላት ከመምሪያው ሙያተኞች ጋር ያለ ግንኙነት የላላ መሆንና መምሪያው ያለበት ችግር ጥቆማ ሲደርሳቸው እንኳን በቁርጠኝነት መፍተሔ ለማስገኘት አለመንቀሳቀስ (የቀድሞዎቹ እስከ መስክ ሥራ ነጥብ ጣቢያዎች ድረስ ተገኝተው ሙያተኛውን ያበረታቱ ነበር:: የዛሬዎቹ ግን እንኳን የበላይ ኃለፊዎችና የመምሪያው ኃላፊዎችም የመስክ ሥራው ነጥብ ጣቢያ ቀርቶ፣ የቀጠና ጽ/ቤቶቹን አይተው አያውቁም) ለመምሪየው ውድቀት ሌላው ምክንያት ነው::

**8.** በመምሪያወ ላይ ሚተገበሩ ጎጂ አፈፃፀሞች፤ **ለምሳሌ፡-** የመመሪያው መኪኖችና መለዋወጫዎቻቸውን ከመምሪያው እዝ ውጭ ማድረግ፤ የኃላፊዎች በሠራተኞቻቸው ላይ መሸፈጥና ማጉላላት፤ ለመምሪያው ሥራ የተፈቀደውን በጀት፣ የመኪኖች ነዳጅ፣ የውሎ አበል ወዘተ. ለሌሎች ክፈሎች ጉዳይ መዋል፤ ለመምሪያው ባለሙያ ከገበያ ላይ ከመቅጠር ይልቅ በሌሎች ክፍሎች መደብ ያወጡትን ማዛወር፤ ክፍሉን በጥየቄ ለቀው የሄዱትን የተዛወሩበት ሲታጠፍ መመለስ፤ በሌሎች ክፍሎች ጥፋት የፈፀሙትን በግዞትነት ወደ መምሪያው መላክ፤ የክፍሉን ሙያተኞች በውስት ሽፋን ለሌሎች ክፍሎች አሳልፎ መስጠትና ማስቀረት ወዘተ... ፤ በሙያተኞች መካከል አድሎአዊ አፈፃፀሞች፣ ለምሳሌ፡- በመስክ የመረጃ ሰብሳቢ ሠራተኞችና በቢሮ የመረጃ አጠናቃሪ ሠራተኞች መካከል (በውጭ የትምህርት ዕድሎች፣ በሥልጠና እና በወርክሾፐ ተሳትፎዎች) ኃላፊዎች አጠገባቸው የሚገኘውን የቢሮውን ተጠቃሚ፣ የመስኩን ተመልካች ያደረገ፣ አፈፃፀም ወዘተ. ብዙ መዘርዘር ይቻላል፤ ለመምሪያው ሙያተኞችን ከገበያ በብቃታቸው ከመቅጠር ይልቅ በመንግሥታዊ ትዕዛዝ፣ ለምሳሌ፡- የቀድሞው የብሔራዊ ውትድርና ዘማቾች ከአገልግሎት መልስ እንደሙያተኛ በዘርፉ ቴክኒሺያን ብሎ መመደብ - የዛሬውን እናንተው ግለጹት:: እንዲሁም በተለያየ መልክ መምሪያው እንዲቀበል የሚደረጉ ለመብታቸው የማይናገሩ (ተኛ ሲባል መተኛት፣ ተነስ ሲባል መነሳት፣ ግባ ሲባል መግባት ውጣ ሲባል መውጣት፤ ለምን? ብለው የማይጠይቁ ስለሚደርስባቸው የጤና ችግር ሆነ አደጋ የማይጨነቁ ዓይነት ስዎች በመምሪያው እንዲበረክቱ መደረጉ የመምሪያው የአሰራር ኖርም እንዲጣስ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ነው::

**9.** ቀደም ሲል ኤስ.ፒ.ኤም አሁን ደግሞ ቢ.ፒ.አር ለመምሪያው ጥሩ ነገር ይዘው ይመጣሉ የሚል ተስፋ ነበረን:: የሆነው ግን ሌላ ነው:: የመ/ቤቱ ጂ.አይ.ኤስ የመረጃ ማዕከል ስለሆነ፤ ሐይድሮሎጂም የሚሰበስበው መረጃ ሰለሆነ፤ መረጃ ከመረጃ ይቀላቀል በማለት ከ50 ዓመታት በላይ በውሃው ዘርፈ በመምሪያነት የሚታወቀውን በመግፈፍ የሐይድሮሎጂ ንዑስ ዘርፍ የሥራ ሂደት ተደርጓል:: ይህ የክፍሉን ሙያተኞች በሙሉ ያስቆጣና ያሳዘነ አድራጎት ለመምሪያው ትኩረት መነፈጉን ከሚያመለክቱት መካከል ሲሆን የባሰ እንዲዳከም አስተዋጽዖው ከፍተኛ ነው::

እዚህ ላይ ጂ.አይ.ኤስ የመረጃ ሥራ ስለሆነ፣ ሐይድሮሎጂም የመረጃ ሥራ ስለሆነ ይቀላቀሉ ማለት ኢ-አማክኖአዊ አካሄድ ነው፤ የጂ.አይ.ኤስ ሚና ሌላ፣ የሐይድሮሎጂ ደግሞ

የወንዞች ውሃ መረጃ ማከማቻ ነው:: ጂ.አይ.ኤስ፣ የሐይድሮሎጂን መረጃ የመሰብሰብ ሚና በምንም መስፈርት ሊተካው አይችልም፤ የአስተዳደርና ፋይናንስን፣ የመስኖና ድሬኔጅን፣ የላቦራቶሪን ወዘተ. ሚና መተካት እንደማይችል ማለት ነው:: ሊሆን የሚችለው ግን በመ/ቤቱ ስር በቁመቱ፣ በወርዱና በስፋቱ ልክ እንኳን ማደግ ባይችል በመምሪያነቱ ወይም በቢ.ፒ.አር በዳይሬክቶሬትነት መቀጠልና እንደሌሎቹ ዳይሬክቶሬቶች እሱም የበኩሉን መረጃ ለጂ.አይ.ኤስ ማስተላለፍ ነው::

## የመፍትሔ ሀሳቦች

ለዚህ መምሪያ ችግሮች መፍትሔዎች ያሉት እስከዛሬ ከዘረዘርኳቸው ጉዳዮች ውስጥ ነው::

ለምሳሌ:-

- የተዋቀረለትን መዋቅር በትክክል መተግበር
- የሰው ኃይል አያያዝ ማስተካከል፤ ፍልሰቱን የሚያቆም ነገር መፈፀም
- የሚመደብለት በጀት ከሀገሪቱ ዕድገት ጋር አብሮ የሚያድግበት ዘዴ መቀየስ
- የበጀትና የመኪኖች አጠቃቀም ሥርዓት ማስተካከል
- የሥራ መሥሪያ ቢሮ ቤቶች ራሱን ችሎ ማድረግ
- የድጋፍ ሰጪዎችን ሚና ለማጠናከር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መስራት
- የመምራያውን ዎርክሾፕና ላቦራቶሪ ማጠናከር
- ለኦብዘርቨሮች ሚና ተገቢውን ዕውቅና መስጠት
- በመምሪያው የሚገኙ ሙያተኞች የመፍትሔ አስተያየቶች እንዲሰጡ ማድረግ
- ቀደም ሲል የተቀመጡለትን የአሠራር ኖርሞችና የሙያውን ባህል ማክበር
- ሙያተኞችን በችሎታ ከገበያው መቅጠር፤ በየጊዜው ሥልጠና መስጠት
- ኃላፊነት የሚሰማቸውና ችሎታው ያላቸውን በተለያየ የኃላፊነት ቦታዎች መመደብ
- የበላይ አካላት የቅርብ ክትትልና እንክብካቤን ማጠናከር ወዘተ...

ሌላው መፍተሔ መምሪያው ከሚሰጠው ጠቀሜታ አኳያ በቁመቱ፣ በወርዱና በስፋቱ ልክ ማጠናከር ነው:: ይህ ማለት፣ ከመሰል እህት ተቋሞች ተሞክሮ አንፃር ማደራጀት:-

- **<u>የመጀመሪያው ተሞክሮ</u>** - የራሱ ነባር የአሠራርና የአፈፃፀም ይዘቱ ምንም እንከን የሚወጣለት አልነበረም፤ ዕድገት እያሳየ አለመሄዱና የአፈፃፀም ችግሮች አለመወገዳቸው ካልሆን በስተቀር:-

- **<u>ሁለተኛው ተሞክሮ</u>** - የብሔራዊ ሜትሮሎጂ አገልግሎት አደረጃጀትና አወቃቀር ይመጥነዋል:: የሥራውም ባህርይ ተመሳሳይ ነው::

- **<u>ሦስተኛው ተሞክሮ</u>** - የውጭ አገሮች ተሞክሮ በተለይ:

ሀ) የግብፅ የውሃ ሀብት መረጃ ማዕከል ከመረጃ ማሰባሰብ ጀምሮ፣ ተጠናቅሮ ለተጠቃሚዎች አገልግሎት እስከሚውል ድረስ አስፈላጊውን ቁጥጥር ስለሚያደርግ እና ለሠራተኞች ወቅታዊ የብቃት ሥልጠና ስለሚሰጥ፤

**ለ)** *የአሜሪካን የሐይድሮሎጂ ምህንድስና ማዕከል* (Hydrologic Engineers Center - HEC) *መረጃዎች ለመሰብሰብ፣ ለማጠናቀር፣ ለመተንተንና ለማሰራጨት ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ስለሚጠቀም፡፡*

የዘርፉን ምሁራንና ተገልጋዮችን /Stakeholders/ ማማከር (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ወዘተ.)፤ ሀገሪቱ የሐይድሮሎጂ ምሁራን ደሃ አትመስለኝም፡፡

በአጠቃላይ መምሪያው ትኩረት ስለአጣ ትኩረት ይሰጠው! በማለት እንጂ ማንንም ለመንካት የታለመ አለመሆኑን ግንዛቤ ቢኖር፡፡ በ1998 ዓ.ም የውጤት ተኮር ትግበራ በማለት የመ/ቤቱ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ጽ/ቤት ኃላፊ አማካኝነት በተጠራው የመምሪያ ሠራተኞች ስብሰባ ላይ የሠራተኞች አፈፃፀም ዝቅተኝነት ተበክሮ ሲገለጽ ያቀረብኩት ጥያቄ «ቁልፉ የሚገኘ ው በኃለፊዎች እጅ፣ ሠራተኞች ምን ማድረግ ይችላሉ?» የሚል ነበር፡፡ ይህን ያልኩት ሠራተኞች የታዘዙትን ሳይለግሙ ለመፈፀም ዝግጁ መሆናቸውን ለመግለጽ ነበር፡፡ ለዚህ የተሰጠኝ ምላሽ «የምን ቁልፍ?» የሚል ስለነበር ሐይድሮሎጂ ከሥራው ባህርይ አኳያ እቅድ በጀት - ሥምሪት በኃላፊዎች እጅ ስለሆነ እነሱ ሲፈቅዱ ብቻ መሆኑን ለመግለጽ ነበር፡፡

ሌላው በ2002 ዓ.ም በቢ.ፒ.አር ትግበራ ስብሰባ ላይ ያቀረብኩት «አንዳንድ ኃላፊዎች ለሠራተኞቻቸው ጠረጴዛ ላይ ሥራ አያቀርቡላቸውም (ሥራ አይሰጧቸወም)፣ ሥራ ፈትተው ጋዜጣ ለማንበብ የተገደዱትና ሲሰለቻቸው ወጣ ገባ ለሚሉት ምን መፍትሔ ይኖራል?» የሚል ነበር፡፡ የተሰጠኝ መልስ «ይስተካከላል» የሚል ነበር፤ ነገር ግን መፍተሔ ባለማስገኘቱ የካቲት 30 ቀን 2002 ዓ.ም የማስታወቂያ ቁጥር ውሚ32/07/171 «ከመጋቢት 1 ቀን 2002 ጀምሮ የመ/ቤቱ ሠራተኞች ከጧቱ 2 ሰዓት ተኩል እስከ 6 ሰዓት ተኩል እና ከቀትር በኂላ ከ7 ሰዓት ተኩል እስከ 11 ሰዓት ተኩል ባለው ጊዜ ከመ/ቤት ውጭ እንዳይወጡ፣ ለመውጣት ከዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር ለዚህ ተብሎ የተዘጋጀ ውጭ የመውጣት ፈቃድ የተሰጠበት ሰነድ ለበር ጥበቃ ሠራተኞች በማስረከብ በመኪኖች መውጫ በር በኩል መውጣት እንዲችሉ» የሚያዝ ነበር፡፡

እንግዲህ የቢ.ፒ.አር ትግበራ ይህ ነው? መ/ቤቱ የጥቂት ግለሰቦች ብቻ እንዲመስል የሚደረገው ለምንድን ነው?

በሌላ በኩል በ2015 እ.አ.አ ሐይድሮሎጂን ዓለም አቀፍ ሜትሮሎጂ የደረሰበት ለማድረስ ሁሉም በርትቶ እንዲሰራ ይባላል፤ ሥራዎች ግን ቀጥ ብለዋል፡፡

ውሃ ህይወት ነው፤ ውሃ የግብርና መር ኢኮኖሚው የጀርባ አጥንት ነው፣ ያለሐይድሮሎጂ መረጃ የሚሰራው የውሃ ዘርፍ ልማት እርባና አይኖረውም እየተባለ ትኩረት መንፈግ ምን ይባላል? ስለሆነም ለኔ የማታየኝ ይታያችሁ፣ ለኔ የሚሰማኝ ይሰማችሁ ብዬ ይህን ጽሁፍ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት እንዲያውቁት አድርጌአለሁ፡፡ እውነታውን ለማጣራትና ለማወቅ ለሚፈልጉ ወገኖች ሁሉም ማስረጃ በውሃ ሀብት ሚኒስቴር ሐይድሮሎጂ መምሪያ ውስጥ ይገኛል፡፡

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርካት! ይጠብቃት!**

# የውሃ ሃብት /ሀይድሮሎጂ/ መረጃ አሰባሰብ ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡

/በውሃ ሀብት ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ/

ለአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል
<u>አዲስ አበባ</u>

*ይህንን ጽሁፍ ለመጻፍ ያነሳሳን አውራምባ ታይምስ እትም 3ኛ ዓመት ቁጥር 109 በመጋቢት 25/2002 ዓ.ም ላይ **<u>ሃይሎሮሎጂ! ምን ነካው? የውሃ ሀብት ሚኒስቴር ማኔጅሜንት ሲፈተሽ</u>** በሚል አርዕስት ባወጣው ጽሁፍ ላይ አስተያየት ለመስጠት ነው፡፡*

በቀጥታ ጸሃፊው እንደ መረጃ በመጥቀስ እያነሱ የጻፉት ጭብጥ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ከመስጠት ይልቅ ስለ ሀይድሮሎጂ ንዑስ የስራ ሂደት አጠቃላይ ሁኔታ ከዚህ በታች ለመግለጽ እንፈልጋለን፡፡

የሀይድሮሎጂ አገልግሎት አላማ የአገሪቷን የውሃ ሀብት በመገምገምና በመቆጣጠር ብሎም በተገቢው መንገድ ለተለያዩ የሶሽዮ ኢኮኖሚ ልማቶች ለመጠቀም በጊዜና በቦታ ተለዋዋጭ የሆነውን የረጅም ጊዜ የወንዞች፤ የሀይቆችና የተፋሰሶች የውሃ ሃብትና ፍሰት መረጃዎችን በመሰብሰብ በማጠናቀርና በመተንተን ለተጠቃሚ አካላት ማቅረብ ነው፡፡

የሀይድሮሎጂ አገልግሎት ታዳሽ የሆነው የአገሪቱ የገጸ-ምድርና የከርሰ-ምድር የውሃ ሃብት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የሀይድሮሎጂ አገልግሎት የወንዞችና ሀይቆች ፍሰትና ጥልቀት መጠን መለካት፣ በውሃ እየታጠበ የሚሄደውን የአፈር/ደለል መጠን መከታተል፤ የገጸ-ምድር የውሃ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የማያስችሉ የተለያዩ ደረጃ ያላቸውን የሀይድሮሎጂ ጣብያዎችን ማቋቋምና ማደራጀት ዋና ዋናዎቹ ተግባራት ናቸው፡፡

የአገሪቱን የገጸ-ምድር ውሃ ሀብት ለመከታተልና በተለያዩ ተጠቃሚዎች ለሚከናወኑ የልማት ተግባራት የሚውሉ አስተማማኝ የመረጃ ፍላጎትና ስርጭት ለማሳካት የሀይድሮሎጂ ጣቢያዎችን የማስፋፋትና የማደራጀት ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡

የሀይድሮሎጂ መረጃ አሰባሰብ ሂደት የማያቋርጥ ሂደት በመሆኑ በመላ አገሪቱ በተቋቋሙት ዘጠኝ የሃይድሮሎጂ ቀጠናዎች በሚገኙ ባለሙያዎችና ቴክኒሺያኖች እንዲሁም በዋናው መ/ቤት ባለሙያዎች የሀይድሮሎጂ ጣቢያዎች የማቋቋምና የማጠናከር ተግባራት በማከናወን መረጃዎችን ለመሰብሰብ፤ ለማጠናቀርና ጥቅም ላይ ለማዋል እንዳሁም የመረጃ ክምችትና ትንተና አቅም ለማጎልበት ጥረት ተደርጓል፡፡

በመላው አገሪቷ በሥራ ላይ ከሚገኙት 475 የሀይድሮሎጂ መረጃ ማሰባሰቢያ ጣቢያዎች መረጃዎች እየተሰበሰቡ በመረጃ ማዕከሉ ተጠናቅረውና ተተንትነው ለተለያዩ ተጠቃሚዎች እንዲሰራጩ እየተደረገ ነው፡፡

የገጸ-ምድር ውሃ ሀብት መረጃዎች በዋናነት በመንግስት፣ በዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች፣ በግል ኢንቨስተሮችና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በሚካሄደው የመስኖ ልማት፣ የሃይድሮፖወር ልማት፣ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የተፋሰስ ልማት፣ የጎርፍ መከላከልና የአካባቢ እንክብካቤ ፕሮጀክቶችና ልማት ፕሮግራሞች ወዘተ አገልግሎት እየዋለ ነው።

ወቅታዊ የሃይድሮሎጂ መረጃዎች በአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ላይ ወሳኝ በመሆናቸው የውሃ ሃብቱን በአግባቡ ለማልማት በተለይም የከርሰ-ምድር የውሃ ሃብት መረጃዎችን ለማመላከትና ለመከታተል እንዲሁም የአገሪቱን የውሃ ሃብትን በአስተማማኝነት ለመተንበይና ወቅታዊ መረጃዎችን ለማቅረብ በሚያስችል መልኩ እየተጠናከረ ይገኛል።

ውድ አንባቢያን ከላይ የተጻፈው ስለ ሃይድሮሎጂ አጠቃላይ ሁኔታ ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የውሃ ሃብት መረጃ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ስር ብቻውን በሃይድሮሎጂ ንዑስ የስራ ሂደት የተደራጀው ከሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት እንመልከት።

<u>የሃይድሮሎጂ ዋና ዋና ተግባራት፣</u>

1. መረጃ መሰብሰብ / በመላው የአገሪቱ ተፋሰሶች/፣

1.1 የሃይድሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ Network ማጥናትና መተግበር፣

2.2 ለመረጃ መሰብሰቢያ የሚሆኑ ጣቢያዎችን መምረጥና ማቋቋም፣

2.3 ለመረጃ መሰብሰቢያ ሎጂስቲክ ማሟላትና በወርክሾፕ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት

2.4 ከመላው የአገሪቷ ተፋሰሶች በስሩ በሚገኙ የኃይድሮሎጂ ጽ/ቤቶች በኩል የገጸ- ምድርና የከርሰ ምድር የውሃ ሀብት መረጃዎችን መሰብሰብ / የውሃ ከፍታ፣ የውሃ ፍሰት፣ የደለል ናሙና፣ የውሃ ጥራትና የመሳሰሉት/፣

2.5 በተለያዩ ኃይቆችና ግድቦች ላይ የተከማቸውን የደለል መጠንና የተጠራቀመውን የውሃ መጠን ለማወቅ የሚያስችል ሰርቬይ ስራ ማከናወን፣

2.6 የተሰበሰቡ የደለል ናመናዎችን በላቦራቶሪ በመመርመር የደለል መረጃ ማጠናቀር፣

1.7 የግድቦችና ወንዞችን የውሃ ከፍታ ወቅታዊ መረጃ መሰብሰብ፣

2. መረጃ ማጠናቀር የመረጃ ጥናት ቁጥጥር ማድረግና ወደ መረጃ ማዕከል በማስገባት ለተጠቃሚ ዝግጁ ማድረግ፣
3. መረጃዎችን ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፣
4. ለመረጃ ተጠቃሚዎች ለፕሮጀክቶችና ለክልሎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፣ በአጠቃላይ የሃይድሮሎጂ ሥራዎችን በተመለከተ ድጋፍና የማማከር ስራዎች መስራት፣
5. በግድቦችና ወንዞች የውሃ ከፍታ ትንበያ በመስራት የቅድመ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የጎርፍ አደጋን መከላከል፣
6. በግድቦች የሚገኘውን የውሃ መጠን በመተንበይ የውሃ አጠቃቀምን መከታተልና የግድቦችን የውሃ ሥርዓት ማውጣት፣
7. የውሃ ሃብት መረጃን በመተንተን ለተለያየ ጥቅም እንዲውል ማድረግ፣
8. በልማት ሥራዎች በኃይድሮሎጂ ጥናት ላይ መሳተፍ ናቸው።

ውድ አንባቢያን  ጸሐፊው አሉታዊ ጽሁፉን የራሱን የግል ፍላጎት ለማራመድ ሲል ለጻፋቸው ጽሑፎች እንደ ማስረጃ አድርጎ በጠቀሳቸው ነጥቦች ላይ ተጨባጩን እውነታ ከዚህ በታች እንገልጻለን።

ከነዚህም በአሉታዊ ገጽታነት ከተጠቀመባቸው አንዱ የቦዮ ግድብ ነው። ይህ ግድብ የተገነባው በደርግ መንግስት ነበር። ነገር ግን የደርግ መንግስት ግድቡን ስራ ሳያስጀምር በመገርሰሱ ግድቡን ስራ ለማስጀመር ጥናት በሚካሄደበት ወቅት ሁሉም ደርግ እንደሚያደርገው የሚገነባቸውን ፕሮጀክቶች የአካባቢውን ሕብረተሰብ /ነዋሪ/ ሳያማክር ያካሄደው ግንባታ መሆኑ ታወቀ። በመሆኑም በውሃው የሚሸፈነው ቦታ ውስጥ በርካታ ሕዝብ መፈናቀል ስለአለበት ከነዋሪዎቹ ጋር በተደረገው ምክክርና ጥናት መሰረት ይኸንን ህዝብ ከማፈናቀልና ምንም አይነት የአካባቢ ተጽዕኖ ሳያስከትል ወደታች ዝቅ ብሎ መሰራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ በአሁኑ ወቅት የዝርዝር ጥናትና ዲዛይን ስራው ተጠናቆ ለግንባታ ዝግጁ ሆነዋል።

ጸሐፊው እንደአሉት የውሃ ሀብት መረጃ /ሃይድሮሎጂ ጥናት/ ባለመሰራቱ /መረጃ እጥረት/ ሳይሆን ግድቡ በደርግ መንግስት የተቀደሙ ለመንግስት እርሻ በመሆኑ የተደረገው ለውጥ የፖሊሲ አቅጣጫ ለውጥና በወቅቱ ትክክለኛ የሶሽዮ ኢኮኖሚ ጥናት ባለመካሄዱ ነው።

ሁለተኛው በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአሚባራ አካባቢ የመስኖ ልማት ችግር አጋጥሞታል ተብሎ የተጠቀሰው የውሃ ሃብት መረጃ ጠፍቶ ወይም በበቂ ሁኔታ ሳይጠና ቀርቶ ሳይሆን በአካባቢው ያለ የመሬትና የከርሰ-ምድር ውሃ አቀማመጥ መሆኑ መታወቅ አለበት።

በአገራችን ካሉት 12 ዋና ዋና ተፋሰሶች ውስጥ እጅግ በርካታ ጥናቶች የተካሄድበትና ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተለያዩ ልማቶች የተካሄዱበት የአዋሽ ተፋሰስ ነው። ስለዚህ ጸሃፊው እንደጠቀሱት ለውሃ ሀብት ጥናት መረጃ ትኩረት አለመስጠት ተብሎ በጸሐፊው መደምደሙ የግል ፍላጎታቸውን ንዑስ የስራ ሂደቱን በማጥላላት ለማሟላት የፈለጉ መሆናቸውን በግልጽ ያሳያል።

ከዚህ ውጭ የከርሰ ምድር ውሃ ከፍ ቢል እንኳን ጸሐፊው እንደባለሙያ መፍትሔው የድሬይኔጅ ስራ /የመሬት ውስጥ ወይ የመሬት ላይ/ መሰራት እንደአለበት መጠቆም ይችሉ ነበር። እንዲሁም ጸሐፊው ስለጉዳዩ ዕውቀት ከሌላቸው ጠይቀው መረዳት ይችሉ ነበር። ሊጽፉ ለፈለጉት አላማ ማሳኪያ እንዲሆን በማለት ብቻ መስኖን ከድሬይኔጅ ነጥለው ማቅረብ ተገቢ አለመሆኑን አንባቢያንና ጸሐፊው እንዲገነዘቡ እንወዳለን። እንደዚሁም ጸሐፊው ከ38 ዓመት በላይ ተመድበውበት የውሀ ሀብት መረጃ ሲሰበሰቡበት የነበረውን የአዋሽ ተፋሰስ የመረጃ ዕጥረት ያለበት አድርገው ማቅረባቸው ለትዝብት የሚዳርጋቸው ነው።

ሶስተኛ የመቂ ዝዋይን መስኖ ልማት በተመለከተ ጸሐፊው የጻፉት ጽሁፍ የዝርዝር ጥናት እጥረት እንደአለ ያቀረቡት ከሃቅ የራቀ ነው። በደርግ መንግስት ዘመን ፕሮጀክቱ ለመንግስት እርሻ የታቀደ ስለነበር በአካባቢው የሚኖሩ አርሶ አደሮች አንነሳም /አንፈናቀልም/ በማለታቸው የተፈጠረው ማሕበራዊ ችግር ነው። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የቆመውን የመቂ ዝዋይ መስኖ ልማት የፖሊሲ አቅጣጫ ለውጥ ተደርጎ /ከመንግስት እርሻ ወደ ሕብረተሰብ መስኖ ልማት/ ለሕብረተሰቡ መስኖ ልማት በግንባታ ላይ ይገኛል። በወቅቱ የአካባቢው ነዋሪዎች /አርሶ አደሮች/ ሳይወያዩበት የመንግስት እርሻ ለማድረግ ተሰርቶ የተቋረጠው 3000 ሄክታር ሲሆን አሁን እጥፍ የ6000 ሄክታር ዝርዝር ጥናት ተጠናቆ ግንባታ ተጀምሮ እየተፋጠነ ይገኛል።

ስለዚህ የመቂ ዝዋይን መስኖ ልማት ፕሮጀክት ያስቀመው የሃይድሮሎጂ ጥናት ዕጥረት ሳይሆን በደርግ ዘመን የነበረው የልማት ፖሊሲ አቅጣጫ መሆኑን ውድ አንባብያንና ጸሐፊው እንዲገነዘበው እንወዳለን::

አራተኛው ለጎንደር ከተማ ነዋሪዎች የንጹህ ውሃ ምንጭ የሆነውን የአንገረብ ግድብን በተመለከተ ጸሐፊው የመሰላቸውን ሃሳብ ለመግለጽ ሞክረዋል:: ግድቡ በደርግ መንግስት ተጀምሮ ደርግ ሳያጠናቅቀው በዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ሊወገድ በመቻሉ በመንግስት በ1995 ዓ.ም ሊጠናቀቅ ችሏል:: እንደጸሐፊው አገላለጽ የውሃ መረጃ እጥረት ያለበት ፕሮጀክት ሳይሆን ግድቡ ሌሎች ግድቦች ከሚሰጡት አገልግሎት የተሻለ እንጅ ያነሰ እንዳልሰጠ መገንዘብ ያስፈልጋል:: በተጨማሪም ወደ ግድቡ የሚገቡትን የደለል መጠን ለመቆጣጠር በአካባቢው ተፋሰስ እንክብካቤ ስራዎች መስራት ተችሏል:: ግድቡ ከ17 ዓመት በላይ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከሁሉም በላይ ግድቡ ከታለመለት አላማ አኳያ ውሃ የሚጠራቀምበት ቦታ ላይ ከፍተኛ የከርሰ-ምድር ውሃ በአካባቢው እንዲገኝ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው:: በመሆኑም ከግድቡ በታች የውሃ ጉድጓዶች ተቆፍረው ለከተማው የውሃ አቅርቦት የሚሆን ብዛት ያለው የውሃ መጠን የሚያመነጩ ሆነዋል::

በመጨረሻም ጸሐፊው በሚኒስቴር መስሪያ ቤታችን ለረዥም ዓመታት ያገለገሉ ናቸው:: በሃይድሮሎጂው አገልግሎት ከ38 ዓመት በላይ አገልግለዋል::

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሃይድሮሎጂ ቀጠና ጽ/ቤቶችን በተመለከተ ለስነ-ምግባር መከታተያ ጽ/ቤት የቀረቡት ሶስት ጥቆማዎች ተጣርተው ሁለቱ ትክክለኛ ጥቆማ በመሆናቸው በአጥፊዎቹ ላይ የዲሲፕሊን ቅጣት ተወስኖባቸዋል:: ቅጣቱ ተግባራዊ ሆኗል:: አንደኛው ጥቆማ ግን የራሳቸውን ፍላጎት /ጥቅም/ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ለማሳካት ያስችለኛል ብለው የገመቱት በመሆኑና ጥቆማው ሲጣራ ጭብጥ የሌለው በመሆኑ ውድቅ እንዲሆን ተደርጓል::

በዚህም የተነሳ የሃይድሮሎጂ የስራ ዘርፍ ለማጥላላት ተገደዱ እንጅ ንዑስ የስራ ሂደት ቢሆንም በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ከሃይድሮሎጂ ጋር ተመሳሳይ የስራ ፍሰቶችን ማሰባሰቡ የግድ ስለሆነ በውሀ ሀብት መረጃ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ስር በንዑስ የስራ ሂደት እንዲደራጅ ተደርጓል:: ንዑስ ስራ ሂደት ከሆነና ከመሆኑም በፊት የሚያከናውናቸው ስራዎች የተቀነሰበት የለም:: ሌሎች ለስራው ደጋፍ ሊሰጡ የሚችሉ እንደ ሎጅስቲክና በጀትም ጭምር አልተቀነሰም:: ስለዚህ ውድ አንባቢያንም ሆናችሁ ጸሐፊው ግለሰብ ይኸንን እንዲገነዘቡልን ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን::

## ቅዳሜ መዝናኛ

### አንዳፍታ

### «የእኔን ዘመን ፈጥሬ ማለፍ እመኛለሁ»

**አርቲስት ዓለማየሁ ታደሰ**

*በ1986 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በ«ቲያትር አርት» የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል:: ከዩኒቨርሲቲ ጀምሮ ሰላሳ ሁለት በሚጠጉ የመድረክ ቲያትሮች ላይ ተውኗል:: አንጋፋው*

አርቲስት መርሐዊ ስጦት «ከእግዚአብሔር የተላከ ሎተሪ ነው» ሲሉ ያወድሱታል፡፡ በቅርቡ በተካሄደው «የኮሜዲ ቲያትሮች ፌስቲቫል 2002» ላይ ሦስት ቲያትሮች በመፃፍ፣ ሦስት ቲያትሮች ላይ በመተወን የክብር ተሸላሚ ሆኖ 2500 ብር ተሸልሟል፡፡ በቲያትር ዳይሬክተርነት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቲያትር ውስጥ በማገልገል ላይ ነው፡፡ «አሪፍ ተዋናይ ነኝ» የሚለው አርቲስት ዓለማየሁ ታደሰ አንድ አፍታ ***አቤል ዓለማየሁ*** ላቀረበለት ዘና የሚያደርጉ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቶባቸዋል፡፡

***<u>ከአርብ እስከ እሁድ በብሔራዊ ቲያትር መድረክ ላይ ቲያትር ታቀርባለህ፡፡ ለምሳሌ ከስናፍቅሽ ተስፋዬ ጋር በሦስቱም ላይ አብራችሁ ትሰራላችሁ፡፡ የአንዱን ቃለ-ተውኔት ለሌላው የመጠቀም ሁኔታ ገጥሞህ ያውቃል?</u>***

የቲያትሮቹ ገፀ-ባህሪዎችና ሁኔታዎች የተለያዩ ናቸው፡፡ ከስናፍቅሽ ጋር ባቢሎን በሳሎን ላይ አምጥቼ የማስቀናባት ሴተኛ አዳሪ ናት፡፡ ምስጢረኞቹ ላይ አባቷ ሆኜ ነው የምሰራው (በዚሁ ቲያትር ላይ ፍቅረኛዋ ሆኖ ይሰራ ነበር፡፡) ደመ-ነፍስ ላይ እጮኛዬ ናት፡፡ የምጠራት በተለያየ ስም ነው፡፡ ትኩረትን ይጠይቃል፡፡ ድምጿ፣ እንቅስቃሴዋ የእሷ ናቸው፡፡ የምንጀምርበት ጉዳይ ግን የተለያየ ስለሆነ በጭራሽ አይቀላቀልም፡፡

***<u>ቃለ-ተውኔትን አጥንተህ ለማወቅ (ለመያዝ) ትችላለህ፡፡ ህይወትንስ አጥንተህ ለማወቅ ሞክረህ ታውቃለህ?</u>***

ኡው.. ህይወት እኮ ደስ የሚለው ነገር እሱ ነው፡፡ ቲያትር ስንጀምረው በምን ሁኔታ እንደሚያልቅ ቀድመን እናውቀዋለን፡፡ ህይወት ላይ ግን ይህ የለም፡፡ እግዚአብሔርም ሲፈጥረን እንደ ቲያትሩ የእኛን ፍፃሜ ያውቀዋል፡፡ ትወናው ላይ መጀመሪያ ትጣላው የነበረውን ሰው መጨረሻ በፍቅር የምትገናኝበት ሁኔታ አለ፡፡ የፍቅሩን ጊዜ በሚታመን ሁኔታ ሰርተህ አልፈኸው፤ በፀቡ ጊዜ ደግሞ ይህንኑ መስለህ ፀቡ ይቀጥላል፡፡ የተጠና ያለቀ ጉዳይ ነው፡፡ ህይወት ላይ ግን ይሄ የለም፡፡ እንዳንሰለችም የሚያደርገንም ይኸው ነው፡፡

***<u>ህይወት አጨራረሱ የማይታወቅ ልብ አንጠልጣይ ቲያትር ነው እያልከኝ ነው?</u>***

አዎ! ማለት ይቻላል፡፡ አጨራረሱ አይታወቅም፡፡ እስካለን ድረስ ስንተውን እንኖራለን፡፡

***<u>በአሁን ሰዓት በመድረክ ቲያትሮች ላይ አስቂኝ ገፀ-ባህሪያትን ትጫወታለህ፡፡ ይህ በመደበኛው ህይወትህ ላይ ተጽዕኖ የለውም? «እንደ ቲያትሩ ቀልድ አታብዛ እንጂ» የሚሉህ የሉም?</u>***

ከጓደኞቼ ጋር ሆነን የምንጨዋወት ከሆነ አሪፍ «ሙድ» መፍጠር እችላለሁ፡፡ ቁም-ነገር ላይ ቁም-ነገረኛ ነኝ፡፡ አንዳንዴ ሰዎች ያምታቱታል፡፡ ተጨንቀህ ሰው ልትጠይቅ ሐኪም ቤት ስትሄድ «ሊነጅሱህ» ይሞክራሉ፡፡ «ፊልም ነው? ካሜራ አለ እንዴ?» ይሉሀል፡፡ ሰው የምትጠይቅ አይመስላቸውም፡፡

***ለምሳሌ የተገናኘን ጊዜ «አንተን ለማግኘት ፈጋሁ እኮ» ስልህ [ለጨዋታ ያህል ነው] እጅህን አፍህ ላይ አድርገህ «እንዴ!» ብለህ የሳቅከው ሳቅ በምትሰራቸው ቲያትሮች ላይም ተመልክቼው አውቃለሁ። እና ተፅዕኖ...***

አየህ የሚያየው ሰው ያወቀዋል። ተዋናይ እኮ ከየትም አያመጣወም። እስከ ዛሬ ከትምህርት ቤት ጀምሮ የሰራኋቸው 32 የሚጠጉ ቲያትሮች ከእኔ የሚወስዷቸው ድምፅ፣ እንቅስቃሴና አኳኋን አሉ። ሊመሳሰልብህ ስለሚችል ሰው እንዳያስታውስ በሆነ አይነት መልኩ ለመቀየር ትሞክራለህ። የሰራኸው ነገር እየበዛ ሲመጣ ፈተናውም አብሮ ይጨምራል። የተለያየ ነገር መፍጠር አለብህ። እንዳልከው ያቺ «ሳቅ» የሆነ ነገር ላይ ገብታ ይሆናል። እንደውም ሰዎች ስትተውን ልጅህን ትመስላለህ ይሉኛል። ባቢ (በእምነት ዓለማየሁ) ከእኔጋ ያመሳስሉታል።

***ባደረግኩት የዳሰሳ «ናሙና» በተለይ ወጣት የቲያትር አፍቃሪያን ለአንተ አድናቆት አላቸው። አንጋፋው አርቲስት መርሐዊ ሰጦትም «ከእግዚአብሔር የተላከ ሉተሪ» ሲሉህ አብረን ሰምተናል። ይህ ለምን የሆነ ይመስልሀል?***

እእ...እ...ኸ እንግዲህ አሳምኜ ስለምሰራ ነው። ሌላ ነገር የለውም።

***አሳምኜ ምን ማለት ነው?***

ገፀ-ባህሪው የሚፈልገውን ነገር የእውነት ሆኜ ስለምሰራ ያ ነገር ይመቻቸዋል ለማለት ነው። «ስጦታ» አለኝ ማለት ነው።

***አንደኛ ነኝ እያልክ ነው?***

አይ! ተቀብቻለሁ ለማለት ነው። (እየሳቀ)

***አንደኛ ነኝ ለማለት ፈራህ ወይስ ይሉኝታ ነገር ...***

አንደኛ ለማለት ሳይሆን... ሰው ሲመሰክርልህ እንደምትችል ታውቀዋለህ (ታረጋግጣለህ።) የበለጠ ሙያው (የምትሰራው ነገር) ይመችኃል። ለእኔ ተመችቶኝ ስለምሰራ ሰዎችም የሚያዩት ነገር ይመቻቸዋል።

***አንተስ ስለ ሙያህ ራስህን እንዴት ትገልፀዋለህ?***

አሪፍ ተዋናይ ነኝ። አይክበድህ እንዲህ ስልህ። (እየሳቀ)

***«ፌስ ቡክ» ላይ የአንተን የግል ማህደር ሳይ ተዋናይ፣ ፀሐፊ (ደራሲ)፣ ተራኪ፣ ታሪክ ነጋሪ (story teller) (በዚህ ዘርፍ ስዊድንና ኡጋንዳ ሄዶበታል) ዳይሬክተር፣ ተርጓሚ መሆንህን አስፍረሀል። ከሁሉም የጥበብ ዘርፍ በበለጠ ጥበብን ስገልጽ ደስ ይለኛል የምትለው በየቱ ነው?***

በትወና። በተለይ የመድረክ ቲያትር እዚያው ምላሹን የማገኝበት ስለሆነ «የመጨረሻ» ያስደስተኛል።

***ሉሲ፣ ሰላም፣ በቅርቡ ደግሞ ከአራት ሚሊየን ዓመት በላይ እድሜ ያላት «አርዲ» የተሰኘች ቅሪተ አካል ተገኝታለች:: ይህ ደግሞ በመንፈሳዊ አቆጣጠር ውድቅ ይደረጋል:: አንተ የቱን ትቀበላለህ?***

የሃይማኖቱን ነው የምቀበለው::

***ለእነ አርዲ እውቅና አልሰጠሁም ማለት ነው?***

ታሪኩ ደስ ይላል:: ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ናት ሲባል ደስ ይልሀል:: ምርምሩም ብዙ ድካም የሚጠይቅ የሳይንስ ዘርፍ ነው:: እኔ ግን ከእንደዚያ ዓይነት ፍጥረት የተገኘሁ ነኝ ብዬ አላስብም::

***ካየህ ግን አጠገብህ ሐረገወይን አሰፋ በሎተሪ አምስት መቶ ሺህ ብር አግኝታለች:: አጋጣሚ በፈጠረው መልኩ ብዙዎች የስኬትን መንገድ ሲመላለሱበትም ይታያል...***

እኔም ሎተሪ ቆርጣለሁ ደርሶኝ ገን አያወቅም:: እሷ (ሐረገወይን) ቆርጣ አታውቅም ነበር:: ስትቆርጥ ግን ደረሳት:: 500 ሺህ ብር እኔም ፈለግ ነበር:: ይሄም እድል ነው የሚባለው አይደል? ሁሉም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው::

***ስም ከመቃብር በላይ ይውላል ይባላል:: በዚህ ታምናለህ?***

ሰው የሚሰራው ከመቃብር በላይ ለመጠራት ብሎ አይደለም:: ስትሰራ ከአንተ አልፎ ለሌሎች ይደርሳል:: ሌሎች ሰዎች ውስጥ ቀርቶ በዚያ ትታወሳለህ:: አሪፍ ነገር ሰርተውም የማይታወሱ ሰዎች አሉ:: የሚያውቃቸው ትንሽ ሰዎች ብቻ አውርቶ የሚያልፈው ይኖራል:: አንዳንዱ ደግሞ ከሰራው በላይ የሚነሳና የሚታወስ አለ:: በመልካምም፤ በመጥፎም ሊሆን ይችላል::

***አንተ ከመቃብር በላይ የሚቀመጥ ስም አኖራለሁ ብለህ ታስባለህ?***

በሚገባ:: በእዚህ ሙያ ውስጥ ሲወድቅም ሲነሳም አብሬው ነኝ ያለሁት:: አቅሜን ካወቅኩትና እንደምችል ከተረዳሁ የእኔን ዘመን ፈጥሬ ማለፍ እመኛለሁ::

***መድረክ ስራዎችህ ላይ አንዳንድ ጊዜ ዓለማየሁ ስለሆንክ ብቻ የሚስቁልህ ይመስለኛል?***

አይመስለኝም:: አንተ ቲያትሮችን በጣም ስለምትከታተል ይሆናል እንጂ አብዛኛዎቹ (ፊልሞችን የሚመለከቱ ሰዎች) ምን አይነት «አረመኔ» ሰው ነው የሚሉኝ:: «ኤልዛቤል»ን ከሠራሁ በኋላ «ዴዝዴሞና» ሲደገም ጊዜ ጠምደውኛል:: መድረክ ላይ ግን የሚያስቁ ነገሮች በዝተዋል:: ለምደውኝም ይሆናል:: መጀመሪያ ሲያዩኝ የሚስቁ ይኖራሉ:: ከዚያ በኋላ ግን «ትራክ» ውስጥ እንዴት እንደማስገባቸው እኔ አውቃለሁ:: [ጋሽ መርሐዊም «ዴዝዴሞና ላይ እንዳለው ዓለማየሁ እንዳይመስልህ ጥሩ ልጅ ነው» ብለውኛል::]

***«አይስ ክሬም» እየላስክ መንገድ ላይ ትሄዳለህ?***

ምንም ችግር የለብኝም እሄዳለሁ:: ምንም የሚያሳፍር ነገር የለውም::

***ለማረጋገጥ አሁን ስንወጣ እንሞክረዋለን...***

[በጣም እየሳቀ] አሁን የምልስበት ጊዜ አይደለም፡፡

[***ስለዚህ የተናገርከውን ሁሉ አታርገውም ማለት ነው***] ***(ሳቅ፡፡) እንለፈው... ትዳር የያዝከው፤ ትዳር መያዝ አለብኝ ብለህ በማመንህ? ሳላገባ ዕድሜዬ አለፈ ብለህ ስላሰብክ? ወይስ ለአንተ የምትሆን ሴት ስላገኘህ ነው?***

እኔ ትዳር የያዝኩበት ምክንያት ከጓደኛዬ ጋር ለምን ተለያይተን እናድራለን ከሚል ስሜት ነው፡፡ ተዋደናል፣ ቀኑ ያልቅብናል፣ ምሽቱ ውስጥ እንገባና ቤተሰብ የሚነካ ሰዓት እንገባለን፡፡ ወድጃታለሁ፣ ተጣጥመናል ለምን ወደ ቤቷ ትሄዳለች? ለምን እንለያያለን? ብለን አሰብንና በቤተ-ክርስቲያን የተክሊል ስርዓት ተጋብተን አብረን መኖር ጀመርን፡፡ አንዳንዶች ፈጠንክ ብለውኝ ነበር፡፡

***ምንን ስታይ «ኦ አምላክ የእኔ ስላደረከው አመሰግንሃለሁ» ትላለህ?***

ባለቤቴንና ልጆቼን፡፡ (ሁለት ልጆች አሉት)

***በሙያህ ካገኘኸውስ?***

ለትወና የሚያስፈልገውን ነገሮች ሁሉ ስለሰጠኝ፡፡ በደንብ እንድገልፅበት አደርጉኛል፡፡

***ሰዎች ለመዝናናት ወደ እናንተ (ቲያትር ቤት) ይመጣሉ፡፡ አንተስ የመዝናኛ ምርጫህ የት ነው?***

እኔ የሰራሁባቸውም ሆኑ ያልሰራሁባቸውን ፊልሞች ማየት እወዳለሁ፡፡ ቲያትሮችንም እመለከታለሁ፡፡ አሁን አሁን ከቤተሰቤ ጋር የማሳልፈው ሰዓት እያነሰብኝ መጣ እንጂ በጣም ደስ የሚለኝ ሰዓት እሱ ነው፡፡ ቅዳሜ እና እሁድ ባገኘቸው ደስ ይለኛል፡፡ መጫወት እንደ ጀመርን ወደ ስራ እመጣለሁ፡፡ ማታ አምሽቼ ስሄድ ተኝተው እደርሳለሁ፡፡ ይህ ጊዜ ቢበዛልኝ ደስ ይለኛል፡፡

***"«ስርቅታ» ሰው ሲያነሳ ነው፤ የዚያ ሰው ስም ሲጠራም ይቆማል" ይባላል፡፡ አጋጥሞህ ያውቃል?***

«ፎዚያ» ድራማን ስንቀረፅ ረጅም ሰዓት «ስርቅ» እያለኝ አልቆም ብሎኝ ያውቃል፡፡ ውሐ ጠጥቼ፣ ቆይቶ ተወኝ፡፡ ማንን ጠርተህ ማንን ትተወዋለህ፡፡ ስም ሲጠራ መተው አጋጥሞኝ አያውቅም፡፡

## ዳሰሳ

# ማን ይሆን ኪነ-ጥበብን ነፃ የሚያወጣ? እርሶስ፣ ማንን ይመርጡ ይሆን?

**በነበበ ብሩ**

ገፅታቸው ዴሞክራሲያዊ፣ ወይም የምርጫ ሂደታቸው *እንከን የለሽ* ናቸው ተብለው የሚታመኑ አገራት ምሳሌ ይሆኑን ዘንድ ዩናይትድ ስቴትስ አሜሪካን እና ሕንድን በጥቂቱ እንመልከታቸው:: የኪነ-ጥበብ ባለሞያዎች ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከፍተኛ እገዛ ያደርጉላቸው ነበር ወይም ፓርቲዎች የኪነ-ጥበብ ባለሞያዎችን ይጠቀሙ ነበር:: በአሜሪካ በቅርቡ በተደረገው ፕሬዝዳንታዊ ምርጫ፣ [ፕሬዝዳንት] ባራክ ኦባማ እና [ሴክሬታሪ] ሂላሪ ክሊንተን በከፍተኛ ደረጃ የሙዚቀኞችንና የተዋንያንን እርዳታ ጠይቀው ድምፅም ሆነ ዘርፈ ብዙ ድጋፎች ተችሯቸው ነበር:: የሚገርመው፣ [ለፕሬዝዳንት] ኦባማ የሪፑብሊካን ፓርቲ ፕሬዝዳንታዊ እጩ ተፎካካሪ ሆነው እርሳቸውን የተፎኳኮሯቸው *ሴናተር ጆን* ማኬይን፣ በተመሳሳይ ልክ እንደ አቻ ተፎካካሪያቸው ከፍተኛ የአርቲስቶች ድጋፍ ነበራቸው:: በተወሰኑ የምረጡኝ የቅስቀሳ ጉዞዎቻቸው ወቅት እንደነ ቶሚሊ ጆንስ ያሉ ተዋንያን እንዲያጅቧቸው ለማስደረግ ችለው ነበር::

በዚያ የአሜሪካ ፕሬዝዳንታዊው ምርጫ ወቅት ፕሬዝንት ኦባማ ፕሬዝዳንታዊውን *ሥ*ልጣን እንዲይዙ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጥረው ነበር ተብለው ከሚታመኑ ግለሰቦች መካከል ተወዳጇና *የቶክሾው* አቅራቢዋ ኦፕራ አንዷ ነች:: አሜሪካውያንና በተለይ አጋሮቿ የአሜሪካ *ታላቅ መሪ* የሚሏቸው ፕሬዝዳንት ሮናልድ ሬገን፣ ከሲኒማው ኢንዱስትሪ የወጡ የልዕለ-ኃያሏን አገር ፕሬዝዳንታዊ ሥልጣን ለመያዝ የበቁ መሪ ናቸው:: አገሪቱንም ለ8 ዓመታት መርተዋታል:: በየስክሪኑ ላይ ታንክና አውሮፕላን ሳይቀር በእጁ ሲገለባብጥ የሚታየው ግዙፉ አርኖልድ ሽዋዜንገር ዛሬ የፌዴራል አሜሪካ አካል የሆነችው ካሊፎርኒያ አገረ-ገዢ ለመሆን የበቃ ነው:: አገረ-ገዢ ሽዋዜንገርና ተዋናይ ጃኪ ቻን የቅጅ መብት ጥሰትን በመቃወም ቆንጆ ማስታወቂያ በቅርቡ መስራታቸው የሚታወስ ነው::

ሕንድን ስንመለከት፣ እንደ ሃሚታ ባቻህንና ደርሜንድራን ያሉ ታላላቅ የአገሪቱ ሲኒማ ክዋክብት፣ አገራቸውን ለማገልገል የፓርላማ ተመራጮች ሆነው ለተወለዱባቸው አካባቢዎች ዘላለማዊ አስተዋፅዖ ለማበርከት ችለዋል:: ዛሬ ከፍተኛ ተወደጅነት የተጎናጸፈው ሻሩክ ካህን፣ ያለውን የፖለቲካ አቋም በግለፅ ለማስቀመጥ ተቻለው ነውና፣ የሚሰራቸው ፊልሞች ከእናት አገሩ አልፎ በሌሎች አገራትም እጅግ ተመልካች ያላቸው እንዲሆኑ አስችሏቸዋል:: ምሳሌ ይሆን ዘንድ በቅርብ የሰራው «My Name is Kahan» የተሰኘው ፊልሙ፣ እጅግ ውጤታማ የሆነው ከቀናት በፊት የአገሪቱን ፖለቲካ እሰመልክቶ በሰጠው አስተያት ነበር::

እኛስ? የእኛስ አርቲስቶችስ? መቼ ነው *ፈታ* የሚሉት? ያኔ የዴሞክራሲ ፀሀይ እንደ አንዳች ቦግ ብላ በበራችበት የ1997 ዓ.ም ምርጫ፣ ቀላል የማይባል የአርቲስቶች ተሳትፎ ነበር:: ነገር ግን እንደማንኛውም ሰው፣ ለራሳቸውም ጨምሮ፣ ለውጥ ከመፈለግ አንፃር ብቻ እንጂ በርካታ ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ የዜጎች መብቶችንና ጥቅሞችን ከማስከበር አንፃር አመለካከታቸውን በይፋ ለሕዝብ በማሳወቅ አልነበረም የነበራቸው ተሳትፎ::

እነታማኝ በየነ፣ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ)፣ ንዋይ ደበበ፣ ደበበ እሸቱና ሌሎች መሰለል አርቲስቶች ያደርጓቸዋል እንዲሁም እያደረጉ ነው የሚባሉ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች፣ በመላዋ ኢትዮጵያ እየተስተዋሉ ካሉ ፖለቲካዊ ተሳትፎዎች ጋር አብሮ እንደ አንድ ተደምሮ የታይ እንጂ፣ በቀጥታ የአርቲስቱን ጥቅሞችና መብቶች ከማስከበር ጋር የሚገናኝ የነበረ አይመስለኝም::

ኢትዮጵያ በርካታ አርቲስቶችን ያፈራች ናት፡፡ የሙዚቀውና የፊልሙ ንግድ ደግሞ ምንም አይነት ድጋፍ የማይደረግለትና ጭራሹንም እንደ ቅንጦት የሚታይበት ጊዜ ላይ ነው የምንገኘ ው፡፡ አንድ ኢንቨስተር ኢንቨስትመንት ቢሮ ሄዶ ማበረታቻ ያላቸውና የሌላቸው ኢንቨስትመንቶች የሚለውን ሲያይ፣ በሚገርም ሁኔታ ምንም አይነት ማበረታቻ ከሌላቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች ውስጥ በጉልህ ተቀምጦ የሚያገኘው የሲኒማውን የኢንቨስትመንት ዘርፍ ነው፡፡

እሺ፣ ማበረታታት ሌላ ነገር ነው፣ አስፈላጊ አይደለም ብለን እንለፈው፡፡ ልክ እንደ አልኮል መጠጥ ንግድ፣ ልክ እንደ ሲጋራ ንግድ ጉጂ ነው ተብሎ ይታመን፡፡ የሲኒማ መሳሪያዎች ቀረጣቸው ከፍተኛ ይሁን፡፡ ይህ ችግር ጉጂ ቢሆንም በግድ እንቀበለው፡፡ ስለዝርፊያውስ!? በኢትዮጵያ የኮፒራይት ጉዳይ ላለፉት አስራ ምናምን ዓመታት ለኪነ-ጥበብ ባለሙያው ትልቅ ችግር፣ ትልቅ ስቃይ የሆነ ነው፡፡ የአገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች የምረጡኝ የቅስቀሳ ፕሮግራም ሲካሄድ፣ ከመልዕክታቸው ኋላና ፊት ሙዚቃን በማጀቢያነት ይለቃሉ፡፡ አንዳንዶቹ ራሳቸው አሰርተው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ጭራሽ ማንንም ሳያስፈቅዱ የታዋቂና የተወዳጅ ድምፃውያንን ስራዎች ለቅስቀሳቸው ይጠቀሙባቸዋል፡፡

እስካሁን እንደተመለከትኩት፣ አንዳቸውም የፖለቲካ ድርጅቶች የኪነ-ጥበብንና የኪነ-ጥበብ ሰዎችን ችግሮች የሚመለከቱ አጀንዳዎችን አንስተው ሲቀሰቅሱ አላዳመጥኳቸውም፡፡ በእርግጥ፣ እጅግ በርካታ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ያሉባት አገር ውስጥ እንደምንኖር የሚታወቅና ድብቅ የሆነ አይደለም፡፡ ጉዳዩን ያላነሱበት አመክንዮ ምናልባት እጅግ ጥቂት የቅስቀሳ የአየር ሰዓት ስለተሰጣቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም ደግሞ ከነአካቴው ኪነ-ጥበብ ብሎ ነገር አይጥማቸውና አይገባቸው ይሆናል፡፡

ላለፉት አስርት ዓመታት ሥልጣን ይዞ የቆየው ገዥው ግንባር (ኢሕአዴግ)፣ ለኪነ-ጥበብ ባለሞያዎችና ለሙያው ችግሮች የተዋጣላቸው መፍትሄዎችን ሰጥቷል ማለት በጭራሽ የሚቻል አይደለም፡፡ አልፎ አልፎ ለጥቂት ግለሰቦች ከተሰጡ ሽልማቶች እና የቀብር ሥነ-ሥርዓቶች አድማቂ የሆኑ ደብዳቤዎችን ከመፃፍ ውጪ አንዳች የተደረገ ነገር የለም ማለት ይቻላል፡፡ ኪነ-ጥበብ፣ ድግስ ከማድመቀ ውጪ ይህን ያህል ጉልህ ሚና ያላት የማይመስላቸው የመንግስተ ኃላፊዎች በየቦታው አሉ፡፡ ያለ ሙዚቃ፣ ያለ ሲኒማ፣ ያለ ቴአትርና ያ ሥነ-ጽሁፍ ትውልድ ማነፅ እንደማይቻል የማያውቁ በርካታ ኃላፊዎች አሉ፡፡

ምንም አይነት አሰተያየት ያልተደረገበት ይህ ዘርፍ፣ ወደፊት ምን አይነት እጣ ይጠብቀዋል? በአገራችን ከትውልድ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣ ሥነ-ቃል፣ ዜማ፣ ተረት ታንፃ እዚህ አንደደረሰች በርካታ ባለሥልጣናት የዘነጉት ይመስለኛል፤ አልያም ቀድሞውኑ አያውቁትም፡፡ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ፣ ባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ የኪነ-ጥበብ ባለሞያዎች ሀዘን ተደምጧል፡፡ አንዳንድ የኪነ-ጥበብ ባለሞያዎች ሞያቸውን እየተዉ፣ በኮንስትራክሽን እንቅስቃሴዎች እና ሰዎችን በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ ውጪ በማስወጣት (በአገራችን የወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ ተግባር) ተግባሮች እጃቸውን በማስገባት ላይ ይገኛሉ፡፡

የኪነ-ጥበብ ሰዎች አድርባይና ፈሪ እየሆኑ ነው፡፡ ሰርተው ከማደርና ካለማደር በሚመነጩ ፍርሀቶችና ጭንቀቶች ተሸብበዋል፡፡ ዛሬ ዛሬ የግል ሲኒማ ቤቶች ባላወጡት ገንዘብና በሌላቸው እውቀት የፊልሞችን አጀማመርና አጨራረስ እየወሰኑ እና ፕሮዲውሰሮች ገንዘብ ለመቆጠብ ሲሉ ብቻ ምንም አይነት የትወና ብቃትና እውቀት የሌላቸውን ዘመዶቻቸውን በስፋት እያሰሯቸው

ይገኛሉ። የፊልም ጥበብ አየሞተ ነው። ታዲያ ማነው ይህን ሕብረተሰብ፣ ይህን ተስፋ የቆረጠና እየደከመ የመጣን የኪነ-ጥበብ መንደር ነፃ የሚያወጣው?

የኪነ-ጥበብ የሞያ ማሕበራት የማይካድ ትልቅ እንቅስቃሴ እያደረጉ መሆናቸው ግልፅ ቢሆንም፣ አቋም ይዘው የፖለቲካ ፓርቲዎችን መጠየቅ አለባቸው የሚል ምልከታ አለኝ። በርካታ የኪነ-ጥበብ ሰዎች አሉን፤ በርካታ ዘፋኞች፣ ሙዚቀኞች፣ በርካታ ቴአትረኞች፣ በርካታ የፊልም ባለሙያዎች፣ ተወዳጅ ተዋንያን አሉን። የአገሪቷን ሕዝብ ሥነ-ምግባር በማነፅ፣ በማዝናናት፣ የአገር ፍቅርና ወኔ ወደ ላይ እንዲመነደግ በመቀስቀስ ከፍተኛ ስራ ሲሰሩ የኖሩና እየሰሩ ያሉ በርካታ የጥበብ ሰዎች አሉ።

ቀላል ያልሆነ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉ፣ በቀላሉ የሕብረተሰቡን አመለካከት ሊለውጡ የሚችሉ የጥበብ ሰዎች በአገሪቷ አሉ። እነዚህ ሰዎች ጥያቄዎች የቀረጥ መቀነስ ጉዳይ አይደለም። በእርግጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያተኮሩት ቀረጥ በመቀነስ ላይ መሆኑን የሚቃወም የለም። የሕክምና ትምህርት ወዘተ የሚባሉት አጀንደዎች ለሰው ልጅ አስፈላጊ ናቸውና መነሳታቸው ተገቢና አስፈላጊ ነው። ግና፣ የሰብዓዊ ፍጡር መብቶች የሆኑት ሰርቶ የማደር መብት፣ በትክክለኛ መንገድ ኃብት የማካበት ነፃነት ወዘተ፣ በኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች በተግባ ላይ ሲውል አይታይም።

ስለሆነም፣ ከላይ ያነሳሁዋቸው የሞያ ማሕበራት ገዢውንም ሆነ ተቃዋሚ ድርጅቶችን አስፈላጊና ወሳኝ የሆኑ ጥያቄዎችን የሚጠይቁበት ጊዜ አሁን ይመስለኛል። ማንን ነው የኪነ-ጥበቡ ቤተሰብ መምረጥ ያለበት? መብቱ የሚከበረው ማን ሥልጣን ቢይዝ ነው? ያለፍርሀት ሀሳቡን የሚገልፀው ማን አገሪቱን ቢመራ ነው? የሚሉ ጥያቄዎች መጠየቅ አለባቸው።

አዎ! ማንን እንምረጥ? ማን የኛን ጥቅም ያስከብራል? ማን ከአደባባይ ዝርፊያ ነፃ ያወጣናል? ማን ከቀረጥ ጫናና አላስፈላጊ ወጪዎች ከለላ ይሰጠናል? ማን . . . ???

## እኔ የምለው

# የወንድ አፅም ያለህ!

**በሊዮ**

አንዳንዴ ግን እንዲያው ዝም ብሎ አይገራርማችሁም። የሆነ በወንዶች ላይ ጭቆና ነገርማ አለ። እስቲ ተመልከቱ ሀገር የምትጠራው በሴት ነው። ጥሩ ነገር ስናይ የምናቆላምጠው «አንቺ» እያልን ነው። አቦ አንተ የሚባል አገር ይኑረን እንጂ። ልብ ብላችሁ ከሆነ በሀገራችን የሚገኙት እድሜ ጠገብ አፅሞች ሁሉም ሴቶች መሆናቸውን ልብ ብላችኋል? ኧረ ስላምን ያገኛ ችሁ አርኪዮሎጂስቶቻችን ሰለሞንንም ፈልጉ እንጂ! ነው "affirmative Action" በአፅሞችም ዘንድ መኖሩ ነው። ካለም እውነቱን ንገሩን።

አንድ ወዳጄ ፀጉሩን አሳድጎ ሁለት ጆሮውን ተበስቶ አግኝቼው «ጨዋ ተበላሸ» ብዬ ክው ብል «ምን ላድርግ በየሄድኩበት ቢሮ ቅድሚያ ለሴቶች እያሉ ተጠባባቂ መሆን ሰለቸኝ እንዲህ ሆኜ ልሞክረው ብዬ ነዋ» አለኝ «ሣቅ» ሳልል፣ ስቅም ሳይለኝ ጭጭ አልኩኝ። ወንዱ እኮ ቀሚስ

መልበስ ነው የቀረው ብሎ ቦተሊካ ከመንዛት በፊት ቀርቦ እንደ እኔ ምክንያት መጠየቅ ጥሩ ነው አልኩኝ፡፡

ጉራማይሌ ነገር እየበዛ አስቸግሮኛል፡፡ ሻይ የሚያዝ ሰው አስተናጋጁን ተጣርቶ «ወተት የሌላው ሻይ አምጪልኝ» ብሎ ግራ ማጋባት ምንድነው? ጉርደን ያልገባበት ቀዝቃዛ ቢሮ እንደማለት እኮ ነው፡፡ ሆሆሆ!!! ነዳጅ ሲጨምርና ኑሮ ሲወደድ አማርኛውም እየናረ ይሆን? «ኢንደገና» የሳምንት ሰው ይበለን፡፡

## ግጥም

**ትካዜ**

እንኳንስ የደላው የቸገረውም
ካለም መነጠሉን የሚወድ የለም፡፡
ቢደሰት ቢከፋ ቢስቅ ቢተክዝ
ይመርጣል በዓለም ላይ ቆሞ መታረዝ፡፡
ሄዶ ከሚደሰት ከማያወቀው ሥፍራ
ይመርጣል ሥቃዩን ዓለም ካንቺ ጋራ፡፡
በማያውቀው ዓለም ብዙ ተድላ ከሚያይ
ሰው ከዚህ ዓለም ጋር ይወዳል ቢሰቃል፡፡

**ሙዚቃ**

በዓይን አትታይ በእጅ አትዳሰሺ
የሕይወት ጠበል ስሜትን ፈዋሽ
ተጠለሽ የነጠርሽ ረቀት ሙዚቃ
በደም ተሰራጭተሽ ስሜትን ማራኪ
የሊቆች ፍትፍት ነሽ ላንቃ የማትነኪ፡፡

***የከርቸሌ ግጥሞች***
***ከጌዲዮን ወልደአማኑኤል***
***(የዓለም በቃኝ ግጥሞች)***
***ግንቦት 1996***

## ቅንጭብጭብ

የመኖርና ጤነኛ የመሆን ጉጉቷ ከፍተኛ ስለበር ለመጀሪያ ጊዜ በወርልድ ዋይድ ኦርፋንስ ፋውንዴሽን በተባለ የአሜሪካ ድርጅት ኢትዮጵያዊ የህክምና ባለሙያዎች ድጋፍ የፀረ ኤድስ መድኃኒቶቹን ስትወስድ ፊቷ ላይ ፈገግታ የማይታይበት ጥግ አልነበረም፡፡ እጅግ በጣም ተደስታ ነበር፡፡ ፍንክንክ፣ ፍንድቅድቅ ብላ ነበር፡፡ እንደምትድን ተስፋ አድርጋ ነበር፡፡ … ነበር… ነበር …ነበር፡፡

በድንገተኛ ኃይለኛ የደም ግፊት ምክንያት እጆቿን መጠቀም አቃታት፡፡ እግሮቿም አልታዘዝ አሏት፤ ያለሰው ድጋፍ መራመድ ተሳናት፡፡ በ1998 ዓ.ም ጥቅምት መጀመሪያ ላይ ህመሟ ፀንቶባት ዘውዲቱ ሆስፒታል ተኛች፡፡

ደብዳቤ መፃፍ የማይታክቱት ቀጫጭን ጣቶቿ ከአእምሮዋ ጋር ጥሩ ቅንጅት መፍጠር እስኪሳናቸው፤ ብዕሩን ጨብጠው መያዝ እስከሚያቅታቸው ህመሟ ከባድ ነበር፡፡ ከዚህ የሚከተለው አጭር መልዕክት በብዙ ትግልና ስቃት መስመሮቹን ስታና ቃላቶቹን አደራርባ እንደነገሩ ጽፋዋለች፡፡ ፊደሎቹ ከሌሎች ደብዳቤዎቿ በተለየ ሁኔታ ትልልቅ ናቸው፡፡ ይህቺን አጭር መልዕክት ለመፃፍ ብዙ እንደደከመች በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡ አንድ ፊደል ለመጻፍ ብዕሯን ወረቀት ላይ ማንሸራተት እጅግ ከባድ ነገር የመግፋት ያህል ፈታኝ እንደሆነባት የፊደል አጣጣሏ ይመሰክራል፡፡ ይህን ያላለቀ ዓረፍተ ነገር ለመጻፍ ያለተን ትንሽ አቅም አንጠፍጥፋለች፡፡ በመጨረሻም አቅቷት ትታዋለች፡፡

. . .ባልተለመደ ሁኔታ ፀጥ ማለቷን አስተዋለች፡፡ የሚከብድና የሚያስፈራ ግርማ ያለው ፀጥታ በአመለዘውድ እጅግ የመነመነ ሰውነት ላይ ረብቧል፡፡ እንደሞተች አወቀች፡፡ ያልጠበቀችው ነገር አልነበም፡፡ አመለዘወድ የነበረችበትን ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ባለፉት ጥቂት ቅናት አይታለች፡፡ ቀደም ሲል አመለዘወድ እግዚአብሔር እንደሚምራትና እንደምትድን ታምን ነበር፡፡ ያ እምነቱ ባለፉት በርካታ ሳምንታት ባየችው ከቀን ወደቀን እየባሰ በመጣው የአመለዘወድ የጤና ችግር ተሸርሽሯል፡፡ ከአንድ ሳምንት በፊት ዘውዲቱ ሆስፒተል ተኝታ እየታከመች ነበር፡፡ እዚያ ያሉት ሀኪሞች ህይወቷን ማቆየት እንደማይችሉ ስለተገነዘቡ ነበር ከሆስፒታል እንድትወጣ የወሰኑት፡፡

...ለመኖረ የነበራትን ጉጉት፣ ለወንድሞቿ የነበራትን ፍቅር፣ ሌሎች ሀጻናትንም ለመገሰጽና ጥሩ ልጆች እንዲሆኑ ለማድረግ ምን ያህል ትደክም እንደነበር አስታወሰች፡፡ ሙት ለታማሚዋ ትልቅ እረፍት ቢሆንም አዘነች፡፡ ነፍሷ በዚህች ዕለት ወደ ገነት እንደገባች ከልቧ አመነች፡፡ እምነቷ አጽናናት፡፡ አመለዘውድ ማረፏን ለዶክተሯ ልትነግራት በእርጋታ ከክፍሉ ወጣች፡፡

**ያልተኖረ ልጅነት**
**(እውነተኛ ታሪክ) - እዮብ ጌታቸው - 2001 ዓ.ም**

## *ቃለምልልሶች*

# «ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የአንድ ፓርቲ የግል ንብረቶች አይደሉም»

*አርቲስት ደበበ እሸቱ*

«... *ፖለቲካ ሁልጊዜ መወራት የለበትም፡፡ ስለዴሞክራሲ፣ ነፃነት፣ ርዕዮተ ዓለም፣ ሰብአዊ መብት ይሰበካል፡፡ የሕብረተሰቡ መብቶች ናቸው፡፡ ስለእነዚህ ነገሮች የሚናገር በሙሉ እኮ ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት የአባልነት ፎርም የሞላ ነው ማለት አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ* ...» ይህ ንግግር ባልደረባችን ውብሸት ታዬ *"ብዙ ኢትዮጵያውያን በአገራችን ፖለቲካ ውስጥ ያለን ተሳትፎ ቀዝቃዛ*

*የሆነው ለምንድነው?"* ሲል ላቀረበለት ጥያቄ አንጋፋው አርቲስት ደበበ እሸቱ ከሰጠው ምላሽ ተቀንጭቦ የተወሰደ ነው:: ሙሉውን ቃለ-ምልልስ እነሆ!

***ከቲያትር መድረክ ላይ ከጠፋህ እንደቆየህ ይነገራል:: የፖለቲካ ተሳትፎህም የቀዘቀዘ ይመስላልና በአሁኑ ወቅት ምን እየሰራህ እንደሆነ ለአንባቢዎቻችን ብትገልጽልኝ? የጤንነትህ ሁኔታስ ምን ይመስላል?***

በጤንነቴ በኩል በአንድ ኢትዮጵያዊ ፊዚዮቴራፒስት ሕክምናዬን እየተከታተልኩ ነው:: በተረፈ እረፍት ላይ ነኝ:: እረፍት ላይ ሆኜ ግን ሁለተኛው መጽሐፌን ለማሳተም እየተዘጋጀሁ፣እንዲህ እንዳሁኑ ደግሞ ቃለ-ምልልሶችን እየሰጠሁና በማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ እየተሳተፍኩ እገኛለሁ::

***የምታዘጋጀው መጽሐፍ በምን ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን ነው?***

የመጀመርያው መጽሐፍ ተከታይ ክፍል ነው:: የመጀመርያው የ1997 ዓ.ም ምርጫ እና እስር ቤት እስክንገባ የነበረውን ሂደት የሚሸፍን ነበር:: ሁለተኛው መጽሐፌ ደግሞ ከተፈታን በኋላ የነበረውን ሁኔታ የሚያትት ነው:: እኔ በካናዳ የቅንጅቱ ወኪል ሆኜ ሄጄ ስለነበር በዚያ የተነሱትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ባህርይ የመዳሰስና ፓርቲው በመፈራረስ ላይ ስለነበር «ምን ተፈጠረ?» የሚለውን ለመመለስ ነው:: እንደሕዝብ ግንኙነቴ ከተረዳሁት፣ ከተመለከኩት፣ ካሳለፍኩት ሂደት አኳያ ያለውን ይይዛል:: ወደዚህ ልመጣ ስል አስቀድሜ እዚያው ያለችውን ልጄን ለመጠየቅና በእስሩ ወቅት በጣም ትጨነቅልኝ በነበረችው እህቴ ዓለምፀሐይ ወዳጆ ወደ ዋሽንግተን እንድመጣ ተጋብዤ በሄድኩበት ወቅት እዚህ ላለው የድጋፍ ጨ ቡድንና ለአንዳንድ ኢትዮጵያውያን መድረክ ተዘጋጅቶ «ጥያቄዎች ብትመልስ» አሉኝ:: እሺ ብዬ ተዘጋጀሁ:: እዚያ የተነሱ ጥያቄዎች ቁልፍ ቁልፍ ጥያቄዎች ነበሩ:: እዚያ የተመለከትኩት ነገር ቢኖር ብዙ ያልተመለሱ ጥያቄዎች እንዳለ ያሳየ ነበር:: መጽሐፌ እነዚህን ሁኔታዎች የዳሰሰ ነው::

***ከዚያ በኋላ ያለውስ? የአንድነት ፓርቲ መመስረትና ክፍፍሉ?***

እዚያ እያለሁ የፓርቲው ሊቀመንበር ሆና የተመረጠችው ወ/ሪት ብርቱካን ደውላ «ለምስረታው ለምን አትመጣም?» ብላኝ ነበር:: በእርግጥ በምስረታው ላይ አልደረስኩም እንጂ ድጋፌን ግን በኢሜይል አስታውቄያለሁ:: ወደ አገሬ ስመለስ ወደ ፓርቲው ጽ/ቤት ሳልሄድ እቤቴ ነበር የተቀመጥኩት:: በወቅቱ ጋሽ መስፍን [ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም]፣ ብርቱካን፣ ታምራትና ሌሎችም ሆነው እቤት ድረስ በመምጣት እንኳን ደህና መጣህ አሉኝ:: ከዚያ በሊቀ መንበሯ ግብዣ ቢሮውን ተመለከትኩ:: እና በሌላ ጊዜ ብርቱካን «እንግዲህ ከመጣህ ኤዲቶሪያል ቦርዱን አንተ ያዝልኝ፣ በእርግጥ ደመወዝ አንከፍልህም» ስትለኝ «እሺ ግን በጉዳዩ ላይ ብሔራዊ ም/ቤቱ ይወስንበት» ባልኳት መሰረት ብሔራዊ ም/ቤቱ አስቀድሞ ያውቀው ስለነበር ወስኖበት ስራውን ጀመርኩ:: ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በነበርኩበት ኃላፊነት ይቀርቡ የነበሩ የመርሕ መከበር ጥያቄዎችን

እንደሽማግሌም፣ እንደኃላፊም ለመፍታት መሞከሬን በኋላም የሂደቱ አካል ሆኜ ከፓርቲው ተባራችኋል እስከምንባልበት ጊዜ ድረስ ያለውንና ሌሎቹንም ያካትታል፡፡

***አንተ የበለጠ በምትታወቅበት የቴአትር መድረክ ላይ እንዳትገኝ ካደረጉህ ነገሮች አንዱ በፖለቲካ አቋምህ የተነሳ የተፈጠረው ስጋት መሆኑን አንብቤያለሁ፡፡ በስነ ልቦናህ ላይ የፈጠረብህ ጫና አለ?***

በስነ ልቦናዬ ላይ የፈጠረብኝ ምንም ችግር የለም!/በእርግጠኝነት ስሜት ቀና ብሎ/፡፡ እውነቱን ነው መነጋገር ያለብን፡፡ የዚህ መንስኤው አንዳንድ ወዳጆቼ በእስሩ ወቅት ስላልጠየቁኝ «ምን ይለናል?» በሚል አስተሳሰብ የተከሰተ ነው፡፡ እኔም ይህንን ለማጥበብ የተቻለኝን ሁሉ እያደረግሁ ነው፡፡ እኔኮ ይገባኛል ችግራቸው፡፡ እንዴ… እኔስ ብሆን ተመሳሳይ የፖለቲካ ውዝግብ ሁኔታ ተፈጥሮ ቢታሰሩ እጠይቃቸው ነበር? እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ጓደኝነት ሌላ ነገር ነው፡፡ እነዚህ ጓደኞቼ በክፉም በደጉም ቀን አብረውኝ የነበሩ ልጆቼን አንቀባረው የዳሩልኝ ናቸው፡፡ የፖለቲካ አቋማችን የየራሳችን ነው፡፡ እና ይህን ይመስላል፤እንደዚህ ቢቀበሉት ደስ ይለኛል፡፡

***የራሳቸው የሆነ የፖለቲካ አቋም ያላቸውና ይህንኑ አቋማቸውን ያለፍርሃት የሚያንፀባርቁ በርካታ ዜጎች እንዳሉ ያታወቃል፡፡ በሌላ በኩል ግን የአገራችንን አርቲስቶች ጨምሮ ቀላል የማይባል ቁጥር ያለን ዜጎች ለፖለቲካው ያለን አመለካከት ቀዝቃዛ እንደሆነ ይገለጻል፡፡ ለምንድነው ትላለህ?***

እንግዲህ ጥበብ እኮ መግባባት፣ መነጋገርና ግልጽ መሆንን ይጠይቃል፡፡ ለአንዳንዱ ፖለቲካ የሚያስፈራበት የገዢው ፓርቲ አካል ካልሆንን ህልውና አይኖረንም በሚል ይመስለኛል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ እናንተም አስተማሪ ሥራዎችን ብትሰሩበት፣ ብትተቹበት መልካም ነው፡፡ የሰለጠነው ዓለም የፖለቲካ ምልከታ እኛምጋ መምጣት አለበት፡፡ ፖለቲካ ሁልጊዜ መወራት የለበትም፡፡ ስለዴሞክራሲ፣ ነፃነት፣ ርዕዮተ ዓለም፣ ሰብአዊ መብት ይሰበካል፡፡ የሕብረተሰቡ መብቶች ናቸው፡፡ ስለእነዚህ ነገሮች የሚናገር በሙሉ እኮ ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት የአባልነት ፎርም የሞላ ነው ማለት አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ የሚያምንበት የፖለቲካ አስተሳሰብ፣ የሚከተለው መስመርና ዕውን እንዲሆን የሚመኘው የስርዓት ቅርጽ አለ ማለት ነው፡፡ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የአንድ ፓርቲ የግል ንብረቶች አይደሉም፡፡ እነዚህን መብቶች መጠየቅ ማንንም ሊያስቆጣ አይገባም፡፡ ራሳችን የምንፈጥረው የአስተሳሰብ ችግር ነው፡፡…

***…በእርግጥ «ራሳችን የምንፈጥረው ችግር ነው» ሊባል ይችላል? ወደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ የገዢው ፓርቲ ባለሰልጣናት በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን የተቃውሞ ፖለቲካ ፓርቲዎች በመሉ በአንድ ጫማ ውስጥ አቁመው «ኪራይ ሰብሳቢዎች ናቸው» ይሏቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በራሱ የሚፈጥረው አሉታዊ ተፅዕኖ አይኖርም? ጠ/ሚ/ሩ በቅርቡ ለፓርላማው ባቀረቡት ሪፖርት ለተቃዋሚዎች በሰጡት ምላሽ የኢህአዴግ ሊቀመንበርነትና የጠ/ሚኒስትርነት ጉዳይን እስከ አምስት ዓመት መጠበቅ ግድ መሆኑን ከመግለጽ በተጨማሪ ከምርጫው በኋላ «አሁን እየተሰሩ ባሉ ጥፋቶች» ላይ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ገልፀዋል፡፡ እነዚህና የመሳሰሉት ራሳችን የምንፈጥራቸው ስጋቶች ናቸው የሚባሉት እንዴት ነው?***

ይህን ጉዳይ [የጠ/ሚ/ሩን] ከቲአትር አንፃር እንመልከተው:: ቲአትር ሲሰራ ተዋናዮቹ በማሕበረሰቡ ውስጥ ያሉ ችግሮችን እንዴት በውይይትና በመግባባት መፍታት እንደሚቻል እናሳያለን:: እሳቸውም የፓርላማውን መድረክ ሲይዙ ይህንን ነው ማድረግ የሚጠበቅባቸው:: አገርን ከሚገዛ አካል ይህንን ነው መማር ያለብን:: አንድ ገፀ ባህሪ ገር፣ አዋቂ፣ ይቅር ባይ ከሆነ ይገነባል:: እኩይና ተንኮለኛ ከሆነ ተፅዕኖ እንዳያደርግ ሌላው ገፀ ባህሪ እየተጫነው ወደመልካም ሊመልሰው ይገባል:: እኔ ከመንግስት ይህን እጠብቃለሁ:: ቲቪ ስመለከት የምቃወማቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢሆኑ እንኳ ጥሩ ሲናገሩ እርካታ አገኛለሁ:: ፀያፍ ሲናገሩ አፍራለሁ፣ እሸማቀቃለሁ:: ሁሉም ይሸማቀቃል:: ኢትዮጵያ ታፍርባቸዋለች:: ለምን ይህችን እናት አገራችንን እናሳፍራት? እናሸማቃት? ልምዳችንን በአዎንታዊ ጎኑ ማካፈል አለብን::

*ስለ ልምድ ካነሳህ.. አንተ እንግዲህ በሶስቱም መንግስታት በመስራት ትታወቃለህ...*

የምን ሶስት መንግስታት? አምስት ነው እንጂ! የጃንሆይ አለ፣ የመንግስቱ ንዋይ አለ... አንድ ቀንም ቢሆን (እየሳቀ) ከዚያ ደግሞ የደርግ መንግስት አለ:: ከዚያ ግንቦት ስምንት ሊገለበጥ የተሞከረው አለ:: ይሁን ብቻ ሶስት መንግስት ልበልልህ::

*በንጉሱ ጊዜ ጋዜጠኛ ነበርክና በወቅቱ የነበረውን አቀራረብ ከሌለቹ መቼቶች ጋር በማነፃፀር እንዴት ትመለከተዋለህ?*

«ሾኬ» የምንለው አቀራረብ ነበረን:: በግሌ የማሳትማት «ቁም ነገር» የምትሰኝ መጽሔትም ነበረችኝ :: አሁን ያለው አይደለም:: አሁን ያለው «ቁም ነገር» ስሟን ወስዶ «አመሰግናለሁ» እንኳ አላለኝም:: የሆነ ሆኖ «ሾኬ» የሚባለው አቀራረብ እዚሁ አገር የተፈፀመውን «በሌላ አገር የተፈፀመ» በማለት ነበር የምናቀርበው:: አንባቢው ወይም አድማጩ «የሌላ አገር ፖለቲካ፣ ክንውን» እያለ ይማርበት ነበር:: ደርግ... ለተወሰነ ጊዜ መጽሔቶች ፈቀደና በኋላ እንደምንም ብሎ አድበስብሶ አጠፋቸው:: ፀደይ፣ ቁም ነገርና ሌላ መጽሔትም ነበሩ:: ጋሽ ስብሐት [ስብሃት ገ/እግዚአብሄር] ከእኔ ጋር ይሰራ ነበር::

*ደርግ አስሮህ እንደነበር ሳታነሳ ዘለልከውኮ:: ለምን ነበር ያሰረህ?*

.../እየሳቀ/ ምንድነው ያኔ የሆነው መሰለህ... ጋሽ ፀጋዬ [ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን] በመሾሙ ሰልፍ ወጥተን ነው:: ጋሽ ፀጋዬ ቲአትር ድርሰት ፀሐፊ ነው:: ወሰዱና ባሕል ሚ/ር ባለስልጣን አደረጉት:: የቴአትር ድርሰቱ ቆመ:: ስለዚህ እኛ ተጎዳን:: እሱ ደግሞ አንዳንድ ሰዎችን ብሔራዊ ቲአትርን ይጠቅማሉ በማለት አስቀመጠ:: ... ድርሰቱን ትቶ! ያንን ተቃውመን ሰላማዊ ሰልፍ ወጣን:: በሌላ በኩል ደግሞ የመንግስት ቋሚ ሰራተኛ እንድንሆን ያለበለዚያ በማሕበር እንድንደራጅ ይፈቅድልን የሚል ነው:: የቲአትር ቤት ሰራተኛው ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ ግብር ይከፍላል:: ቋሚ አልነበም፣ ጡረታም አልነበረውም:: ወይ በማሕበር አልተደራጀም:: እና ፀጋዬ

ገ/መድህንን አትሹሙብን ይፃፍ የሚልና እሱ ያስቀመጣቸው ሰዎች እያበላሹ ነው፣ የሰራተኝነት መብታችንም ይጠበቅ ብለን ወጣን::

***በወቅቱ ሰላማዊ ሰልፍ ክልክል ነበር :: እንዴት ደፍራችሁ ወጣችሁ? በወቅቱ በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍም አንድ ሰው መገደሉን የሰማሁ ይመስለኛል፤እያይዘህ ብትመልስልኝ?***

አዎ ሰላማዊ ሰልፍ ክልክል ነበር:: ጉዳዩን አስረድተን አስፈቅደን ነው:: በእርግጥ እኔ በሰላማዊ ሰልፍ ፈቃድ ጥየቃው ወቅት አልነበርኩም:: በወቅቱ እነዚያ ጋሽ ፀጋዬ ያስቀመጣቸው ሰዎች ቲአትር ቤት እየሰራ መጽሔትም ያሳትማል ስለዚህ ገቢው ለቲአትር ቤቱ ይሁን በማለት ተቃውሞ አስነስተው ስለነበር ትቼ ወጥቼ ነበር:: ከአዲስ አበባ ወጣ ብዬ ስመለስ ብሔራዊ ቲአትር ወረቀት ተለጣጥፎ ግርግር ሆኖ ደረስኩ:: ይህማ ቤቴ ነው እኔም አለሁ ብዬ... ለመጽሔቴም ወሬ እንዲሆነኝ ካሜራዬን ይዤ ወደሰልፉ ሄድኩ:: በአገር ፍቅር አራት ኪሎ አድርገን ባሕል ሚ/ር ሄድን:: እንግዲህ እዚያ በተፈጠረው ግርግር ነው ጥይት ተተኩሶ አንድ ልጅ የሞተው:: እኔና ወጋየሁ ንጋቱ አምልጠን አንድ ጽ/ቤት ተሸሸግን:: ከሶስት ቀን በኋላ ወጋየሁ ቤት እያለን እሱን መጥተው ሲወስዱት እኔንም ማሰር አለባችሁ ስል «ያንተ ዝርዝር የለም» አሉኝ:: በኋላ መጽሔቴን ላሳትም ብርሃንና ሰላም እያለሁ ሁለት ሰዎች ይከታተሉኛል:: አንድ የሺጥላ የሚባል ሰው «እነዚህ የደርክ ሴኩሪቲዎች ሳይሆኑ አይቀሩም የሚከታተሉህ አንተን ነው:: » ሲለኝ እዚህማ አልያዝም ብዬ ቢሮዬ ሄድኩ:: ያሉኝን ነገሮች አደራጀሁ:: በኋላ ደውለው «ና» ሲሉኝ «በስልክ ተጠርቼማ አልሄድም፤ ከፈለጋችሁ መጥታችሁ ወሰዱኝ» አልኳቸው:: እና መጀመርያ 3ኛ ሻለቃ ከዚያ 4ኛ ክ/ጦር አንድ ሶስት ወር ቀምሰን ወጣን::

***እንድትወጡ የታዘዘበትን ደብዳቤ የፃፈው ማን ነበር?***

ጠ/ሚ/ር ፍቅረ ስላሴ ወግደረስ ነበር::

***በ1997 ዓ.ም እስር ወቅት ቃሊቲ ማረሚያ ቤት ስትገናኙ ስለእስሩ አነሳችሁ?***

አዎ:: እና «ልክ ነበርኩ» አለኝ:: ደግሞም ልክ ነው /በምፀት/ የመንግስት ተሳሳች የለውም:: ቢሳሳትም አይሳሳትም::

***ወደ ምርጫ 97 ልመልስህ:: እንደማስታውሰው በአንተ ላይ አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ትኩረት ተደርጎብህ የነበረ ይመስላል:: ባልታወቁ ግለሰቦች ድብደባ ተፈጽሞብህ እንደነበርም በወቅቱ ተዘግቧል:: ለምን ነበር?***

ምላስ አበዛሁ መሰለኝ /እየሳቀ/ እንግዲህ እኔ የቲአትር ባለሙያ ነኝ:: ስለዚህ ለሕዝብ ሊቀርቡ የሚገባቸው ነገሮች እንዴት ሆነው መቅረብ እንዳለባቸወ ሙያዬ አስተምሮኛል:: ሳቀርባቸውም «ድራማታይዝ» እያደረኩ ነው:: እውነቱን ለመናገር የኢህአዴግ ካድሬዎች የነበሩ ሰዎች ሁሉ

/በድብቅ/ መረጃ ይልኩልኝ ነበር። ቢሮ ስገባ በፖስታ የተላከ መረጃ አገኝ ነበር። እነዚህን ሰብስቤ ለሕዝብ ሳቀርብ መራቀቅ የሌለበትና እውነታን የተላበሰ ስለሆነ ተጠንቅቄ ነበር የማቀርበው። በዚህ ቁጭት ይመስለኛል ትንሽ የተጎሻሸምኩት።

***አሁን እየተካሄደ ያለውን የፖለቲካ ፓርቲዎች ክርክር እንዴት አገኘኸው? የተከራካሪዎቹ ብቃትስ ምን ይመስላል?***

እ... እንግዲህ ምንም ሆነ ምን እውነት ነው መናገር የሚያስፈልገው አይደል? እንደተከራካሪ ከሆነ ከልደቱ ሌላ ተከራካሪ አላየሁም። ሌሎቹ አቀራረባቸው እጅ የመስጠት አይነት ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ፓርቲዎች የየራሳቸው አደረጃጀትና ብቃት ሊኖራቸው ይችላል። በምርጫ ክርክር ወቅት ግን ለመራጮቻቸው ይህንኑ ብቃታቸውን የሚያሳዩበት አሳማኝ መከራከሪያና ክርክሩ በሚደረግበት የሙያ ዘርፍ በሳል ተከራካሪ ማቅረብ ተገቢ ይሆናል።

***የእስር ቤት ቆይታችሁ የበለጠ እንድትቀራረቡና የተሻለ ቅርጽ ላለው የፖለቲካ ትግል ያነሳሳችኋል የሚል ግምት አሳድሮ ነበር። ውጤቱ ግን እንደሚታወቀው ሁሉ የውስጥ መከፋፈላችሁን አሸንፎ መውጣት እንኳ ያቃተው ሆኗል። በግልህ መንስኤው ምንድነው ትላለህ?***

ሹመትና ምርጫ የተለያየ ነገር ነው። ዴሞክራሲያዊ በሆነ ስርአት ውስጥ ገብተን ለመስራት፣ ዴሞክራሲያዊነት በሕዝቡ ውስጥ እንዲያብብ ለማድረግ ፈቀደን ገብተናል ነው የተባለው።- ከጅምሩ። ወደተግባር ሲገባ ግን አንዳንዶቻችንን የሚጎዳ ሆኖ ተገኘ። ትልቁ ችግር ይኼ ነበር። በመንግስት ተሹሞ ስልጣን ላይ ለረዥም ጊዜ የቆየ ሰው በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተመርጦ በአንድ ወንበር ላይ እኩል ተጠየቅ ስትለው፣ስትሞግተውና ስትናገረው አይቀበልም። ይህ ሁኔታ ከቅንጅት መከፋፈል በኋላም አንድነት ውስጥ መጣ። አገርን ሕዝብን እንመራለን ብሎ የተነሳ አካል በድርጅቱ ውስጥ ችግር ተፈጥሯል፣ ስህተት ተፈጽሟል ሲባል ችገሩ ምንድነው? ስህተቱስ ምን ላይ ነው? ብሎ በመጠየቅ ፈንታ «ቀኝ አክራሪ፣ ግራ አክራሪ፣ የኢህአዴግ ወኪል፣ ተለዋጭ...» መባል ተጀመረ። ይህ ታርጋ መለጠፍ ከደርግ ጀምሮ የነበረ ያረጀ የካርታ ጨዋታ ነው። የሚሻለው በችግሩ ላይ በአግባቡ ተወያይቶ ወደፊት መቀጠል ነበር።ወጣቱ ምን ያውቃል? የምንለው ነገር አለን። ምን አሳወቅነውና መጀመርያ? መች አቀፍነው? አንድነት ውስጥ ይህ ነበር የተፈጠረው። ወጣቶች ለስልጣን መብቃት አለባቸው የሚባለው ብቻውን በቂ አይደለም። ወጣቶችን አሰባስቦና አብቅቶ አደራ ተረካቢ ማድረግ ከእኛ እግዚአብሔር እድሜውን ከቸረን ሰዎች የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው።

***በወቅቱ ከአንድነት ፓርቲ ተባረሩ የተባሉት አባላት ባለፈው ሳምንት በጠሩት ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ተ/ም/ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡት የ80 ዓመቱ አዛውንት ፕ/ር መስፍን ናቸው። በእርግጥ የፖለቲካ መሪነት የዕድሜ ገደብ ሊደረግበት ይገባል የሚል መርሕ/ለአዛውንቶች/የለም። በተግባር የታየው ይህ ተሞክሮ ግን ለወጣቶች ቦታ መልቀቅ ይገባል በሚል ስታራምዱት ከቆያችሁት መርሕ ጋር አይጣረስም?***

አንድ ከላይ ሆኖ ልምዱን የሚያካፍል፣ የከረረውን የሚያረግብ፣ የለዘበውን የሚያጠነክር አንድ ሰው ያስፈልጋል ተብሎ ነው:: ከዚህም አልፎ መሪያችን ወ/ሪት ብርቱካን ከታሰረችበት ጊዜ አንስቶ የነበሩ፣ በመሆኑ የእሷ አደራ አለብዎት ተብለው አባላቱ ለ45 ደቂቃ ተንበርክከው ለምነዋቸው «በምንም ተአምር አልሆንም እኔ የዲሲፕሊን ሰው ነኝ ከእኔ ጋር መስራት አትችሉም» ብለው በስንት ልመና ነው የተቀበሉት:: ፈልገውት አይደለም::

*ጉባኤውን የጠራው ወገን የሚቀርብበት አንዱ ትችት ተገቢውን ሂደት ተከትሎ መፍትሄ ከመሻት ይልቅ ወደ ፍጥጫ የሚያመራ መንገድ መርጧል የሚል ነው:: በእርግጥ ለሽምግልና ቡድኑ አዎንታዊ ምላሽ አሳይቷል:: በሌላ በኩል ግን ቀደም ሲል የገለፅከው ዴሞክራሲያዊነት ከሚተገበርበት መንገድ አንዱ የአብላጫ ድምጽ ስርዓት ነው:: አጠቃላይ ጉባኤው ለመረጠው ብሔራዊ ም/ቤት አብላጫ ድምጽ ውሳኔ ለምን አልተገዛችሁም? የዴሞክራሲን መርሕ ሳታከብሩ እንዴት «መርሕ ይከበር» ማለት ትችላላችሁ?*

ዴሞክራሲ አንድ መገለጫው እንዳልከው አብላጫ ድምጽ ነው:: ብቻውን ግን አይደለም:: ቁጥር አስልቶ አብላጫ የሆነው ይጠቀማል፣ተገቢ ነው ሊባል አይችልም:: በደርግ ጊዜም እኮ ተሰባስበው በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ አሳለፍን እየተባለ ስንት አሰቃቂ ነገር እንደተፈጸመ ሰምተናል:: አሁንም በፓርላማው ውስጥ እየሆነ ያለውን እያየን ነው:: የአብላጫ ድምጽ ሽፋን በአንድነት ውስጥ ተደገመ:: በቡድናዊ ስሜት መስራት ተጀመረ:: ም/ቤቱ መጀመርያ የነበረው ስሜት ከጥቂት ስብሰባዎች በኋላ ተቀየረ:: የሥራ አስፈፃሚው ሁልጊዜ የሚያሳልፈው ውሳኔ በአነጋጋሪ ጉዳዮች ላይ ሳይቀር ሁለት ግለሰቦች ተቃውሞ ውጪ «በአብላጫ ድምጽ አለፈ» ይባላል:: እንዲህም ሆኖ ቅሬታ ሲፈጠር ውሳኔው ከተላለፈ በኋላ ወደ ጠቅላላ ጉባኤ ትሄዳለህ::

*መጽሔታችሁን ባሳተማችሁበት ወቅት የገንዘብ እጥረት አጋጥሟችሁ እንደነበር ሰምቻለሁ:: በፓርቲው ውስጥ ያሉ አቅሙ ያላቸው አባላት አንዳንድ ወገኖች ወደፓርቲው ሲቀላቀሉ ለመጽሄት ማሳተሚያው ከሚያስፈልገው በሚበልጥ ወጪ የ«እንኳን ተቀላቀላችሁን» ግብዣ አድርገዋል:: ያንን አቅም ለማስተባበር ጥረት አላደረጋችሁም?*

የቡድንተኝነት ስሜት ነግሶ ነበር:: መጽሄቱ ከዚያ ሁሉ ጥረት በኋላ ሲወጣ ግን ኮርተዋል:: የሚገርመው ኢ/ር ግዛቸው በመጽሔቱ ላይ ቅሬታ አሳደረ:: በመጽሔቱ ውስጥ ካለው ይዘትና ስሜት ይልቅ «የወጣወ ፎቶ እኔን አይመስልም» አለኝ:: በአብዛኛው ስለብርቱካን በመፃፉ ሲብሰለሰል ቆይቶ «አንድነት አንድነትን አይሸትም» አለኝ:: መጽሔቱን ለማሳተም ከእኔ ይልቅ ወጣቶቹ ናቸው ብዙ የደከሙት:: «እኛ አንዳንድ ሺህ ብር እናዋጣለን፤ ሌሳውን አንተ ፈልግ» አሉኝ:: ዶ/ር ሽመልስ ደግሞ የአንድ ሺህ መጽሔት ዋጋ አስቀድሞ ከፈለ:: እንዲህ አይነት ጥረቶች ነበሩ:: ከወታ በኋላ ኢ/ር ግዛቸው እኔ እሰጥህ ነበር እኮ አለ:: ግን መጽሔቱ ሳይታተም ስምንት ወር ሙሉ የተቀመጠው በገንዘብ እጥረት እንደነበር ሁሉም ያውቃሉ::

*የገንዘብ ነገር ከተነሳ፣ ከፓርቲው ተባረራችሁ ከመባላችሁ በፊት ኦዲት ተደርጓል?*

እንዲያውም «መርህ ይከበር» ያልንበት አንዱ ጉዳይ የፋይናንስ ሪፖርት ቀርቦ የማያውቅ በመሆኑ ነውኮ:: ጠቅላላ የሥራ ሂደቱን አስመልክቶም ሪፖርት ቀርቦ አያውቅም:: ይህንን ጥያቄ ስናነሳ «ልክ ናችሁ መቅረብ አለበት» ያልተባለው በዴሞክራሲያዊ አሰራር አብላጫ ድምጽ የሚከበርበት ፓርቲ ስለሆነ ነው ሊባል አይችልም::

*በኮከበ ፅባሕ ት/ቤት በተጠራው አጠቃላይ ጉባኤ ላይ ተገኝተሀሃል? ጉባኤው ምን ይመስል ነበር? ጉባኤውን መጥራት የሚችለው ብሔራዊ ም/ቤቱ መሆኑን አመራሩ ሕገ-ደንባችሁን በመጥቀስ ገልጿል:: ብሔራዊ ም/ቤቱ እስኪጠራ ለምን አልጠበቃችሁም?*

የም/ቤቱ አባል ባልሆንም በኮከበ ጽባህ በተደረገው ጉባኤው ላይ ተገኝቻለሁ:: ብሔራዊ ም/ቤቱ ነው መጥራት የነበረበት ላልከው በመጀመሪያ ሰብሳቢ የለውምኮ:: ሰብሳቢው መጀመሪያ ዶ/ር ሽመልስ ነበር:: በኋላ መሐመድ ዓሊ ነበር ለቆላቸዋል:: ሁለተኛው ደግሞ እኛ የጠራነው ሕገ ደንቡ በሚያዘው መሰረት የመስራች ጉባኤ አባላቱን አንድ ሶስተኛ ይሁንታ ይዘን ነው እነሱ በኢምፔሪያል ሆቴል በጠሩት ጉባኤ የመጡት ስንት ሰዎች እንደነበሩ ይታወቃሉ:: ደግሞ እስከዛሬም ሪፖርት አላቀረቡም::

*የእሁዱ ጉባኤ አመራሩን መርጧል:: ቀጣይ ሂደቶቹም በመከናወን ላይ ይመስሉኛል:: ሕጋዊው አመራር ይህኛው ነው ማለት ነው? ምርጫው ሊካሄድ አንድ ወር ሲቀረው የመከናወኑ አንድምታስ ምንድነው?*

በእርግጥ በዚህ ጉዳይ ላይ መግለጫ መስጠት የሚችለው አመራሩ [አዲሱ] ነው:: ከምርጫው ጋር የተያያዘ እንዳልሆነ ግን ላረጋግጥልህ እወዳለሁ:: የምርጫው ጉዳይማ አልቋል:: ዕጩዎች ተመዝግበው፣ የምርጡኝ ቅስቀሳ እያካሄዱ ነው:: ሊቀጥሉ ይችላሉ:: ጉባኤው የሚያሳልፋቸውን ውሳኔዎች ግን ማክበራቸውን ማሳየት አለባቸው::

*ዞሮ ዞሮ ሁለት «የአመራር አካል ነኝ» የሚል መዋቅር አለ:: አሁን የተመረጠው በቀጣዩ ምርጫ ሂደት ውስጥ እጁን አያስገባ እንጂ «ሕጋዊው እኔ ነኝ» ካለ ያኛው ወገን ጥፋት አጥፍቷል ብሎ ሲያምን የቅጣት ውሳኔ ማሳለፉ አይቀርም:: እስከ አሁን ከነበረው ፍጥጫ አንፃር ምን ሊከሰት ይችላል ብለህ ትገምታለህ?*

ሁሉም ነገር የሚሰራው በሕገ-ደንቡ መሰረት ባቻ ነው:: ከዚያ በተጨማሪ ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀትን አስመልክቶ አገሪቱ የምትመራባቸው ሕጐች አሉ:: በዚያ ሁላችንም እንዳኛለን፣መቀታት ካለብን እንቀጣለን:: «የለም ሕግ አይገዛንም፣ ስልጣን አንለቅም»እያሉ ከቀጠሉማ  መንግስቱ ኃ/ማርያምን መሆናቸው ነው::

*በአገር ውስጥ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ቢኖርም በተለይ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን (እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን) አንተና ፕ/ር መስፍንን «መርሕ ይከበር» ከሚለው አካል እንድትወጡ እንዳሳሰቧችሁ ሰምቻለሁ:: ከሁለታችሁ ውጪ ያሉት አባላት የገዢውን ፓርቲ ሥራ በሰርጎ ገብነት እየሰሩለት ያሉና «የተቃውሞውን ጐራ ለመሸርሸር እየተካሄደ ያለው ዘመቻ አካል» ይሏቸዋል:: የቀረበላችሁን ማሳሰቢያ እንዴት ተመለከትከው?*

ይህን ያለው አሜሪካ የሚኖር አንድ ሰው ነው:: በመጀመሪያ ጥያቄውን ስናነሳ የጥያቄዎቹን መሰረት አምኖበት «አበጃችሁ ቀጥሉበት» ሲለን የነበረ ሰው ነው:: ይህ ሰው እዚህ ስራ አስፈፃሚው ውስጥ ወዳጆች አለት::- እንዲያውም አንዳንዶቹ የስጋ ዘመዶቹ ናቸው:: ለማሸማገል ሁሉ ሞክሮ እምቢ ሲሉት አቋሙን ለውጦ ዘለፋ ጀምሯል::

*ሌሎቹ በውጪ ያሉት ደጋፊዎቻችሁ ችግሩ ከተከሰተ በኋላ ምን አቋም ያዙ?*

እነሱ በተደጋጋሚ ያሉት «እናንተ አገር ትመራላችሁ ተብሎ ተስፋ የተጣለባችሁ ሰዎች በመካከላችሁ የተፈጠረውን ያለመግባባት ፍቱ ስትባሉ እምቢ እያላችሁ ወደፊት በአገር አመራር ላይ ያላችሁን ችሎታ እንዴት አምነን እንቀበላችሁ? በሚል በርካታ ጥያቄ አንስተዋል::

*በሁለንተናዊ ተሳትፎ የ«ዳያስፖራው» ሚና ምን ያህል ነው? እዚያ ሆኖ አመራሩን በ«ሪሞት ኮንትሮል» ለመቆጣጠር ይቃጣዋል፤እዚህ ያለው አመራርም ተጽዕኖውን ለመከላከል ቁርጠኝነት ይጎድለዋል የሚል ትችት ይቀርባል:: ትስማማበታለህ?*

እንግዲህ ይህን በሁለት ከፍለን ብንመለከተው ይሻላል:: ዳያስፖራው ገንዘብ ይረዳል:: በውጪ ያሉ መንግስታትን በማነጋገር፣ የፓርላማ/ኮንግረስ/ አባላትን በማነጋገር፣ ጉዳዩን በማስረዳት፣ አላማና ራዕያችንን በመግለጽ ብዙ እገዛ ያደርጋሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ በእነሱ ውስጥ በመሆን ሁኔታውን ተጠቅመው ገንዘብ ለመስራት የሚሮጡ አሉ:: ይህንን እነሱም ማወቅ አለባቸው:: የበኩላቸውን ገንዘብ ስለረዱ «እንዲህ አድርግ» ብለው አመራሩን ሊጠመዝዙት አይገባም ነበር:: አሁን ትንሽ ትንሽ የሚታየው ይህ ነው:: አመራር/አስተባባሪነት/ ላይ ያሉ አንዳንድ ዳያስፖራዎች በተለይ እንዲህ እያደረጉ ነው:: አሁን ግን በተለይ ተሳትፎ የሚያደርገው ተራ /አመራር ያልሆነ/ ዳያስፖራ እየገባው መጥቷል::

*ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን መሪያችን ናት ከማለት ባለፈ እየተደረጉ ያሉት ሕጋዊ ክትትሎች ምን ይመስላሉ?ምን እያደረጋችሁ ነው?*

በእኛ በኩል ከታሰረችበት ጊዜ ጀምሮ ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በበዓላት ተራ በመያዝ እየተመላለሱ ነው:: ዘመድ ነን በማለት ገብተው የጠየቁም አሉ:: ከእነሱ በኩል ግን እዚያ አካባቢ የደረሰም የለም:: በቅርቡ ለመጀመሪያ ጊዜ እነ አቶ ስዬ ሄደው ነበር::

*ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሚነሳው ቅሬታ እሷን ለመጠየቅ የሚችሉት የተመረጡ የቤተሰብ አባሎቿ ብቻ ናቸው የሚለው ነው:: ሕገ መንግስቱ በማያሻማ ሁኔታ ያጎናጸፋት መብት አለ:: ፍ/ቤት ከአንዴም ሁለቴ ሊጠይቋት በሚፈልጉ ወገኖች የመጎብኘት መብት እንዳላት ወስኗል:: ይህ የፍ/ቤት ውሳኔ ተግባራዊ ያለመሆኑ የሚፈጥረውን ጫና እንዴት ትገልጸዋለህ? አያይዘህ ማስተላለፍ የምትፈልገው መልዕክት ካለም ዕድሉን ሰጥቼሃለሁ::*

ኧረ ባለፈው ሳምንት ለሶስተኛ ጊዜም ለፍ/ቤቱ አመልክተናል:: የብርቱካን መታሰር በእውነት ለማንም አይጠቅምም:: የእሷ መፈታት ግን ለሁላችንም ይጠቅማል:: ብርቱካን ሴት ሆና፣ የልጅ እናት ሆናና በብዙ ነገሮች ውስጥ አልፋ የፖለቲካ መሪ ሆና የወጣች ዜጋ ናት:: ገዢው ፓርቲ ደግሞ ለሴቶች የተለየ ትኩረት እሰጣለሁ እያለ ነው:: የሕግ መከበር የሚመነጨው የማሕበረሰቡን ደህንነት ለማስጠበቅና ሁለንተናዊ ጥቀሞቹን ለማስከበር ነው:: መቻቻልን፣ ይቅር ባይነትንና አስተማሪነትን መገንባት ነው:: እና መንግስት ተጎድቶም ቢሆን ቢለቃት እላለሁ:: እስካሁን አስረናታል፣ እንልቀቃት ቢል ይህን እሴት ይገነባል፣ ይከበራልም ብዬ አምናለሁ:: አሁን እኮ እሷ በፖለቲካዊ ዕሳቤ እጅግ ገዝፋለች:: አሁን ደግሞ መንግስት እንዲገዝፍ ከፈለገ ይፍታት:: ማስተላለፍ የምፈልገውና እያልኩ ያለሁት ስለተራ የመገዛዘፍ ጉዳይ ሳይሆን የሚመለከታቸውን ወገኖች ታሳቢ በማድረግ ሂደቱ ሊከናወንበት ስለሚገባው እውነተኛ የይቅር ባይነት መንፈስ ነው:: ይህንን ነው ሁላችንንም የሚጠቅም ያልኩት::- ለሁላችንም ጥቅም ሲባል መፈጸምም ያለበት!

## ልዩቅኝት

# የፕሮፍ የ፹ ዓመት ጉዞ

- «በሆድ አንደኛ ነበርኩ» ይላሉ
- በቀን ከአንድ ፓኮ በላይ ሲጋራ ያጨሳሉ

**<u>በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ጉልህ እንቅስቃሴ የሚያደርጉት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም በዛሬው ዕለት ሰማኒያ ዓመት ይሞላቸዋል:: *አቤል ዓለማየሁ* የፕሮፌሰሩን ከፖለቲካ ውጪ ያላቸውን ህይወት ለመዳሰስ ያደረገው ጥረት እንዳሰበው ያህል ባይሳካለትም ተከታዩን ፅሁፍ አሰናድቷል::</u>**

*መኖሪያ* ቤታቸው ያጌጠው በዕድሜ ጠገብ ቁሶች ነው:: ሰባት ባለ ስፖንጅ ወንበሮች ከእነ ጠረጴዛው ግማሽ ክ/ዘመን አብረዋቸው ኖረዋል፤ የገዙት ቸርችል ጎዳና ላይ በ350 ብር ነበር:: ቤታቸውና ቢሯቸው [ቤታቸው ይገኛል] በመፃህፍት ታጭቋል:: የሚመለከቷቸው ቴፕ፣ ዴክ፣ የዕቃ ማስቀመጫ (ቡፌ) እና ውስጡ የተቀመጠው ሜታ ቢራ የሚል ብርጭቆ «የድሮ» የሚል ተቀጥላ ስማቸው አይነፈጋቸውም:: የሚነዱት ሰማያዊ ሽንጣም «ቮልቮ» መኪናም አካላዊ ውበቱን እንደጠበቀ ቢሆንም አሮጌ የሚባል ነው:: የሚኖሩት በኪራይ ቤት ነው:: ይህ ከሲኒማ

ኢትዮጵያ የጀርባ በር በኩል ቁልቁል ወደ በብሔራዊ ሎተሪ በኩል ሲወርዱ ባለ አራት ህንፃ አንደኛ ፎቅ በር አንኳኩተን አጭሩ የሰማኒያ ዓመት አዛውንት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ከፍተውልን ገብተን የታዘብነው ነው:: «ይሄ የምርጫ ጉዳይ ነው:: ቅሬታ የለኝም:: ድሮም ሆነ ዛሬ የሀብት ምንጭ ማጭበርበርና ለፍቶ ደክሞ ማግኘት ነው:: የእኔ ቃል ኪዳን ደግሞ ለዚህ አልነበረም::» ሲሉ ባላቸው ወቅታዊ የኑሮ ደረጃ እንደማይቆጩ ያስረዳሉ::

የተነሳሁበትን ሲመለከቱ ዛሬ ሰማይ ላይ ነኝ፤ በጣም ሀብታም ነኝ ብለው ያስባሉ:: «ተራ፣ ደሀ ሰው ነበርኩ:: ኮሌጅ ስገባም የምሄደው በባዶ እግሬ ነበር::» በማለት በንጽጽር የዛሬ ማንነታቸው ከፍ ያለ መሆኑን ያሳያሉ:: «የእኔን አይነት ኑሮ የሚኖር ስንት ኢትዮጵያውያዊ አለ?» በማለት የሚጠይቁት ፕሮፌሰሩ «የእኔ ኑሮ ዝቅ ያለ ቢመስልም የእኔን አይነት ኑሮ ያለው ኢትዮጵያዊ ከሁለት በመቶ አይበልጥም:: የሚያሳዝኑኝ 98 በመቶው ነው» ይላሉ::

ሚያዚያ 1 ቀን 1922 ዓ.ም. የዛሬ ሰማኒያ ዓመት አዲስ አበባ ውስጥ ተወለዱ:: የአንደኛ ዓመት ሻማ የት ሆነው አንዳጠፉ ብትጠይቋቸው «ይሄ የፈረንጅ ጥያቄ ነው::» ሲሉ ምላሻቸውን ይጀምራሉ:: «የእናንተ ትውልድ ልደቱን ሊያከብር ይችላል:: የእኔ ትውልድ እኮ የጃንሆይን ልደት ካልሆነ የራሱን ልደት አክብሮ አያውቅም::» ይልዎታል:: ፕሮፌሰር መስፍን በሰማኒያ ዓመት ጉዟቸው አንድም ቀን የልደት ኬክ ቆርሰውና ሻማ አጥፍተው አያውቁም:: ልደታቸውን ለማክበርም እቅድና ፕሮግራም በመንደፍ ጊዜ ማጥፋትን አይመርጡም::

በልጅነት እድሜያቸው እግር ኳስ ይጫወቱና ጅምናስቲክ ይሰሩ ነበር:: ጡንቻቸውንም ለማፈርጠምም ይተጉ ነበር:: «ጡንቻ ማፈርጠም በጣም ትልቅ ነገር መስሎ ይታየኝ ነበር:: በዊንጌትና በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እንደኔ ያለ የጡንቻ ፍቅር ያደረበት የማውቀው ገብረክርስቶስ ደስታን ነው:: ቻርልስ አትላስ ከሚባል የታወቀ የጡንቻ አሰልጣኝ ጋር እየተፃፃፈ ይሰለጥን ነበር:: በትምህርት ቤት የሚያገኘው ወተትም ስለማይበቃው በቀን አንድ ሊትር በኮንትራት ይመጣለት ነበር:: በዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ውስጥ በሆድ አንደኛ እኔ፣ ገብሬ ሁለተኛ ነበርን፤ እኔ እንዲያውም መብላት የማቆመው ጠግቤ ሳይሆን ጥርሴን ሲደክመኝ ነበር::» ሲሉ በአገቱኒ ላይ ስለራሳቸው ይናገራሉ::

24 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ ቆራቢ ነበሩ:: የእሳቸው ትውልድ ሴት የማቀፍና መለኪያ መጨበጥ ታሪካቸውን በኩራት ከሚተነትኑበት የወሬ ጫፍ፤ [ውቤ በርሐ] መሰል ቦታዎች የተቆጠቡ ነበሩ:: ከአንድ ሚስት ሦስት ልጆችን አፍርተዋል:: ከባለቤታቸው ጋር ከተለያዩ ከአርባ አመት በላይ አስቆጥረዋል::

## «አንተ» የፍቅር ወይስ የጥላቻ?

አውራ አምባ ማህበረሰብ ዘንድ ተገኝታችሁ በየትኛውም የእድሜ ክልል የሚገኝ ግለሰብ «አንቱ» እያላችሁ ብታዋሩ ያለመታከት እያስቆሙ አንተ ወይም አንቺ የሚል ቃል ከአፍዎ እንዲወጣ ሳይሰለቹ ደጋግመው ይነግሩዎታል:: «ግንዱ ተለያየ እንጂ የሰው ዘር አንድ ነው፤ የቤተሰብን አባል አንተ፣ ሌላውን አንቱ እንድንል ማን ፈቀደልን? ሁላችንም የአዳም ዘሮች ነን» የሚል እምነት ስላላቸው ነው:: አንተ/ አንቺ ማለታቸውም የፍቅር ስሌት ነው::

ፕሮፌሰር መስፍን ብዕራቸውን አንስተው በሚያሰፍሯቸው በማንኛውም ፅሑፎች ላይም ሆነ በቃለ-ምልልስ ወቅት ምላሽ ሲሰጡ የሚጠቅሷቸው ስሞች በየትኛውም የስልጣን ደረጃ ላይ ቢገኙ እንኳን «አንተ» ማለት ይቀናቸዋል፡፡ ይህን አስመልክቼ ጥያቄ ሳቀርብላቸው «ጥያቄው ራሱ ያስገርማል» ሲሉ ምላሽ ለመስጠት ተንደረደሩ፡፡

«አንተንም አንቱ» በለኝ ነው የምትለኝ?

«አላልኩም፡፡ ጥያቄው ግልፅ አይደለም?»

«በእድሜዬ ከእኔ በታች የሆነንና በመደበኛም አንተ ስል የምጠራውን ሰው ሁሌም 'አንተ' እለዋለሁ»

«የእኔም ጥያቄ ይህንን እንዲያብራሩልኝ ነው፡፡»

«ታዲያ ይህንን ለምን ትጠይቀኛለህ? ግልጽ የሆነ ነገር እኮ ነው፡፡ አንተ ይህንን ማሰብ ካልቻልክ ሌላ ምን ማሰብ ትችላለህ? እኔ ልጄን ሚኒስትር ብትሆን «እርስዎ» ልላት ነው? ምንም ምክንያት የለኝም፡፡ ወንበርን እንጂ ሰው አላከብርም፡፡ ፍርድ ቤት በጣም አከብራለሁ፡፡ በምፅፍበት ጊዜ አንተ ነው የምለው፡፡ ለምሳሌ ከፕሬዚዳንቱ ጋር «አንተ» ነው የምንባባለው፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት ነው፡፡ ስፅፍ ግን «አንተ» አልለውም፡፡ ሌላው ግን ዛሬ ሚኒስትር ይሆናል፣ ነገ ይወርዳል ከነገ ወዲያ ይወጣልና ከእሱ ጋር አልሽከረከርም፡፡ «አንተ» ብዬ እፅፋለሁ፡፡ ከጥላቻ ወይም ከንቀት የመጣ አይደለም፡፡»

## «አገቱኝ» በ80 ዓመት

የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በፍልስፍና አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም (እንደ እሳቸው አገላለጽ በቅጥያነት) ጂኦግራፊ ይማሩ ነበር፡፡ የወቅቱ የትምህርት ሚኒስትር የነበሩት አቶ አካለወርቅ ሀብተወልድ «እስካሁን አንድም «ጂኦግራፈር» የለንም በዚህ ቀጥል» በማለት ስለመከሯቸው በጂኦግራፊ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡

በፈረንጅ አፍ «vulnerability to famine», «The horn of Africa conflict & poverty» እና ሌሎች መፅሐፎችን የፃፉ ሲሆን በአማርኛ፤ ኢትዮጵያዊነት ልማት በህብረት፣ ኢትዮጵያ ከየት ወዴት?፣ የክህደት ቁልቁለት፣ እንጉርጉሮ (የግጥም መጽሐፍ)፣ አገቱኒ ይጠቀሳሉ፡፡ «"ኢህአዴግ" ከመጣ ወዲህ ያለ ሳንሱር መፃፍ ስለተቻለ የአማርኛ መፅሐፎቼን የፃፍኳቸው ባለፉት 19 ዓመታት ነው፡፡» ይላሉ፡፡

የፕሮፌሰር መስፍን ዕድሜ አንድ ክፍለ ዘመን ለመሙላት 20 ሻማ ማጥፋት ብቻ ቢቀረውም እርጅና አልተጫጫናቸውም፡፡ ቁጭ፣ ብድግ እያሉ ሲንቀሳቀሱ ህንድ ድረስ ለህክምና ያስኬዳቸው የጤና መታወክ በሙሉ ጤንነት እንደተቀየረ ያስታውቃል፡፡ የድምፃቸው ለጋነት «ወጣት ነኝ» ብሎ ግብግብ የገጠሙ ያስመስለዋል፡፡ ስምንት አስርት የደፈነ ሰው አይመስልም፡፡

ከወጣትነት እድሜያቸው ጀምሮ የሚያጕፍሩት ፀጉራቸው እንደጢማቸው ሁሉ ዕድሜውን ቆጥሮ ነጭ ብቻ አልሆነም፡፡ ቅንድባቸው ላይ ሽበት ለዓመል አይታይም፡፡ ምግባቸውን የምታበስልላቸው ሰራተኛ ብትኖራቸውም እሳቸውም ሸሚዛቸውን ጠቅልለው ወደ ጓዳ ይገባሉ፡፡ «ባለሙያም ነኝ» ባይ ናቸው፡፡ አይነት ምግብ (በየአይነቱ) ሰርተው ከገበታ ላይ ለማሰናዳት

አይሰንፉም፡፡ መስራት የማይችሉትን ዶሮ ወጥ መብላቱም ላይ እስከዚህም ናቸው፡፡ መረቁ ሲናፍቃቸው ወጣ ብለው አዘው ይመገባሉ፡፡

በተረጋጋና በሰከነ ሁኔታ ነገሮችን ለማየት 80 ዓመት ጥሩ ጊዜ መሆኑን ያምናሉ፡፡ በዚህ ዕድሜ ብዕር ማንሳት ነገሮችን በተረጋጋ ሁኔታ ለማየት አጋጊ ወቅት አድርገው ያስቡታል፡፡ «በጉርምስና ወቅት የምትፅፈው ስሜትህ ያይልና ሚዛናዊነቱ ሊያጋድል ይችላል፡፡ ሚዛናዊ ለመሆን 80 ዓመት ጥሩ ዕድሜ ነው፡፡ ያከማቸኸውን ለመጠቀም የተመቸ ጊዜ ነው» ይላሉ፡፡ የሰው ልጅ ጤንነቱ ጥሩ ከሆነ መስራት ከቻለ እርጅና የሚባል ነገር እንደሌለ ያስባሉ፡፡ ይህ ወቅት ካከማቹት ልምድ አንፃር የተሻለ እንጂ ያነሰ ጊዜ አድርገው አይቆጥሩትም፡፡ «አገቱኒ»ም የዚህ ውጤት መሆኑን ይናገራሉ፡፡

«አገቱኒ» ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ ገበያ ላይ የዋለው የፕሮፌሰር መስፍን መፅሐፍ ርዕስ ነው፡፡ ቃሉ የግዕዝ ሲሆን ትርጉሙም «አገቱኝ» ማለት ነው፡፡ 193 ገጾች ያካተተው ይህ መጽሐፍ ግላዊ ማንነታቸው (በወፍ በረር)፣ የምርጫ 97 ቅድመና ድህረ ታሪኮች እንዲሁም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደትን ዳሰውበታል፡፡ በመጽሐፉ ላይ በአምስት ዓመታቸው አካባቢ አባታቸው ወደ ማይጨው ከዘመቱበት ጊዜ አንስቶ የተለያየ ጠመዝማዛ መንገዶችን ማሳለፋቸውን የሚገልፁት ፕሮፌሰሩ በህይወት ጉዞ የተለያዩ ችግሮች ቢገጥሟቸውም «ለምን ተፈጠረኩ ብዬ ተማርሬ አላውቅም» ሲሉ ለአውራምባ ታይምስ ያስረዳሉ፡፡ «ባልተፈጠርኩ ብዬ አላውቅም፡፡ ሰውና ኢትዮጵያዊ መሆኔን የሚያስጠላ ነገር የገጠመኝ በ1951 ዓ.ም. ትግራይ ውስጥ የተከሰተው ችጋርን ሄጄ መመልከቴ ነው»፡፡ ስቃይ፣ ረሀብና ሞት የተፈራረቁበት ይህን ታሪክ «እስከዛሬ ድረስ ከህሊናዬ ሊጠፉ ያልቻለ፣ ኢትዮጵያዊ መሆኔን ዋጋ ቢስ ያደረገብኝ» ይሉታል፡፡ ከዚያ ጊዜ በኋላም ከርሀብ ጋር ግብግብ የገጠሙ ዜጐችን በቅርብ ርቀት መመልከትን አይፈልጉም፡፡ በጉዳዩ ላይም በፈረንጅ አፍ «vulnerability to famine» በሚል ርዕስ መጽሐፍ ጽፈዋል፡፡

በእሳቸው ዕድሜ ያሉ አዛውንቶች በልጅነት እድሜያቸው ወደ አስኳላ የመላክ እድላቸው አናሳ ነበር፡፡ ፕሮፌሰሩ ግን በዚህ አይስማሙም፡፡ «የትምህርቱ ዓይነት ይሆናል እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ ትምህርት ችግር አልነበረውም፡፡ በየሰፈሩ ተማሪ ቤት ነበር፡፡ ሜዳና ዛፍ ስር እየተሰበሰብን ደሞዝ የሌላቸው አስተማሪዎች ያስተምሩን ነበር፡፡» ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ ዳዊት ደግመው ካጠናቀቁ በኋላ ቅዳሴና ዜማ ለመማር በሰፈራቸው ወደሚገኝ ሌላ ትምህርት ቤት አቅንተዋል፡፡ ከዚያም ተማሪዎችን በአዳሪነት ይቀበል በነበረው ተፈሪ መኮንን በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት ስለነበራቸው በነፃ ተምረዋል፡፡ በ«አገቱኒ» መጽሃፋቸው እንዳሰፈሩት በተፈሪ መኮንን አንድ አስተማሪ በክፍሉ ተማሪዎች ይናደድና ከእነ ዘር ማንዘራቸው ሙልጭ አድርጐ ይሰድባቸዋል፡፡ ወሬው መስፍን ጆሮ ይደርስና በንዴት የተቀጣጠለውን ቡድን ይቀላቀላሉ፡፡ ቀስ በቀስን ከባድ ረብሻ ይነሳል፡፡ አንማርም ብቻ ሳይሆን የመጣውን ባለስልጣን ሁሉ አንሰማም በማለታቸው ረብሻውን ይበልጥ አፋፋመው፡፡ ትምህርት ቤቱ በክቡር ዘበኛ ይከበብና ጃንሆይ ከነልጆቻቸውና ከእነ ሚኒስትሮቻቸው ይመጣሉ፡፡ [«ከየትም ለቃቅመን አምጥተን» ብለው ጃንሆይ ተናገርዋል የሚባለውም በዚሁ ቀን ነው፡፡] ሃያ ሁለት ልጆች ከተፈሪ መኮንን ወደ ሌሎቹ ትምህርት ቤቶች ተዛወሩ፡፡ እዚህ ቁጥርም ውስጥ መስፍንም ተደምረዋል፡፡ «ከሦስት ወራት በኋላ የለንደን «ማትሪኩሌሽን» ተፈትነው ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ሲከፈት እዚያ ገባሁ፡፡ እግዚአብሔር ይመስገንና በጠመዝማዛው መንገድ እዚህ ደረስኩ፡፡» በማለት ያለፉበት ጎዳና እንቅፋት እንደነበረው ይሳያሉ፡፡

«ኢትዮጵያ ውስጥ ሰማኒያ ዓመት እደርሳለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። ራሴን ችዬ መንቀሳቀስ እስከቻልኩ ድረስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ብኖር ደስ ይለኛል። የሚሉት» ፕሮፌሰሩ ከሞታቸው በፊት ለራሳቸው /ለግል ህይወታቸው/ ምንም እንደማይመኙ ይገልፃሉ። «ኢትዮጵያ ግን ከማለፌ በፊት ዴሞክራሲያዊ ሆና፣ ህዝቡ ሙሉ ነፃነትና መብት ኖሮት፣ የሀገሩ ባለቤትና የስልጣን ምንጭ ሆኖ ማየት እፈልጋለሁ።»

## ከኢህአዴግ ጋር በስልጣን ተደራድረዋል?

ኢህአዴግ አዲስ አበባን በተቆጣጠረበት ዓመት ለንደን ላይ «ስልጣን ስጡኝና ልምጣ» ብለው ተደራድረዋል ተብሎ ስማቸው ይነሳ ነበር። «ይህን የተናገረው የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ (ስዩም መስፍን) ነው። እሱን በአካል አግኝቼውም አይቼው አላውቅም። ተነጋግረንና ሰላምታ ተለዋውጠን አናውቅም። «ይህንን ብሏል» ተብሎ በጋዜጣ ላይ ነበርኩኝ። በጊዜውም መልስ ሰጥቻለሁ። የተነጋገርነው ከአቶ መለስ ጋር ሲሆን አብረውን ሌሎች ሰዎችም ነበሩ። ፕሮፌሰር እንድርያስ፣ አብዱልመጅድ፣ ይስሐቅ ክፍሌ፣ ሄኖክ ክፍሌ ነበሩ። (በጀርባ በኩል) ብዙ ሰዎች ተደርድረው ነበር። እዚያ ውስጥ እሱ ይኑር አይኑር አላውቅም። አቶ መለስ ይህን ሲል ሰምቼው አላውቅም። እሱ በኋላ ሆኖ እንዴት እንደሰማ አላውቅም። ያልሞቱ ሰዎችም ምስክር አሉ። እናንተም ጭንቅላት ቢኖራችሁና ብታስቡ እኔ ማን ነኝና እነሱ የሞቱበትንና የተዋጉበትን ስልጣን «ለእኔ አስረክቡና የእኔ ጭፍራ ሁኑ» እንዴት እላለሁ? ብላችሁ ታስባላችሁ?። ይሄ እሱ ውሸት ለምዶበት የተናገረው ነው።»

## አልፈልገውምን በሰማንያ እሺ?

«በትምህርት ፈጠንኩና አስተማሪዬ (አለቃ ታምራት የሚባሉ ነበሩ) ከአለቆች አንዱ አደረጉኝ፤ መጀመሪያ ስልጣን የቀመስኩት በዚህ ነው፤ ጣመኝ፤ አንደ ተማሪ «ጸ» ስለው «ሰ» ያለ እንደሆነ ጆሮው እስኪቀላ ማሸት አንዱ የስልጣን መግለጫ ነበር፤ በዚያ ላይ አለንጋ ወይም አርጩሜ አለ፤ የመጀመሪያው ደረጃ የስልጣን መባለግ ነበር።»

አገቱኒ ገጽ 3

ፕሮፌሰር መስፍን በተለያየ ወቅት የስልጣን ጥመኝነት እንደሌለባቸውና እንደማይፈልጉት ከመናገር ተቆጥበው አያውቁም። በኢትዮጵያ የመጨረሻ በነበረው የንግስና አገዛዝ ዘመን የጊሚራ አውራጃ ገዢና፣ የጊምቢ አውራጃ አስተዳዳሪ ነበሩ። «በጊምቢ የተሾምኩት በአፍሪካ አዳራሽ የዩኒቨርስቲ የቀድሞ ተማሪዎች «ገጠራቱ ኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ ባዘጋጁት ውይይት ላይ በአደረግሁት ንግግር ውስጥ «ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ ያልተወሰነ የአክሲዮን ማህበር እንጂ መንግስት የለም» በማለቴ አስቆጥቼ ስለነበር ነው። ሹመቱ እኔን ከዩኒቨርሲቲው ከአዲስ አበባ ለማስወጣት እንደነበር ግልጽ ነው። እምቢ በማለቴ የጃንሆይን ትዕዛዝ ባለመቀበል ተብሎ አንድ ሳምንት ታሰርኩ ... ጊምቢን ተከትሎ ያጋጠመኝ ስራ በግዴታ የተጫነብኝ ነበር።» በማለት ስልጣን ላይ ፈልገው አለመቀመጣቸወን ለማሳየት ሞክረዋል። «አንዳንድ ሰዎች በማወቅም ባለማወቅ መርማሪ ኮሚሲዮንን ደርግ እንዳቋቋመው አድርገው ይናገራሉ፤ ይጽፋሉም» የሚሉት አዛውንቱ «ማንበብ ለሚችል ሰው መቼ እንደተቋቋመ አዋጁን ማየት ብቻ ነው።» ሲሉ በከፍተኛ ድምጽ ተመርጠው

በሊቀ-መንበርነት ይመሩ ስለነበረው ወንበር ያስረዳሉ። ህዳር 14/1967 ስድሳዎቹ ባለስልጣናት ከተገደሉ ዕለት ጀምሮ ወደ መርማሪ ኮሚሲዮን መሄድ እንዳቆሙም ይናገራሉ። በደርግ ዘመንም ለተወሰነ ጊዜ የወንበሩ የበላይ ነበሩ።

«የአስመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ሁኑ» የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው «መምህራን ለመቅጠር እርዳታ ከየትም ማግኘት እንድችል በመጠየቄ፣ ማርክሲስታዊና ሌኒናዊ ፍልስፍና ከአንድ ትምህርት በዘለለ መልኩ በሌሎች ትምህርቶች ውስጥ እንዳይገባ በማለት ያቀርቧቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንዳላስመረጧቸው ጠቁመዋል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት እንዲሆኑ በኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም ተጠይቀውም «አልፈልግም ብዬው ትቶኛል» ሲሉ በ«አገቱኒ» ላይ አስነብበዋል።

በ1997 የቅንጅት ፓርቲ አባል ይሁኑ እንጂ በስራ አስፈፃሚ አባላት ውስጥ ስማቸው አልነበረም። ለምርጫም አልተወዳደሩም። ስላልፈለጉም ይህን አለማድረጋቸውን በተለያየ ጊዜያት አስረድተዋል። ባለፈው ሳምንት መጀመሪያ ግን በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ መስራች አባላት ስም በኮከበ ፅባህ ትምህርት ቤት በተካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የፓርቲው ምክትል ሊቀ-መንበር ሆነው ተመርጠዋል። አንድነት ፓርቲ እንዳባረራቸው የሚገልፀውና «መርህ ይከበር» ሲሉ ሲንቀሳቀሱ የነበረው ይኸው ቡድን ህጋዊ ሰርተፍኬት ከያዘው አንድነት ፓርቲ በተቃራኒ ቆሟል። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያምን «ስልጣን አልፈልግም ሲሉ ኖረው ኖረው ...?» ብላችሁ ብትጠይቋቸው «የብርቱካን ወንበር ባለ አደራ ነኝ። ወንበር ፈላጊ ፖለቲከኛ አይደለሁም። ስልጣንና አገር ማስተዳደርን አልፈልግም። በጉባኤው ላይ እንዴት እንደተመረጥኩ መጠየቅ ትችላላችሁ» ሲሉ ይናገራሉ። የመርህ ይከበር አባል ደበበ እሸቱም ልምዱን የሚያካፍል፣ የከረሩትን የሚያረግብ፣ ያስፈልጋል ስለተባለና መሪያችን ወ/ት ብርቱካን ከታሰረችበት ጊዜ አንስቶ የነበሩ በመሆኑ የእሷ አደራ አለብዎት ተብለው አባሎቹ ተንበርክከው ከብዙ ልመና በኋላ ነው የተቀበሉት» ሲል ለአውራምባ ታይምስ ተናግሯል።

## «ደደብ ነህ»

ከፕሮፌሰር ጋር ያደረኩትን ቆይታ «ግብ ግብ» ብሎ መግለጽ ሳይቀል አይቀርም። ቀናዊነትን በፍፁም አልተመለከትኩባቸው። የፃፍኳቸውንም ሆነ ያልፃፍኳቸውን ነጥቦች ዙሪያ ስናወራ ቀጥተኛ መልስ ከመስጠት ይልቅ ቁጣ አዘል ግሳጼን ነበር የመረጡት።

ቤታቸው በቀጠሮ የደረስኩት ሰማኒያ ዓመታቸውን ምክንያት አድርጌ ከፖለቲካ ህይወታቸው ውጪ ያሉ፣ እስከ ዛሬ ያልተወሩና «አሁን ይሄ ምን ይጠቅማል?» ሊባሉ የሚችሉ ቀለል ባሉ ጉዳዮች ዙሪያ ለመወያየት ነበር። በተለያዩ ሚዲያዎች ይቀርብላቸው ከነበረው ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ጋር አወዳድረውት ይመስለኛል ጥያቄዎቼ አልተመቿቸውም ነበር። በፖለቲካ ዙሪያ የሚያጠነጥኑትን እንኳን ከመመለስ ይልቅ «እዚያ መጽሐፍ ላይ ፅፌዋለሁ፣ እዚያኛው ላይ ተናግሬው ነበር» እያሉ ሙግት ይገጥሙኝ ነበር። እንደ ልብ ከማይገኙት መጽሐፎቻቸው አንፃር የአንባቢን የማወቅ መብት ታሳቢ በማድረግ የቤት ስራ መስጠቱን ለምን ምርጫቸው እንዳደረጉት ልንረዳዳ አልቻልንም ነበር።

በአሁኑ ሰዓት በውጪ ሀገር ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን መሀከል ግርማ ካሳ የተባሉ ፀሐፊ «መርህ ይከበር» ከሚለው ቡድን ጋር መኖራቸውን ወቅሰው ራሳቸውን እንዲያርቁ ባቀረቡባቸው

ትችት ዙሪያ አስመልክቼ ጥያቄ ሳቀርብላቸው «በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ያለ ሰው ተናገረ ብለህ በቅርብ ያለውን ሁኔታ የምታውቀው አንተ ይህንን ጥያቄ ከጠየቅክ *ደደብ ነህ* ማለት ነው» ብለውኛል፡፡ የጋዜጠኝነት ስነ ምግባር የተባለ ወሬን ከሚመለከተው ቀጥተኛ አባል ጠይቆ ማረጋገጥን ስህተት ብሎት እንደማያወቅና እንደማይለውም ስገልጽላቸው ያቀረቡልኝ ስነ-አመክንዮዋዊ መልስ ዘና የሚያደርግ ነው፡፡ «*መስፍን ጅብ ነው ቢሉህ መጥተህ ጠይቀህ ልታረጋግጥ ነውን?*» ነበር ያሉኝ በቁጣ ሲጋራቸው በፍጥነት ከአፋቸው በማውጣት፡፡

በቀን አንድ ተኩል የሚደርስ «smoking kills» የሚል ጽሁፍ ያረፈበትን ባለ ነጭ ፓኬት «ማልቦሮ» ሲጋራ ያጨሳሉ፡፡ አርባ ደቂቃ በማይሞላ ቆይታችን አራት ሲጋራዎችን ከንፈራቸው ላይ አድርገው ለኩሰዋል፡፡

በህይወት ዘመናቸው ካገኟቸው ሰዎች መሀከል የሚያደንቋቸው ኢትዮጵያውያን የሆኑም ያልሆኑም ግለሰቦች ቢኖሩም እንደ የጅብራርታሩ ቋጥኝ ይድነቃቸው ተሰማ የሚቀጩበት የለም፡፡ «ብዙዎች የሚያውቁት በስፖርት ስሙ ብቻ ነው፡፡ ይሄ ሰው በእንግሊዘኛ፣ በፈረንሳይኛ፣ በጣሊያኒኛ፣ በአረብኛ የሚነጋገርና መጽሐፍት የሚያነብ፣ በአስተዳደርና በህክምና መፃህፍት የፃፈ ኢትዮጵያ ያለተጠቀመችበት ታላቅ ሰው ነው፡፡ እዚህ የደረሰው በራሱ ጥረት ነው፡፡» በማለት ያወድሷቸዋል፡፡

በመፃህፍት ተከበው ይውላሉ፡፡ ምራቃቸውን የማያስውጥ ነገር ሲመለከቱም ሂሳቸውን ለማስፈር ብዕራቸውን ያነሳሉ፡፡ ኬክ ለመቁረስ፣ ሻማ ለማጥፋት ቀጠሮ ባይዙም፣ ቀኑን ለማሰብ ያደረጉት የተለየ መሰናዶ ባይኖራቸውም ዛሬ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ስማቸው በጉልህ የሚጠራው ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ሰማኒያ ዓመት ሞልቷቸዋል፡፡ «ቫይረስ» አጥፍቶባቸው በድጋሚ የፃፉትን መፅሐፍ ለአንባቢ ባደረሱና ፓርቲያቸው ምክትል ፕሬዚዳንት ባደረጋቸው ማግስት፡፡

*«...አንዳንድ ጊዜ የሚያስገርምና በጥልቀቱም በክብደቱም የማይረሳ ነገር ይጋጥማል፤ አንድ ጊዜ ለውሐ አንድ ሺህ ስድስት መቶ አሥራ ሰባት ብር ያህል ከፈልኩ ብዬ በጋዜጣ ጽፌ ነበር፤ አንድ የማላውቀው ሰው መንገድ ላይ ሰላም አለኝና ሰላምታ ተለዋወጥን፤ በጋዜጣ ስለጻፍሁት የውሐ ዋጋ አንስቶ «እባክዎን ትንሽ ልርዳ» አለኝ፤ እኔም ጉዳዩ ያለቀና የተዘጋ ነገር መሆኑንና እርዳታም እንደማያስፈልገኝ ኮስተር ብዬ አስረዳሁት፤ እሱ ግን አጥብቆ የእግዚአብሔርን ስም እየጠራ ለመነኝ፤ አመስግኜው እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብሎ ሰላምታ ሰጥቼ ልሄድ ዘወር ስል «በኢትዮጵያ አምላክ!» አለኝ፤ ደነገጥሁ፤ እጄን ዘርግቼ ገንዘቡን ተቀበልኩትና አመስግኜው ሄድኩ፤ ከመደንገጤ የተነሳ ስሙንም አልጠየቅሁትም፡፡ አሁን መንገድ ላይ ባየው አላውቀውም፤ ሁሌም ይቆረቁረኛል፤ ቤቴ ከገባሁ በኋላ ሳየው ጥቅልል አድርጎ የሰጠኝ አምስት መቶ ብር ነበር፤ ክፉ ቀን ጥሩ ነው ትሕትና ያስተምራል፤ ቸር አድራጊ ለምኖ፣ ተቀባይ ተለምኖ! ምን ሠርቼ ለዚህ በቃሁ?» ገጽ 18*

«እኔ በመጨረሻ የነበርኩበት ግቢ ስንገባ የአይጥ ሰራዊት እንዲቀበለን የታቀደ ይመስል ነበር፤ በወለሉ ላይ፤ በግድግዳው ላይ፤ በጣሪያው ላይ፤ በተኙ ሰዎች አፍንጫ ላይ ጭምር እንደልባቸው ይንሸራሸሩ ነበር፤ በተደጋጋሚ አቤቱታ አቅርበን አንድም ነገር አልተደረገም፤ እኛ

መድኃኒት ገዝተን ለማስመጣትም ስንጠይቅ የነበረው ውጣ ውረድ ብዙ ጊዜ የፈጀ ነበር፤ በመጨረሻም በመከራ መድሃኒት ብናስገባ ለቅመን እንድናስረክብ ተገደድን፡፡ አስተሳሰቡን መረዳት ያስፈልጋል፤ አይጦቹ በሚያመጡት የተለያየ በሽታ ብንሞት ምንም አይደለም፤ ነገር ግን ድንገት በመርዙ ሰው ቢሞት መጥፎ ነው፤ የአይጦቹ አደገኛነት የተረጋገጠ ሲሆን ሰው በአይጥ መርዝ የመሞቱ ዕድል በጣም ያነሰ ነው ብሎ ማሰብ ከባድ ሆነባቸው፡ ገጽ 59-60

ከአገቱኒ የተወሰደ